እንጨት ለቀማ መላክና ፣ ባለትዳር ለሆነችው ሴትዮ ነገሩን ነግሮ ከእንጨት ሰበራ መልስ ምቹ በሆነ መንገድ ይዛቸው እንድትመለስ ።

ልኬለሽ እንደ ተለመደው ፣ መጫኛዋን ጠቅላና ድግድጋቷን አሳምራ ከባልንጀራዋና ከተመከረችው ሴትዮ ጋር እንጨት ሰበራ ስትሔድ ፣ ምንዳዬና ሁለት ጓደኞቹ ፣ ጢሻ ውስጥ አድፍጠው እየተሟሟቁ አሳለፏቸው ። ቀስ ብለውም ባሳቻ መንገድ ተከተሏቸው ።

ልኬለሽ ስትሰቅ ፣ ስታወራ ፣ ስትዘፍን ፣ ስትቀልድ ——— የሚሰማት ምንዳዬ ፣ ጠልፏት እስኪገባ ቸኮለ ። የልቡ ምት ፈጠነ ። እያያት ናፈቃት ። ድምጿ እንደ ውሃ አዟሪት ሕሊናው ውስጥ ተሽከረከረ ። የሚያይና የሚሰማው ሁሉ ደስ አለው ። እነ ልኬለሽ እንጨታቸውን ተሸክመው ወደ ቤት ሲመለሱ ፣ እነ ምንዳዬ እየተከተሉ ከተመከረበት ቦታ ደረሱ ። ልኬለሽ ከመኻል ሆና እየዘፈነች ስትጓዝ ፣ ምስቱም ወንዶች ሴትዮዋን አሳለፉና ሁለቱ የልኬለሽን ሸክም ከግራና ቀኝ ድንገት ብድግ ሲያደርጉት ፣ ምንዳዬ ማንገቻውን ባንገቷ በኩል አወለቀና ሁለት እጅዋን ይዞ ሲሸከማት እሪታዋን አቀለጠችው ።

"ዝም በይ ! እስቲያባሽ ትጮሂያለሽ !" አላት በቁጣ ። ኡኡታዋን ስታስነካው አውርዶ አፏን አፈነው ። አንደኛው ባልንጀራው አሮጌ መቀነቷን ፈትቶ አፏን አሰረና ፣

"ና አሳዝለኝ" አለው ሌላውን ። ልኬለሽ አልታዘልም በማለት ባለ በሌለ ኃይሏ ተፈራገጠች ። አልሆንላትም ። እንድ ሁለተዬ ቀላል ጥፊ እንደ ቀመሰች ፣ ከማይለቅ ወጥመድ እንደ ገባች ዐወቀች ።

"ዋ ! እንዲች ብላችሁ አንዲት ወሬ ብታወሩ ! በሉ ቀጥ ብላችሁ ሒዱ" ተባሉ ሴቶቹ ። ጓደኛዋ እንጨቷን ጥላ እያለቀሰች ፣ ቤትዮዋ እንዳላወቀች ፣ "ምነው ዛሬ ቀን እግሬን በሰበረው" እያለች ጉዞ ቀጠሉ ።

ልኬለሽ ኡኡ እንዳትል ታፍናና የዱላ ውርጅብኝ ፈርታ ከፊት በምንዳዬ ፣ ከኋላ በባልንጀራው ታጅባ እየንፈረቀች ወደ ምንዳዬ ቤት ታዝላ ስትገባ ዕልልታው ቀለጠ ።



## ምዕራፍ ሠላሳ አራት

ምንዳዬ ፣ በዕለቱ ከቀኛዝማችና ከአቶ ወርቅነህ መዘውር ጋር ስለዋለው ውሎ ሲያወራላቸው ፣ "እንዳንድ ቀን ደሞ እሚያሯሩጥ ነገር አለባቸው" አለች ልኬለሽ ። "ድንገት ብድግ ይሉና መንገድ ይገባሉ ፤ ዛሬስ አይመለሱም ሲባሉ ፣ ከተፍ ይሏታል ። ሰው ይደክመዋልን እማያውቁ ሰውዬ ! እኔ እንዲያው አቅም ቢኖረኝ ሌላም አልመኝ ። እሳቸውንም ጠበንጃ አሸክሞ ሲያስሮጡ ማዋል ነበር ! ታዲያ በየት !" አለች እየሣቀች ።

"ምን በደሉሽ ልጄ ? እኛስ 'ዕድላችን' ሆኖ ነው ፣ እሳቸው ደሞ ምን በወጣቸው ? መቼም ሰውን ተጠላነው ፣ የኛን ክፉ ለሱ ነው ።"

አልመለሱለትም ።

ቀኛዝማች ፣ ስለ ልኬለሽ መኖር ወይም አለመኖር ደንታ የላቸውም ። በሳቸው ዐይንና ግምት ፣ በአካባቢው ከሚግበሰበሱት አንዷ ነች ። እውነትም የኑሯቸው ደረጃ ሲነጻጸር ከትልቅ ዳመራ አጠገብ የምትበራ ስንጥር ትመስላለች ። ታዲያ እንዴት ይዩዋት ?

"እውነትክን ነው ልጄ ፤ እኔ ለያውስ ምኑን ዐውቄው! ይኸነዩኮ ደህና ሰው ይሆኑ ይሆናል" ብላ ምንዳዬን ላለማስከፋት ንግግሯን ጠገነችው ።

"በሉ ሌላ ጨዋታ እንጫወትበት ፣ እኛ ስለነሱ እናወራለኒ ፣ እነሱ ከጆሯቸውም ጥፈውን ዐያቁ" ብሎ ቸርነት እየሣቀ አሣቃቸው ።

መዓዱ እንደ ተነሣ "ያንን ነገር ላምጣው እንዴ ?" አለች ልኬለሽ ቸርነትን እያየች ።

"የቱን?" አላት እየጠረጠረ ።

"ያንን ነዋ! ያንን ቅድም የሰጠኸኝን ።"

"ምን ነካሽ ? ደህናም ሰው አልነበርሽ እንዴ ? ምን ነበር የተባባልነው ?" አላት በመገረም ።

"አይ ያንተ ነገር ! ምን እንዳይል ብለህ ነው ? ከሆነ አይቀር ሁላችንንም ደስ ይበለን ።"

"ጤናም አልያዛት እንዴ ? በይ ልሒድልሽ እቴ ! ባልና ሚስት
ታንድ ምንድን ነበር ይቀዳል እሚሉት ? — — ያሏትን ትታ ያላ
ኟትን" ብሎ ብድግ አለ ።

"ካንድ ወንዝ ይቀዳል ነው ። መቼም ያለኔ አይሆንልህ" ብሎ
ጣልቃ ገባና ፣ "ምንድነው ነገሩ? ለኔ ንገሩኝና ልገላግላችሁ ። ባይሆን
የዳኝነቱን ትከፍላላችሁ ።"

"ማ ቢያቀምስህ? የምን ጠጋ—ጠጋ ነው — — — እኔና እሱ
እንተዋወአለን!" ብላ ቸርነትን ጉትታ አስቀመጠችው ። እንደ ቆመ
ችም ፣ "ጥሩ ነገር በማድረግህ ምን አስፈራህ? እንዲያውም ባንተ እጅ
ያምራል ። እኔ በናንተ መኻል ምን ዶለኝ ።"

"ምንድነው ነገሩ? ይኸንዬ እኮ አርቲ—ቡርቲ ይሆናል — —"

"መስሎሃል? ምንም ይሁን ምን ፣ ምን አስቸኮለህ? — — ቀስ
ብለን ኮርተን" አለች እየሣቀች ።

"እይ ያንቺ ነገር! ደሞ አደራሽን ስል መዋሌ ። ለዚህ—ለዚ
ህማ ምን አለፋፋኝ" አለ ቸርነት ።

"እንዲያውም አልሰማ! ለምናችሁ ትነግሩኝ የለ! — — ያለኔ
አይሆንላችሁ" ብሎ ምንዳዬ ሣቀ ።

"እንዴት ተጎዳን እቴ? አንተ አልሰማ አልክና ጉዳያችን አይነ
ቅዝ ፣ እኛም ሳናስደገድግ አንነግር" አለችው ።

"ታዲያ ምን ልበል? እንዳንዳንደዬው የነቀኛማይ ወሬ ነገራች
ሁን ጥፍትፍት ስታረጉት ፣ አቄላችሁኝኮ!"

"ይልቅዬ ቀልድህን ትተህ ፣ የምነግርህን እህ በልና —— እሺ
በለኝ!"

"ብያለኋ! ያለኔ አይሆንላችሁ ። ለእሺውም ፣ ለእምቢውም እስቲ
መጀመሪያ ይሰማ ነገሩ?"

"እምቢ ብሎ ነገርማ የታል? እማይባለውን! ለዚያውም ቢሆን
በመጀመሪያ ልኬለሽ ሙች ብለህልኝ ነው ። እንዲህ በዋዛ እንላቀቅ
መስሎሃል!" ስትል ቸርነት ቀና ብሎ አያት ።

"ወይ ጣጣዬ! ነገሩን ሳላኸው ፣ ሙችና አትሙቺን ምን አመ
ጣው?"

"ነገሩማ ይነገርሃል — — — የት ይቀራል ።"



"አንቱል አስምለሽኝ የማይሆን ነገር ተሆነስ? ይኸን እያስማሉ
መንገር ተውኝ አላልኩምይ!"

"እዬ! ምነው በቁሜ ገበያ ባታወርዱኝ ። አሁን ማ ይሙት
ቸርነት ቢጠይቅህ እምቢ ትለዋለህ?" አለች ኮስተር ብላ ።

"እሱ'ስ እውነሽን ነው እምቢ አልለውም ። ታዲያ እምቢ አይ
ልም እያላችሁ እንደ ሞኝ — — —"

"እኛ ሞኝ ነህ አላልንም! ያውም አንተን! ምን ቅብጥ ቢያረገን!
ይልቅዬ በይ ሙች በልና ይነገርህ ። ቀላል መስሎታል!"

"ግድየለሽም ስልሽ!"

"እይይይ! ምንድነው እቴ ምንችክ ማለት!"

"በይ ደስ ይበልሽ! እላለሁ ።"

"እላለሁ ከማለት አትለውም?"

"ልኬ ሙች!" አላት በቁም ነገር እየሣቀ ።

የቸርነት ልብ በደስታ ተከብባ ነፍሱ ተነፈሰች ።

"እንግዲያውማ ቸርነት እንዲህ አረገልህ — —" ከማለቷ ሁለ
ቱም ትኩር ብለው አዩዋት ።

"ምን አረገ ልጄ?" አላት ቶሎ ብሎ ።

"ከሰውዬው ጋ አዲሳባ ልትሔድ ነው ማለትን ተሰማ ጀምሮ
አብሶ ይኸን ሰሞን ግራ ግብት ብሎታል ። ሰማይ መሬቱ ድፍት እሚ
ልበት ነው የመሰለው ። ከኔ ብሶልሃል ። ዛሬ ሳያመው የውሸቱን እመ
መኝ ይልልህና ያቺኑ ጤፍና ቀጠሮውን (ማሽላ) ሸጥ አርጎ ፣ ለምንዳ
ስጪልኝ — — —" ብላ ንግግሯን ሳትጨርስ እንባዋ ዠርግፍ አለ ።
ቸርነት አቀረቀረ ።

"ተቀበልሽው እንዴ ?" አለ አሻቅቦ እያየ በዝግ ገጽታ ።

"እሱንማ ልነግርህ አደል? አይሆንም ብዬ ብለው ብሠራው ፣
እምቢ አለኝ ። እምቢ ሲለኝ ምን ላርግ ትለኛለህ ?" ብላ ወደ ጓዳ
ስትገባ ሁለቱም ባይናቸው ተከተሏት ። እንደ ተመለሰችም ምንዳዬ
ሳያስበው የተጠቀለለውን ገንዘብ አስጨበጠችው ። ደነገጠ ። ቀለላት ።

ምንዳዬ በሐሳብ ፣ ቸርነት በደስታ ተዋጡ ።

“ምነው እንዲህ ማረግህ ቸሩ? አ—አ—አ—ሁን ይኸ እሚገባ ነገር ነው?”

“የጂ ማጠር ነውዴ እንዲህም አልነበር — ድህነቱ በየቲ — — እንዳሳቤማ — — —” ብሎ ራሱን ነቀነቀ ።

“ኧረ አጨናነቁን ባየኸው !” ብላ ዐይኗን በጅጌዋ አበሰችው ።

“ምን አስጨነቀው ? አርጉልኝ ዋሉልኝ የሚል የሩቅ ሰው ሲሆን ነው ።”

“የሌላ መሰለህ ? አነሰች ብሎ ሠግቶ ነውዴ ከ(ፊ)ታውን ነውዴ ማየት !” ብላ ከነእንባዋ ፈካ አለች ።

“መች አጣሁት ! ለምን አንዲት እፍኝ አተር አትሆንም ?” ብሎ አክብሮቱን በፈገግታ ገለጸ ። ሦስቱም ተያዩ ። የመንፈሳቸው አንድነት የፊታቸውን ጸዳል አደመቀው ። እናም የደስታ ዝምታ ዝም አሉ ።

“ለኔስ ምን ታረግልኛለህ ? እሱ በለጠብህ ማለት ነው ? ታዘብ ኩህ!” አለችው እየሣቀች ።

“ምን ላርግልሽ ? ዐፈር ስሆን ንገሪኝ ልኬ ?” አለ ቸርነት ከልቡ ።

“ኧረ እኔ የቀልዶዬን ነው ! — ሆ !”

“የሱን—የሱን ነገር ታሰላስል ፣ አንቺን — — —” ከማለቱ ፣

“ከተማ ይሙት ! አንተ እኮ የምርህን ይሆናል ። ያው ምያለሁ።”

“እይ እኔ አንቺን ብሆን” አለ ምንዳዬ ።

“ግድ የለህም —እንኳንም እኔን አልሆንክ!”

“የቀረብሽ አንቺ! እኔ ምን አሻኝ! — ” ብሎ ሲሥቅ ፣ እነርሱም ሣቁ ።

“ይልቅዬ የዚያን የርሻውን ነገር ንገረው” አለች ሳያስቡት ።

“ምን አሉ ?” አለ ቸርነት ።

“ኧረ ምንም ያሉት ነገር የለም ።”

“ምኑን ነው ታዲያ እሚነግረኝ ?”

“ከትላንት ወዲያ ማታ ተጠርቼ ሔድኩልህ” አለ ምንዳዬ ። “ራት ቀርቦልኝ በላሁና ቅራሪ ቢጤ ስጠጣ ፣ ‘በያ ሰሞን እንደ ነገርኩህ ከኔ ጋ አዲሳባ ትሔዳለህና ታሁኑ ተዘገጃጅ ፣ ቤትህን በወጉ በወጉ አርግ፣ ሁነኛ ሰው ፈልግና እርሻህን አሳርስ ። ቀላል መሬት አይምሰልህ ። እግርህን ስመው ነው እሚለምኑህ ፣ ስንቱ መሰለህ ይጭረው ያጣ’ ሲሉኝ ጊዜ ብድግ ብዬ ጉልበት ስሜ ወደ ቤቴ መጣሁ እልሃለሁ ። እስቲ ጥሩ ገበሬ ማነው ? ማ ይሻል ይመስልሃል ?” ብሎ ትክ ብሎ እያዬው ።

“የምን ገበሬ ልጂ ? ምን ይሆንህ ?”

“እንዴት ነው ፣ ምን ይሆንህ ብሎ ነገር ! ዐፈር እየተዘገነ አይቃም ።”

“ሌላውን እላለሁዴ ፣ አንዳንድዬስ አንተም አንፍር ነህ ! ምን ዐመል ነው ወንድሜ ! ኤ — ድ ! ምንድነው እንዲህ ያለ ነገር !” አለ ቸርነት በከረረ ድምፅ ።

“ምን አጠፋሁ ቸሩ?”

“ምን አጠፋሁ? እኔ ምን ሆኜ ነው ሌላ ሰው ማስፈለጉ?”

“ኧረ ንሱ ሰዎች! አሁንስ አበዛኸው! ደሞ ብዬ — ብዬ አንተን! ‘በቅሎ ቲሸለም ጊዜ አህያውን ለጅብ ሰጠ’ ያሉት ሰውዬ ቢጤ መጣ — — አዲሳባ ልውሰድህ የተባልኩ እንደሁ — — አንተን — —” ብሎ ሳይጨርስ ፣

“ቸርነት እርሻ አይችልም ያለህ ማነው?” አለ ቆጣ ብሎ ።

“ተውይ ቸርነት —— እኔና አንተኮ — እንዴት ነው ነገሩ ?” ብሎ መላ—ቅጡ ጠፋው ።

ቸርነት ድንገት ቆመና ፣ “ይኸ ሰው እውነትም ጤናም አልያዘው ፣ ገለል ቲልለት ጥሪኝ” ብሎ ራመድ ሲል ፣ እዚያው የቆመችው ልኬለሽ ቀኝ እጁን ያዘችው ። ምንዳዬም ቆመ ።

“እኮ ምን አርግ ነው እምትለኝ? ምን አጠፋሁ?” አለ ምንዳዬ በለ ዘብታ ።

“አሁን ገና ጥሩ ብለሃል! እየው ገለል ቲልልህ! እጐንህ ተወዝፌ ጥላ ሁኜብህ ኖሯል ለካ! መቼም ብልህ ሰው የቆለ ለት አያድርስ ነው! እኔ ምን ሆኜ? እኔ የት ሔጄ ነው ሰው ማስፈለጉ? ኧረ ምን ስታረግ አሰብከው — —” ብሎ ዝም ሲል ፣ ያም ዝም ስላለው ፣

“ነገሬም አልጣመህ መሰል! — — አቦ ልቀቂኝ ልሒድበት!” ብሎ እጁን ሲስብ ፣

“እስቲ ና ቁጭ እንበልና ንገረኝ?” አለ ምንዳዬ እንገቱን ዘለስ አድርጎ ።

“ምኑን ልንገርህ? ለኔ እሚነገረውን ለሌላ ልንገር ስትል!”

“እስቲ አንዳፍታ ቁጭ በሉና ተነጋገሩ ። እሱም እንዳንተ ፈርቶ ነው ። ምነው እንደ ራስህ ብታየው” አለች ልኬለሽ ለማቀራረብ ።

“አንቺ ደሞ አታለባብሽለት ። የኔ ፍሪያት ሌላ ፣ ይሽ ሌላ ፣ እስቲ በይ ምንና ምኑ ይገናኛል? እኔ እንደናቴ ልጅ ሳየው እማደል ፣ እሱ እንደባዳ ያራቀኝ፣ አለያማ መች ሌላ ሰው ፈልግልኝ ይል ነበር? ሰው ተሚያምነው ባልንጀራው ምስጢሩን አይደብእም ። እኔ እያለሁ አን ቺና ልጆቹ ጠማችሁን አታድሩ፤ እምቢ ይለኛል ብሎ ነው ሰው ማፈ ላለጉ ።”

“ቦጋለ ይሙት! ገና አሁን ነው ነገሩ የገባኝ! ፍቅርህን! እኔ ልሙትልህ ። ለምን ግልጥልጥ አርገህ አትነግረኝም ። ጥቅሙ ለማን ሆነና ነው፣ እሺ አንተ ባልክ ይሁን” አለና ከልኬለሽ ጋ ወደ መቀ መጫው መለሰው ።

ቸርነት ሐሳቡን እጥር—ምጥን አድርጎ ገለጸለት ። ሣቀችባቸው ።

“ደስም አላለህ እንዴ?” አለው ቸርነት እየሣቀ ።

“እንዴት ብዬ ልንገርህ፣ የኛ የሰውዬ ተረት ትዝ ይልሃል?”

“የየቱ?”

“የሚኻእል ለት ማታ እኔና አንተን ያጫወቱን ።”

“እእእ! እባ ወርቅነህ ናቸዋ! ምን ብለው ነበር፣ ረሳሁት እኮ!”

“ሰውዬው አሉ ፣ አህያና በሬውን እየነዳ ተዱር ወደ ቤቱ ቲመ ለስ ፣ አፋፍ ላይ ይደርሳል አሉ ። በሬው ድንገት ይንሸራተትና ገደል መግባት ። ቁቂታውን ያቀልጠዋል ። ሰዎች ከያሉበት ተሯሩጠው ይደ ርሱና ፣ እንደ ምንም ተንፏቀው ወርደው ፣ ያንን ቲያጣጥር ያገኙትን በሬ ይባርኩታል ። ገፋፈው የቻሉትን ያህል ይበሉና ፣ የተቀረውን ቆራርጠው ፣ ታቹን በሚዳው ዞረው ያንን ያዋጡትን ሥጋ በበሬው ቆዳ ጠእለው አህያው ላይ ያጫጭኑታል ። መሽቶ ወርወር ሲል ፣ እቤቱ ሊደርስ ጥኢት ሲቀረው ፣ ወገቤን ልፈትሽ ይልና አህያዋ እየ ሔደች ከምንገድ ዳር ገለል ይላል ። ለካ የራበው ጅብ ገና ከጉሬው ወጥቶ ሱክ—ሱክ ይል ኖሮ ፣ አህያዋን ስታዘግም ያያታል ። ጠጋ ብሎ ሲመለከታት በቆዳ የተጠቀለለ ሥጋ ተጭናለች ። የልቡን ሲያገኝ ጊዜ



‘አንቺዬ! እንዲያው ለመሆኑ አሁን እንቺን ማ ብለው ይጠሩሻል፣ አንቺው ራስሽ ሥጋ ፣ የተጫንሽውም ሥጋ ፣ ተባረኪ! እሰዬው እሰይ!’ አላት አሉ” ብሎ ከት አለ ።

“እና የዚች ፍቺዋ ምን መሆኗ ነው?”

“እእ! እዩልኝ እንግዲህ! የልቤን የምኞቴን አገኘሁ ነዋ! ምን ቅሬታ አለ ፣ ሁለመናው አማረ ነዋ! አንተ እኔ አለሁ ስትለኝ ከዚህ ወዲያ ምን ይገኛል፣ አርሶ እሚያመርተው ቸሬ፣— ተቀባይዋ ልኬ ። ተየህ ወዲያ ምን ይምጣ?” አለው ፊቱ በፈገግታ ተጥለቅልቆ ።

# ምዕራፍ ሠላሳ አምስት

ቀኛዝማች ፣ ከበሬቱ የበለጠ ግዝ አዘጋጅተዋል ። በነጭ ጤፍ የተቆ
ሉት ስልቻዎች ፣ አዳራሹ ውስጥ ተደራርበውና ተደጋግፈው እንደ
ትላልቅ የቤተ—ክስያን ከበሮ ተጋድመዋል ። በገዛ አህያውና አጋሰሱ
ጭኖ ማጀቱ ለማድረስና እጅቦ ለመሸኘት የተዘጋጀው ዘመድና ባላ
የሚነሡበትን ሰዓት ይጠባበቃል ። ጥር 29 ቀን ማጀቱ ወርዶው ፣ በማ
ግሥቱ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ መሰናዷቸው ተጠናቋል ።

አስካዳች ጠላ ጠምቃና ጋኗን መርጋ ፣ ልበ—ወርቅ ሲካካ ዶሮ
ዋን አዘጋጅታና ቢላዋዋን ስላ የምትጠባበቀው የቀኛዝማችን መሔድ
ነው ። ዘግይተውባታል ።

የወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ቅናት ፣ ስርጓጉጥና ሽለቆውን ፣ ገመገምና
ተራራውን አቋራርጦ ፣ ከወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ጋር የተለመደ ትንቅንቁን
ቀጥሏል ። የምንዳዬንም ጉዞ እየፈሩ እንደሚወዱት ፣ እየጠሉ እንደሚ
መርቁት ጠላት ፣ ሳይወዱ በግድ ተቀብለውታል ። ቸርነትና ልኬለሽ
በሬው በሰኔ ገደል እንደ ገባበት ገበሬ ኩምትር ብለዋል ። ምንዳዬ
ውስጡ ቢንሰፈሰፍም ላይ—ላዩን ብርቱ መስሏል ።

ደስታና ሐዘን ፣ ልቅሶና እልልታ ፣ ፍቅርና ጥላቻ — በእያንዳ
ንዱ ሰው ግላዊና ማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ፣ ሰው ራሱን ለመከላከልና
ለማዳን ፣ ኑሮውን ለማመቻቸትና ከመሰሎቹ ጋር ተስተካክሎ ወይም
ልቆ ለመታየት በሚያደርገው ውጣ—ውረድ የሚያጋጥሙ የኑሮ ባሕ
ሪዎች በመሆናቸው ሁሉም በዚያ ጉዳና ላይ ያልፋል ።

በቀኛዝማች ግቢና በአካባቢው የሚገኙ ሰዎች ፣ በተለያየ ስሜ
ትና ሥጋት ፣ ተስፋና ትካዜ የሚጠባበቋት ቀን ፣ ላንዳንዶቹ ፈጥና ፣
ለሌሎቹ አዝግማ ደረሰች ። የምንዳዬም ስንቅ በሁለት ከረጢት ተቋጠረ ።

እነ ቀኛዝማች ፣ በቅቤ የተንጨቀጨቀ ዶሮ ወጣቸውን ፣ ጥሬ ቢጫ (?)
ሰለ የጤፍ እንጀራ እያሸበለበሉ ፣ ሲላቸው በነጭ አረቄ ፣ አልያም (?)
በጠላ እያወራረዱ ሲውጡ ፣ ልኬለሽ ፣ ምንዳዬና ቸርነትም ፣ የቅመም (?)
ዓይነት ያላነሳትና የቅቤዋ ሽታ ከደጃፍ ያላለፈ የዶሮ ወጣቸውን (?)
የለቱ—ለት በተጋገረ የማሽላ እንጀራ በልተው ሙግ—ሙግ የሚል (?)
ጠላቸውን ሲጠጡ ዋሉ ።

ፀሐይዋ ዘቅዘቅ ፣ አየሩ በረድ እንደ ማለት ሲል ፣ የቀኛዝማች ጓዝ ተጭኖ መንገድ ገባ ። ወዲያው ሸኚና አጃቢው ሁሉ ከያለበት ተሰበሰበ። ልኬለሽ ገና አሁን ቁርጧን ያወቀች ይመስል በረዥሙ ተነፈሰች ። ልወደድ ባይና ዘመድ ፣ ኑሮ የፊጥኝ ያሰረው ተጋዥ ገበሬና ሎሌ ፣ በተለይም ዋና ቤተኛ ልምሰል ባዩ ፣ እነ ቀኛዝማች የሚቀመጡባቸውን በቅሎዎች እየሳበ ፣ ሌላው አጃቢ ጠበንጃውን ይዞ ካጥር ውጭ መደዳውን ተገጠገጠ ። እነርሱም ረጋና—ኮራ ባለ አረማመድ እያወሩ ዋናውን አጥር እንዳለፉ ፣ ምንዳዬም ጠበንጃውን አንግቶ ፣ ቸርነትን ፣ ልኬለሽንና ልጆቹን አስከትሎ ከጕጆው ብቅ አለ ።

ልኬለሽ ፣ የቤቷን በር ስትዘጋ የእንባዋ በር ተከፈተ ። ማንም ልብ አላላት ። ሁለቱ ሰዎች በቅሎዎቻቸው ላይ እንደወጡ ፣ ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱና አንዳንድ ሰዎች እየተሰናበቱ ተመለሱ ። ሌላው ከበቅሎ ፊትና ኋላ እየሆነ መንገድ ገባ ።

ልኬለሽ ፣ ልጆቿን አስከትላ ጥቂት እንደ ተጓዘች ፣ ምንዳዬ ክንዷን ያዝ አደረገና ፣ "በይ ተመለሺ ። ለልቅሶና ለእንቅፋቱ ከሆነ ይበቃል!"

"ማን ሆ! እኔ ነኝ ተመላሿ? ምነው በል ፣ ምንስ ቢሆን መኪና ላይ መውጣትህንና ከሳቸው ጋ በደህና ምንገድ መግባትህን ባይኔ ሳላይ ነው ፣ ነፍሴ በጇ ብላኝ እምመለሰው? እንቅፋትም አይመታኝ ፣ ራመድ—ራመድ እላለሁ ። ለልቅሶውም አታስብ ። እንዲህ ልኩን ሳቀው እርፍ እል የለ? ግድየለህም አታስብ ፣ ይልቅ ሒድ እንሒድ!"

"ቤቱን ለማን ትተሽው? ልጆቹስ?"

"እኛም አብረን እንሔዳለን ፣ አይደኸ፣መንም" አለ ትንሹ ያባቱን እጅ እያሻሸ ።

"በሉ ኑ እንሒድ ፣ መንገዱስ ምንም አደል?" አለ ቁርጡን ዐውቆ።

ቸርነት የመለየት ስሜት አፉን ሸብቦት ፣ የምንዳዬን ስንቅ አንጠልጥሎ ይከተላል ። ከነሱ ኋላ ሌላ ሰው አልነበረም ።

ጥቂት እንደ ተጓዙ ፣ ምንዳዬ ትንሹን ልጁን እንኮኮ አለው ። መንገዱ ሳይታወቃቸውና የሔዱ ሳይመስላቸው ማጀቴ ደረሱ ። በመጀመሪያ ሁሉም ቀኛዝማች ከገቡበት የዘመድ ቤት ገብቶ ዐረፈ ። የማታ ማታም ወደየዘመዱና ወደየሚያውቀው ሰው ቤት ሲበተን ፣ ምንዳዬም ከጓደኛው ጋር የሚያድርበትን ቦታ ነግሮ አስፈቀደ ። ልኬለሽ ልጆቿን ፣ ምንዳዬንና ቸርነትን ይዛ ማጀቴ ዶር — አምባ ከሚኖሩት ዘመዷ ቤት ገባች ። ጥሩ መስተንግዶ ተደርጎላቸው



ሲያወሩና ሲያወኩ ሌሊቱ ተጋመሰ ። ለሁለቱ ወንዶች አልጋ ተለቀላቸው ፣ ልኬለሽ ከነልጆቿ ጀንዲ ተነጥፎላት ከባለቤቲቱ ጋር ወለሉ ላይ ተኙ ።

ዶሮ ደጋግሞ እንደ ጮኸ ሴቶቹ ተነሥተው ፣ ባለቤትዮዋ ምጣድ፣ ልኬለሽ ድስት ጥደው ሲጣደፉ ወፍ ተንጫጫ ። ወገግ እንዳለ እነ ምንዳዬ ፊታቸውን ታጠቡ ። ካማን አውለኛቸው በኋላ ፣ ምንዳዬ ፣ ልኬለሽንና ቸርነትን ይዞ ወደ ጓሮ ዞረ ። ጠበንጃውን ባፈሙዙ ጨብጦ በእሱና በጓደኛው መኻል በሰደፉ ካቆመው በኋላ ፣ "ቸርነት" አለው ልብ በሚመስጥ ድምፅ ። "እንግዲህ የልኬንና የነአሻጋሪን ነገር አደራ! እኔ ብሔድ አንተ አለህ ። አንተ ካለህ ደሞ እኔ ያለሁ ያክል ነው ። ልጆቹን እንዳያስለቅሷቸው ። እሷንም እሱ ተሔደ ብለው እንዳያንከላፍቷት — አደራህን" ብሎ ዝም አለና ፣ "አንተም እንካ ይኸን ቀኝ እጄን ፣ ጠበንጃዬን ። ወንድም የለኝም ወንድሜ ነው እንካ!" ብሎ በሁለት እጁ ሰጠው ።

ልኬለሽ ፣ ይሆናል ብላ ያልጠበቀችው ጉዳይ ቢሆንም ፣ የባለቤቷ ጠበንጃ ፣ እሷም ለምታምነውና እሱም ለሚወደው ባልንጀራው በመስጠቱ ምንዳዬ በከፊል አብሯቸው የቀረ ስለ መሰላት በጣም ደስ አላት። ቸርነት በጠበንጃው ሳይሆን በጓደኛው እምነትና ፍቅር ተመሰጠ ። የሚናገረው ጠፍቶት ዝም ሲል ዐይኖቹ እንባ ከተቱ ። ከቃላት የላቀ መልስ ነበር ። እየተለያዩ መዋሐጃ ፣ እየተዋሐዱ መኀልበቻ ።

"አታስብ ፣ እኔ እያለሁ ማባቱ ይነኻቸዋል ? —— አታስብ! አሁንማ ቀኝ እጅህን ወንድምህን ትተህልኛል ፣ ሁለዜም አብረኸኝ ነህ" ብሎ እንባውን ለማበስ ፊቱን አዞረ ። ምንዳዬ አንገቱን ሰበር ሲያደርግ ፣ የልኬለሽ ዐይን የእንባ ቦዩን ቀደደ ።

የአውቶቡሱ ጥሩንባ ፣ መንገደኞችን ለመቀስቀስ በተከታታይ ተነፋ ። ልኬለሽ ልጆቿን አስነሥታ አንድ ሁለትዬ አጕረሰቻቸውና አውቶቡሱ ወደ ነበረበት ገሠገሡ ። በመኪናው ዙሪያ ከተሰበሰቡት ሰዎች አንዳንዶቹ የሚጫን ዕቃ ወደ ላይ ሲያቀብሉ ፣ ሌሎቹ ኮተታቸውን እየቋጠሩ ፣ ካንዱ ወደ ሌላው እያጋቡ ያመቻቻሉ ።

ሞተሩ ተለኩሶ ፣ ጢሱ ቡልቅ—ቡልቅ ሲል ፣ መላ ብረታም አካሉ ተንዘፈዘፈ ። እነ ቀኛዝማች ወደ አውቶቡሱ ሲጠጉ ፣ አብዛኛው ሰው ገለል አለላቸው ። ምንዳዬና ቸርነት ጠጋ ብለው እጅ ነሡ ።

"ጥሩ ደርሰሃል ፣ እንግዲህ ነቃ—ነቃ ማለት ነው" ብለው ወደ አቶ ወርቅነህ ዘወር ሲሉ ፣ እነሱም ወደ ልኬለሽ መለስ አሉ ። ሊለያዩ ተያዩ ። አንዳንድ ሰዎች ወደ አውቶቡሱ መግባት ሲጀምሩ ፣

ምንዳዬ ልጆቹን አገላብጦ ሳመና ፥ "አንተ ካለህ ምንም አሳብና ሥጋት የለብኝ" ብሎ ቸርነትንም ሳመው ። እንባዋ አልገታ ያላትን ልኬለሽን ፥ ቀኝ እጅዋን ያዝ አድርጎ ፥ "እኮ በቃሽ ልኬ ! ምነው ምነው ነግሬሽ እያለቀሽ አትሸኝኝ ደግም አዶል !" ብሎ አገላብጦ ሲስማት ፥ እንባቸው ጉንጫቸው ላይ ተቀላቀለ ። ቸርነት ግን ፈዘዘ ።

እነ ቀኛዝማች ፥ ከሾፌሩ አጠገብ ካሉት ጥንድ ወንበሮች ላይ ሲቀመጡ ፥ ምንዳዬ ወደ መጨረሻው መደዳ ሒዶ ጠባብ አልጋ መሰል ወንበር ላይ በስተግራ ጥግ ካሉት ሰዎች ጋር ተቀመጠ ። እሱ በዝግ መስተዋት በኩል ወደ ውጪ ፥ ልኬለሽ ፥ ቸርነትና እነአሻጋሪ ከውጪ ቆመው ሲተያዩ ፥ መኪናው አጓርቶ ጎማዎቹ ተንከባለሉ ። መለያየትና መነፋፈቅ ተወጠነ ። አውቶቡሱ በኮረኮንቻማው መንገድ ላይ ደፋ ቀና እያለና አቧራውን እያቦለለ ቁልቁል ተሽከረከረ ። ቸርነት ፥ ልኬለሽና ልጆቹ ባቧራው ብናኝ ውስጥ እየራቀና እያነሰ የሚጓዘውን ተሽከርካሪ ባይናቸው እየተከተሉ ሲሸኙት ፥ ምንዳዬም የኋልዮሽ ሲመለከት፥ ከዚህም ከዚያም የእንባ ውሃ ሻሽና የአቧራ ብናኝ ተዘርግቶ ፥ የጭጋግ ግርዶሽ ፈጠረ ።



## ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት

የሞገስ እምባቸውና የላቀች ተገኜ ጋብቻ ጉዳይ ቀነ—ቀጠሮ የተያዘለት ቢሆንም ፥ ሞገስ የምኞቱን ፍሬ ጨብጦ ወደ ቤቱ እስከሚገባና ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑም የቀጠሮው ቀን ደርሶ እስከሚያስረክቡት ድረስ ፥ ገባ—ወጣውና የመጢቃቀሙ ነገር በሰፊው ቀጥሎ ሰነበተ ። እሱም ቢሆን ነፍሱ ተደስታ ተስፋው የምትፈካው ፥ ባካባቢዋ ተገኝቶ ሲያያት ነበር ። በፍቅሯ ተይዞ መመላለሱ እንዳይታወቅበት ልዩ ልዩ ጥረት ቢያደርግም ፥ የገጽታው መለዋወጥ ፥ የዐይኑ መንከራተት ፥ የቀልቡ መሸፈትና ፥ "መጣሁ" እያለ ወደ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ቤት ጐራ የማለቱ ነገር ፥ "ይቺ ባላገርኮ በፍቅር አናወዘችው" የሚለውን የቤተሰቡን ወሬ አጠናከረው እንጂ ፥ እንዳሰበው ሊሸፈንለትስ አልቻለም ።

አንድ ቀን ላቀች ከተገዛላት ልብስ መኻል ፥ ደማቅ ሰማያዊ ቀሚስና ቢጫ ሹራብ ለብሳ ፥ ነጭ ተረከዝ አጭር ጫማ አድርጋ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ፊት ስትቆም ፥ ባለባበስና በወጣትነቷ እየቀኑ ፈገግ አሉና ፥ "ተዋል አደር ደሞ ስንትና ስንት አለ — — —ገና ሙያሽንና ጣምናሽን ታያቀው ይኸን ያክል የሆነ —— ሰንበትበት ብሎማ እጁ የዶለሸለት —— ኧረ ተይኝ እቴ" አሉ እየሣቁ ።

የልቧን በልቧ ይዛ ፥ "እኔ እኮ ታዲያ ቲመላለስ ፥ ተምሩም አልመሰለኝ ፥ እስተዚህም ነገሬ አላልኩት ነበር ። 'የከተማ ወንዶች ውል የላቸውም ፥ መላ—ቢሶች ናቸው' ሲሉ እየሰማሁ ካንገት በላይ ይመሰለኝ ነበር ። ለካ ውለኛ ሰውም አለባቸው" አለች ኮስተር ብላ ።

"ይኸ ሁላ ሰው እየሁ የተወለደ መሰለሽ? ከስንት አንድ ነው ። አሁን ይኸ እምታዪው ሞገስ ለዚህ ሁሉ ወግና ማረግ የበቃው እዚሁ ተወልዶና አድጎ አይምሰልሽ! እኚህ ያጐቴ ሚስት የቡልጋ ሴት ናቸው። የዚህ የሞገስ አባት እንዴት ያሉ ዘመድ ወዳድ ፥ ቸር ነበሩ አሉ ። ያባትዬው ውለታ አልፎባቸው ኖሮ ፥ ልጅዬው አድጎ ትልእ ልጅ ተሆነ በኋላ ፥ አንዳንድ ልጆች ተማሪ ቤት እየገቡ ቲስተማሩ ያይልሽና ፥ እረኝነቱን እምቢ ማለት ። ቀን ይውጣላህ ቲለው ። አንድ ጊዜ ያቺ ማደሪያው ተላይ—ተጌታ ተጥፋ የለ! ተማሪ ቤት መግባት ። ሴትዮዋ ታዲያ ይማራልን ሲሰሙልሽ ጊዜ ተደብረ ብርሃን ያስመጡና እዚህ አዲሳባ ማንትስ አሉት እቴ— —ተማሪ ቤት ይዶሉታል ። ያገር ቤት

ልጅ መሞላፈጥ መዘተል አያቅም፣ ትምህርቱን ቶሎ ቶሎ ይማር ይፈጥምና ማለፊያ የምግሥት ሥራ ይይዛል ። እየሁ ቤት፣ እነሱው ጋ ነው ለሰውነት የበቃው ። እንዲህ እንደልቡ ወጣ—ገባ የሚለው፣ ከልጆቻቸው እኩል በልቶ፣ የለበሷትን ለብሶ በማደጉ ነው ። ይኸው ትታዘቢያለሽ፣ ሌላማ ማ ዝር ይላል፤ በያ ላይ ደሞ ይኸ የኔ አጐት እንዲህ አይምሰልሽ፤ ትዳር ነው ደጉ ነገር ይልና፣ እጪዋ ቤት ገብቶ ማለፊያ ትዳር ያሲዘዋል ። የህል—ውሃ ነገር ሆኖ ቃይሆንለት ቀርቶ ነውዪ፣ ቃንዴም ሁለቴ ጉልቻ ሞክሯል አሉ” በማለት ስለ ሞገስ ከሰሙት መካከል በከፊል ነገሯት ።

ከሦስትና ከአራት ጊዜ በላይ እያገቡ የሚፋቱ ወንዶችና ሴቶች ስለምታውቅ፣ ሁለተኛ አግብቶ መፍታቱ አላስደነቃትም ።

* * *

ሞገስ አምባቸው፣ በ14 ዓመቱ ትምህርት ጀምሮ እስከ 8ኛ ክፍል የነበረውን ትምህርት በ5 ዓመት አጠናቆ 10ኛ ክፍል እንደ ደረሰ፣ ካባቱ ሞት በኋላ ሀብታቸው እየሚሰሰና ንብረታቸው እያነሰ የሔደውን እናቱን እንዲረዳ በማሰብ፣ በአቶ ወርቅነህ መዘውር ግፊትና ይሁን—ይሁን ባይነት፣ አገር ግዛት ሚኒስቴር ተቀጥሮ መሥራት ከጀመረ ከ10 ዓመታት በላይ ሆኖታል ። ከአዲስ አበባ የመኖሪያው አካባቢና ከት/ቤት ጓደኞቹ ቀስ በቀስ በቀሰመው ጠባይ፣ የቀድሞ ግትር ባሕሪው፣ ከጊዜ—ወደጊዜ እየተሞረደ፣ ከአሻፈረኝ ወደ “እስኪ ይሁን” ባይነት፣ ከዚያም ወደ መጠነኛ መግባባትና ብልጠት አመራ። ከአቶ ወርቅነህ መዘውርም መስሎ የማደርንና እስኪደላደሉም ጐንበስ ቀና እያለ ማድፈጥን፣ ሁኔታው ተስተካክሎ ሲቃናም ተደላድሎ መቆምን ዐወቀ ። ያም ሆኖ ከፊል ድብቅ ባሕሪው ድንነት እየደፈረሰ ዐልፎ—ዐልፎ ያስቸግረዋል ።

ሥራ የጀመረው አዲስ አበባ ቢሆንም፣ በዝውውር አሩሲ ጠቅላይ ግዛት ሁለት ዓመት ሠርቶ ሲመለስ፣ ከተሰጠው የምስጋናና የትጋት መግለጫ ደብዳቤ ሌላ፣ በልዩ ልዩ የአስተዳደርና የአፈጻጸም ሰበቦች ያገኘውን ብር አጭቆ ነበር ። ከዚያ መልስ አቶ ወርቅነህ መዘውር ቤት ላንድ ዓመት ያህል እንደ ተቀመጠ፣ በወ/ሮ መንበረ አጠያያቂነትና በባልዩው አቀነባባሪነት፣ እሱም እጁ እንደቻለ ሰጥቶ ለወግ ለማዕርግ በቃ ።

አንድ ዓመት በወረተኛ ፍቅር፣ ሁለት ዓመት በንዝንዝ እንዳለፈ፣ የትዳሩ መሠረት ተናግቶ ምሰሶው ዘመመ ። በሽማግሌ ምክርና ተግሣፅም አልሆን አለ ። ሚስቱ “ይኸ አይገባውም ሥልጡን መሳይ ባላገር ነው ። እኔ አንድ ነገር ብሆን የኋላ ኋላ ይቆጫችኋል ። አይሆንም እያልኳችሁ ነው፣ ዝም—በይ ዝም—በይ ብላችሁ ለዚህ ያበቃችሁኝ” በማለት ቀጭን ጌታ ነኝ ባይ አባቷን ጐትጉታ ስትፋታ ከተካፈለችው ንብረት ሌላ የበኩር ልጁንም ይዛበት ሔደች ።

ከዓመት በኋላም፣ በራሱ ምርጫ ለሁለተኛ ጊዜ አገባ ። የዚህችኛዋም ኪጋብቻቸው በፊት የነበራት ጠባይና ቃሳይ የነበረው አስመሳይ ትሕትና ቀስ በቀስ እየተለወጠ በመሔዱ እያደር አልጣጣም አሉ። ከእርሱ ፍላጐት ውጪ፣ ባሻት ጊዜ ወጥታ ባሰኛት ጊዜ የምትመለስ፣ ሲፋጣትና ሲቆጣጠራት የምትደነፋ፣ ተይ ሲላት የሚብስባት፣ ሰው ጤፉ ቢጤ ሆነችበት ። ይህቺኛዋ የፍቺ ንትርክ ሳታበዛ፣ “ምን በወጣኝ ነው ከማንም ግትር ጋር አበሳዬን ማየቴ፤ ልጄን እንደሁ ዕድሚ ለናቴ አቀማጥዬ አሳድገዋለሁ” ብላ ትታው ሔደች ።

ከአንድ ሌላ ተጨማሪ የወንደላጤነት ዓመት በኋላ፣ ለሦስተኛ ጊዜ ከሌላ የኑሮ ጥያቄ ጋር ተፋጠጠ ። ላቀች ተገኜ ። የራሱን የጠባይ ግልባጭ ያገኘ ስለ መሰለውም፣ “ይህቺን እንደልቤ ልቆጣጠራትና ልገሥፃት እችላለሁ” አለ ።

* * *

“አሁን ለቃም አብረን ሔደን ቤቱን አይተሽዋል ። ያን የመሰለ ቤትና ንብረት፣ መኪናይቱንም አይተሻታል ። በቀኝሽ ነው ተነሥተሽ የመጣሽው! ተይ ዝም በይ! ዕድላም ነሽ ። እስቲ እኔ ያገኘሁት ምንድን ነው? ፈጣሪ አምላኽ ደህና ውሃ አጣጪሽን ሰጥቶሻል ። ተስለሽ እንደሁ ስለትሽን አግቢ ። ይኸነዬ ነው ብልጥ መሆን ሞኚት ። ብትበደይና ቢከፋሽም ቀኛማች አሉ፣ እኔም አለሁ ። ስንቶቹ ናቸው ተኛ አገር እየመጡ በየሰዉ ቤት አሳራቸውን የሚንጡት? ደሞ ያንቺን ማን ያገኘዋል! ኧረ ዝም በይኝ እቴ! አንቺኮ ዋል አደር ብለሽ ለብዙ ሰው ትተርፊያለሽ — —እ!” አሉ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ወሬያቸውን ሲያጠቃልሉ ።

“እኔ እኮ ተእድሙም አንቱ እንዳልሁ ብየኋለሁ” አለች ከደማቁ ልብሷ ጋር እየፈገገች ።

“እኔማ ያንጀቴን አውጥቼ ነገርኩሽ ። ወንዶቹም አገር ቤት የሔዱት ደስ ብሏቸው ነው ። ደግም አላረኩ እንዴ?” አሉ ስሜቷን በፈገግታቸው እየገዙ ።

“እሺ ብየሁ የለ?” አለቻቸው ባጭሩ ።

ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ፣ በልዩ ልዩ ምክንያት ወጣ ባሉላት ቁጥር
የቤቱን በር መለስ ታደርገዋለች ። ቀሚስና ሹራብ ፣ ነጠላና ሻሽ እየ
ቀያየረች ፣ የሸራና አጭር የቆዳ ጫማዋን እየለዋወጠች ፣ በረጅሙ
የቁም—ሣጥን መስተዋት ቁመናና መልኳን ማየት አዘውተረች ። የገዛ
ቁመናዋን ትወደዋለች ። አረማመድና አኳኋኗ በአካባቢው እንዳየቻ
ቸው ወጣት ሴቶች ባለመሆኑ ፣ እነሱን ለመምሰል ከግድግዳው እስከ
መስተዋቱ እየተመላለሰች ፣ ከፊቷም ከኋላዋም እየተመለከተች ፣ ራሷን
ከተሜ ለማድረግ ጥረቷን ቀጠለች ።



# ምዕራፍ ሠላሳ ሰባት

ልኬለሽ ፣ ከቀብር እንደሚመለስ ሰው ተክዛና አቀርቅራ ከልጆቿ
ጋር ስታዘግም ወደ ሰደት የምትሔድ እንጂ ፣ ወደ ቤቷ የምትመለስ
ትመስልም ነበር ። የሚንቀረቀረው እንባዋ ገጽታዋን አክብዶ ፈገግታ
ዋን ገፈፈው ። እናም ተበሳጭታ ፣ "ወይኔ ልጂት ! የመሔጃ እጦት ነዉ
ሬስ ሣር—አምባ የሚኬድበትም አገር አዶል!" እያለች ወደዚያው
ዘግማለች ። ቸርነት የጓደኛውን ቀኝ እጅ አንግቶና አቀርቅሮ ፣ ብቸኝ
ት እየተሰማው በቀዘቀዘ ስሜት ይከተላል ። የሁለቱም ልብ ተክዟል ።

እውቶቡሱ ካራቆሬ ከተማ እንደ ደረሰ ፣ ሙዝ ፣ ትርንጎና ሎሚ
ሚሸጡ ወጣቶች ፣ መኪና በመጣና በሔደ ቁጥር ፣ ዘንግና ዱላቸውን
መርኩዘውና ተደግፈው ወጪ ወራጁን የሚያስተውሉ ሥራ—ፈቶች
በቡት ። እነቀኛዝማች ሲወርዱ ፣ ምንዳዩም መከተል ያለበት ስለመ
ለው ፣ እነሱ በወረዱበት በፊተኛው በር በኩል ወረደ ።

ያባታቸውን መምጣት ቀደም ብለው የሚያውቁት የቀኛዝማች
ጆች ፣ ገና በማለዳ ነቅተው ይጠባበቁ ስለነበር ካባታቸው ጋር ተሳ
ሙ ። እቶ ወርቅነህና ምንዳዩም ሳሟቸው ።

"ምነው የሚካኤል ለት ሳትመጡ መቅረታችሁ? ነግሬያችሁ
ልነበረም?" አሉ ቀኛዝማች።

"እቴዋ እናንተ እየሁ ትምርታችሁን እጥኑ ፣ ምንታረጉ ትሔ
ለችሁ ብላን ነው" አለ ምንደሰይል ።

"የቧ ነገር ደሞ ይበዛል! እቡቲ በእንደዚያ ያለው ቀን ልጅ
ከለከላል? እኔ ነኝ ጥፋተኛው ፣ ተማሪ ቤት መዘጋቱን እያወቅሁ ፣
ነው ይዣችሁ በሔድኩ ኖሮ" አሉ ራሳቸውን እየነቀነቁ ።

"እንሔድ ብለናት ነበር ፣ አይሆንም ትትለን ጊዜ ዝም አልን" አለ
ናሽዬው ዋቢሁን ።

"አሁን እቧ ወዴት ሔደች፣ ጠብቂኝ ብያትም አልነበር?"

"ጥሩ ቢና ሸሆቹ ጋ ደርሺ እመጣለሁ ብላ ከትላንትና ወዲያ
ደይ" አለ ምንደሰይል ።

“አይ የቧ ነገር ! እዚህ እበላይዋ የመሶቢት ሚካኤል እያለ ፣ በሉ እንግዲህ የዘንድሮን በርቱ ፣ ለከርሞ አዲስ አበባ ትማራላችሁ ፣ መሰንበቻውንም ልብስ እልክላችኋለሁ ። ደብተር መግዣ ያስፈልጋችኋል እንዴ?” ብለው ድፍን አምስት ብር አውጥተው ለትልቁ ሰጡትና ፣ “በጎ ነሽ ወይ? በደህና ሰነበሽ ወይ ብሎሻል በሏት ፣ ባለቤቷ የለም እንዴ? መቼም እሱ ዕረፍት እሚሉ ነገር አያውቅ ።”

“ከሚሴ እንደሔዱ አልመጡም” አለ ትልቁ ብሩን እያየ ።

እነ ቀኛዝማች ተመልሰው ሲገቡ ፣ ምንዳዬም ከተል ብሎ ገባ። አውቶቡሱ እንደናዳ ድንጋይ እየተንደረደረ ፣ ከካራቆሬ ወደ አጣዬ የሚወስደውን ጠመዝማዛ ቁልቁለት ተያያዘው ።

* * *

ምንደስይልና ዋሲሁን ፣ የቀኛዝማች የመጨረሻ ልጆቻቸው ሲሆኑ፣ ወንዶቹ እነርሱ ብቻ ናቸው ። ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ከቀኛዝማች ስድስት ወልደው ፣ አራቱ ሴቶች ሲሆኑ አንዷ በሕፃንነቷ ስትሞት ፣ ሦስቱ ግን ፡ “የደምና ያጥንት አቻ ተገኘላቸው” እየተባለ በ13 እና በ14 ዓመታቸው አካባቢ ለባል ተሰጡ ። የቀኛዝማች ታናሽ እህት ወ/ሮ ጌጤነሽና ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ሲጀምር ጀምሮ እጅግም አይ ግባቡ ። ሁለቱም ቢጠየቁ ለወቀሳም ይሁን ለጥላቻ የሚበቃ ጉልህ ምክንያት አያቀርቡም ። ከአያሌ ዓመታት በፊት ግን ፣ ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ በተከታታይ ሴቶች በመውለዳቸው የተነሣ ፣ “ወንድሜን የስም ማስጠሪያ ወንድ ልጅ አሳጣቸው” ብለዋል ብለው ወሬ ስላደረሱላቸው ተቀይመዋቸው ኖረዋል ። በተጨማሪም ወ/ሮ ጌጤነሽ ማጀቴ ለጉዳይና ለገበያ ሲሔዱ በሹልክታ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ቤት ደረስ ይላሉ የሚል ያልተረጋገጠ ወሬ ከሰሙ ወዲህ ፣ “የባልን ዘመድ ሰብስቦ ነበር በእሳት መለብለብ” እያሉ ግንኙነታቸው ካንገት በላይ ሆነ ። ያም ሆነ ይህ ሁሉም ‘ያሉ” ወሬና አሉባልታ ስለነበር ሲገናኙም ሲለያዩም ይሳሳማሉ ። ደስ ሲላቸው ሞቅ ያለ ወሬ ያወራሉ ። እንደ ቀኛዝማች ሚስት ፍላጐት ቢሆን ልጆቹ ማጀቴ ቢማሩ ደስታቸው ነበር ። ነገር ግን ፣ ጣውንታቸውን ስለ ጠረጠሩና ፣ ‘በጅ—አዙር መዳኒት ብታቀምስብኝ ምን አባቴ እሆነዋለሁ’ በሚል ፍርሃት ፣ ልጆቹ አክስታቸው ዘንድ ተቀምጠው እንዲማሩ ተስማሙ ።

እባትዬው ግን ፣ “ጌጤነሽ የዋዛ ሴት አይደለችም ። ልጅ ማሳደግ ታውቃለች ። አንዳንድ ሰው ፣ ልጄን አሳድግልኝ ብለው ሲሰጡት ፣ ቀጥቶና ቆንጥጦ አያሳድግም ። ያባልገዋል። ልጆቿ ደብረ—ሲና ወጥተው



ለመማር የበቁት ፣ በሷ ብርታት ነው ። አባታቸውማ ሲበዛ የዋህ ነው። ሴቶቹንም ባለማስተማሯ ያንገበግባታል ። የኖረ ተማሪ ቤት ደግሞ ጥሩ ነው” በማለት ልጆቹን አልብሰውና ቀልበው ማስተማር ለሚችሉት ለወ/ሮ ጌጤነሽ በየጊዜው የልጆች ቀለብ እየተላከላቸው እንዲማሩ ተደረገ ። አራተኛና ሦስተኛ ክፍል ደርሰዋል ። የወ/ሮ ጌጤነሽ ባል ፣ ባንድ በኩል የሚያሳርሱ ፣ በሌላ በኩል ማር ፣ ቅቤና ጌሾ የሚነግዱ ሲሳይ ንብረታቸው የተትረፈረፈ ነው ።

* * *

አውቶቡሱ ፣ ሜዳ ሜዳውን ተግለብልቦና ቁልቁለቱን ተንደርድሮ ፣ ዳገት ሽቅበቱን እየተንጣጣና እየቃተተ ፣ አጣዬን ፣ ሰንበቴን ሸዋሮቢትንና አርማኒያን ዐልፎ አራት ሰዓት ላይ ደብረ—ሲና ገባ ። እነ ቀኛዝማች ከሾፌሩ ጋር ቡና ቤት ለመግባት መንገድ ሲጀምሩ ፣ ምንዳዬ ትዝ አላቸው ።

መንገደኞች በሁለቱ በሮች ሲወርዱ ፣ “ብዙ እንዳትቆዩ ! ቶሎ በልታችሁ ተመለሱ ! እዚህ እናንተን ሲጠብቅ እሚውል የለም ! ገና ስንትና ስንት መንገድ ነው እሚቀረን ፣ በጊዜ ካልገባን አዳሜ የጅርዬ መጫወቻ ትሆናለህ” አለ እበሩ ላይ ቆሞ የሚያስጠነቅቀው ጸጉረ—እንጭብር ቁታ ለባሽ ‘አውታንቲ’

“አንተ ማነህ ? እስቲ ምንዳዬ ብለህ ጥራልኝ እባክህ ?” አሉት ቀኛዝማች ።

ምንዳዬ ፈጠን ብሎ ወርዶ ስላልተከተላቸው ፣ ቅር ብሎት በሩ ላይ ደርሶ ነበርና ገና ከመናገራቸው ዱብ አለ ።

“ና እንጂ! ከእንግዲህ ወዲያኮ ሌላ ምሳ መብሊያ የለም” ብለው በፈገግታ አዩት ። ኃፍረትና የእንግድነት ስሜት እየተጫነው ፣ “እኔ እየሁ እመኪናው ላይ እእያለሁ ፣ አንቱን እከተልሁ እንደሁዪ እሚበላማ ይዣለሁ” ብሎ አንገቱን ሰበር አደረገ ።

“መያዝህንማ መች አጣሁትና ፣ ና ግድ የለህም ፣ ከዚሁ አገር እየለመድክ ትሔዳለህ —— ና !” ብለውት መንገድ ሲቀጥሉ ፣ አለ አሳብ ተቀምጦ ያጨማደዳትን ዙሪያ ቅምቅም ፡ ወገበ ሽንሽን ፡ አፈ—ሰፌ ቁምጣ ሱሪውን እያወናወነና ፣ ከታጠበች ውላ ያደረች ነጠላውን አጣፍቶ ዱላውን እንደያዘ ከመንገድ በታች ወደሚገኝ ቡና ቤት ተከትሎ ገባ ፤ ቀደም ብሎ የገባው መንገደኛ እንደልቡ እያውካካ ይበላል፣

ይጠጣል ። እነቀኛዝማች ሲገቡ ደንገጥ ያለ ፣ ወይም ኖር ብሎ የተቀበለ ፣ ገለል ብሎ መንገድ የለቀቀ ፣ እንደ ሣር—አምባ ወይም እንደ ማጀቴ ሰዎች በተለየ አክብሮት እጅ የነሣ ሰው ባለማየቱ ምንዳዬ ተገረመ ።

ሾፌሩና እነቀኛዝማች በጠባብ ቁልቁለታማ የቤት ውስጥ መተላለፊያ አልፈው ፣ ግርግዳ ላይ በምስማር ተንጠልጥሎና ተለጥፎ የእጅ ውሃ ከሚያንቆረቁረው ገረወይና ላይ ተራ በተራ ሲታጠቡ ፣ ምንዳዬ ጠንቀቅ ብሎ ያያል ። እሱም ያንን ሲፋተግ የሚሰማ ሽካራ እጁን ታጠበ ። ሦስቱ ባንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ሲቀመጡ ፣ ምንዳዬ የት እንደሚቀመጥ ግራ ገብቶት አካባቢውን በኃፍረት እያየ ፣ "ምነው ባልመጣሁ ወንድሜ! እዚያው እንደ ቢጤቴ በበላሁ!" እያለ ቆም እንዳለ ፣ ቀኛዝማች ፣ "እህ? ታጠብክና መጣህ?" ብለው ባይናቸው ወንበር ፈለጉለትና "ያውልህ እዚያ ጋ ወንበር" ብለው በጣታቸው አሳዩት።

ግር እያለው ወንበሩ ጠርዝ ላይ ሲቀመጥ ፣ ዱላውን በጭኖቹ አጣብቆ በግራ እጁ አነቃት ። ትላንትና ከሣር—አምባ ወደ ማጀቴ ሲሔዱ ፣ ቸርነት ቀኛዝማችን ባለማጀቡ ዱላ ብቻ በመያዙና በኋላም ምንዳዬ ጠበንጃውን ሲሰጠው እሱም ዱላውን ተቀብሎ ስለነበር ፣ ዱላውን ሲያይ ባልንጀራው ትዝ አለው ። ወዲያው በጤፍ እንጀራ ሁለት ዓይነት የጾም ወጥ ፣ ሁለት ሾጣጣ ቃሪያ አስከትሎ ቀረበለት። ተስተካክሎ ሳይቀመጥ መብላት ጀመረ ።

ከነቀኛዝማች ጋር የተቀመጠው ሾፌር ፣ እግሩን አንፈራጦና ወደ ጠረጴዛው አቀርቅሮ በሚያበለጨልጭ ብርማ ማንኪያና ሹካ ፣ እያንዘላዘለና እየጠቀለለ ፣ ሹካውን ብድግ ያደርግና ወደሚዝለገለገው ነገር ጉንበስ—ጠጋ እያለ ሲበላ ፣ ምንዳዬ ድንገት ዐይኑን ወርወር ሲያደርግ በማየቱ ከው ብሎ ደነገጠና ፣ "አበስ ገበርኩ!" ብሎ ቶሎ ዘወር አለ። አንዳች ነገር ታይቶት ዝግንን—ስቅጥጥ አለው ። አንጀቱ ተቆለፈ ። "ምኑን ይሆን እያንዘላዘለ እሚበላው? እንካከተውብኝ ይሆን እምላኬ ?" ብሎ ብሽ አለው ። "እህሉ ላይ ምን እየህበት ቢሉኝስ? እነሱ የበሉትን እኔ መተየስ የሌላ ያስመስልብኝ የለ ?" በማለት እየተናነቀው በልቶ ቁራሽ ስትቀረው ፣ እጁን ወንበርና ጠረጴዛው እግር ላይ አባብሶ ተቀመጠ ። እነቀኛዝማች ሲታጠቡ ሲነሡም ፣ አብሮ ሔዶ ታጠበና ተመልሶ ሲወጣ ሾፌሩን ተጠየፈው ።

"በል ሒድ ግባ ፣ መጣን ——" አሉት በትዕዛዛዊ ድምፅ ። እጁን ዱላው ላይ እያሻሸ ወደ አውቶቡሱ ሲመለስ ፣ ቀደም ሲል ልብ ብሎ ያላያቸው መኪናዎች በዙበት ። ሙዝ ፣ ትርንጎ ፣ ሸንኮራ አገዳ ፣ ሎሚና ቆሎ የሚሸጡ ሰዎች ፣ ከወዲያ—ወዲህ የሚተራመሰው



መንገደኛ ፣ ተጓዦችን የሚጣራ የመኪና ጡሩምባ ፣ ልዩ ልዩ ዘፈን የሚያሰሙ ድምፅ ማጉሊያዎች — — —አካባቢው ጭምር ግር አለው ። ተሳፍሮ የመጣበት መኪና የትኛው እንደሆነ ጠፋው ። ዙሪያውን እየዞረ አንድ ባንድ አየ ። ሦስቱ እሽንጣቸው ላይ ፣ አፉን ከፍቶና ጥርሱን አሹሎ የሚዘል ነፈራም አውሬ ተስሎባቸዋል ። "የኛ እንዲህ ያለ ስቅል አልነበረበትም ፣ እንዲያው ቅጠልያ ነው" ብሎ ያንበሳውን ሥዕል ትኩር ብሎ አየው ። ሌላ ቀይ ሻንጣም አውቶቡስ ላይ የሚጋልብ የነጭ ፈረስ ሥዕል አየና ፣ "ይኸም አዶል" ብሎ ዘወር አለ ። ወዲያው አረንጓዴ ቀለም የተቀባውን አውቶቡስ አግኝቶ ጠጋ ሲል ፣ ድንገት የኋላው በር ተከፈተና አጠገቡ የነበሩትን ሽማግሌ አያቸው።

"አሁን እኔ ነኝ ከተማ ገብቼ እምሠለጥነው" ብሎ ራሱን በትዝብት ገመገመ ። በሦስት መደዳ አዝራርና በትልቅ መርፌ ቁልፍ ከተቆለፈችው ከደረት ኪሱ ፣ በትንሽ እራፊ የተቋጠሩ ሳንቲሞች አውጥቶ ሙዝና ሎሚ ገዛ ። ለሽማግሌው ሁለት ሙዝና ሎሚ ሰጣቸው ።

የጣርማበር ተራራ ፣ ትላልቅ የአለትና የቋጥኝ ፍላጭ ንብብሩን ፣ ወጣ — ገባ ገጣጣ ተረተሩን አግጦና ቀዝቃዛ ጉማም እየሩን ተከናንቦ፣ ከደብረ—ሲና ከተማ በስተምዕራብ ራስጌ ፣ ከሰሜን ወደ ደቡብ እየጓነ ፣ እየረበደና እየተዳፋ ተንሰራፍቷል ። ከተራራው እግር እስከ ደረቱ እየተጠማዘዘ የተዘረጋው የመኪና መንገድ ሰፊ እርከን ይመስላል ።

የደብረ ሲና ከተማ ጣርማ በርን አንጋጣ ስታይ ፣ ትልቅ ዔሊ ሥር ያረፈች ቢራቢሮ ስትመስል ፣ እሱም ግጥብጥብ ደረትና ደንደሳም አለቱን አንገልጦ ቁልቁል ይመለከታታል ። ዐልፎ—ዐልፎ ብትፈራውም ፣ እንደማይጨክንባት ታውቃለች ። እሷስ ምኗ ሞኝ ነው? የዘነጋ ተወጋ ብለው ያማከሯት ይመስል የባሕር ዛፍ አጥሯን ገጥግጣዋለች ። እሷ ያለ እሱ ፣ ግርማ ሞገሷ ተቀንሶ የምትቀል ፣ እሱም ያለ እሷ ዝናው ታውቆ ፣ ስሙ ጐልቶ የማይጠራ ይመስላሉ ። እኩያው አለመሆኗን ግን ማንም ይመሰክርለታል ።

ደብረ ሲና ፈጽሞ ሳትታሰብና ሳትታለም ፣ ሳትወለድና ሳትከተም የትየለሌ ዘመናት ቀድሟት ኖሯል! ደብረ ሲና እምትባል ትንሰዬ ከተማ እግሬ ሥር ትቀረቀር ይሆናል ብሎ በሕልሙም በውኑም አስቦት አያውቅ ። የዛሬን አያድርገውና ያኔዬ ከዘመናት በፊት የነበረውን የልምላሜ መጐናጸፊያውን ፣ ዛሬም እንደ ተከናነበ ቢኖር ኖሮ፣ እሱ ድንቅ ደብር ፣ እሷም ትራስጌዋ ያማረ ከተማ ትሆን ነበር ። ማን ያውቃል ፣ አንድ ቀን ይሆን ይሆናል እንጂ ዛሬማ ፣ ጨርቁን ጥሎ ፣ እላቂ ነጭ ሻሽ ሸብ ያረገ ንክ ደብተራ መስሎ በፀሐይና በውርጭ

አሳረ—መከራውን ያያል ። በጉም ሽንት ጠል የጸደቁ ቁጥቋጦና ጦስኝ ቢያጽናኑትም ፥ እርቃኑን ስላልሸፈኑለት ያለት ጎኑ ገጧል ።

ደብረ—ሲናም ዝናውን ሰምታለች ። እኩዮቹም ከሩቁ ይመሰክሩለታል ። እንዲህ ሁለመናው ተቆፍሮና ተጎድፍሮ ያዳሜ መፈንጪያ ከመሆኑ በፊት ፥ ስንቱን ጉረኛና ‘ማ እንደኔ’ ባዩን ሁሉ ወገቤን ሲያሰኘው ኖሯል ። አይቆጨውም ። ዛሬም ቢሆን ‘ዕውቀት የተላበሰ ሰው ተራራ ይነድላል’ አሉ ሆነና ተባብረው ቢነዳድሉትም ፥ ስንቱ መኪና አልቅሶና ፈሱን ጠብሶ ‘አውጣኝ ሞተሬ’ እያለ ሲንፏቀቅና ሲያዘግም እንደሚውል ደብረ—ሲናም ትመሰክራለች ። ምን እሷ ብቻ! አይርቁና አይቀርቡ ቢጤዎቹም ያውቁለታል ። ደብረ—ሲና እግሩ ሥር እንደ ተቆረቆረችማ ፥ በሁለቱ ያልቀና ጋራና ሸንተረር ፥ አረህና ሸለቆ ፥ አሻግሮ ያላየ ተራራም አልነበረም ። መቆፈርና መደፍጠጡን እኮ ቢቀምሱት ፥ ከቀያሽ ዐይን ሰውረኝ ሊሉ !!

አውቶቡሱ ሲንቀሳቀስ ቀኛዝማች ፥ ምንዳዬን አሻግረው አዩት። መኪናው ወደ ተራራው ወገብ እየተጠጋ ሲሔድ ፥ የከተማዪቱ ቤቶች ባረንጓዴ ወረቀት ላይ የተረጩ የነጭና የቡናማ ቀለም ፍንጥቅጣቂዎች መሰሉ ። የዋሁና ታማኙ ጣርማ በር ከፉ አስቦና ፈጽሞ አያውቅም እንጂ ፥ ከገላው ቆርሶና ከቋጥኙ ገምሶ ቢንድ ፥ ደብረ—ሲናም ደብረ—ሲና አትሆን ፥ እሱም ከንቱ የተራራ ቅሌታም ተብሎ ፥ ድን ጋይህ ላፈር በተባለ ነበር ። ታዲያ ካለ ነገሩ እንዲህ ያለውን ቅሌታም ናዳ ለቆ አያውቅም ።

ምንዳዬ ፥ በሁለቱ ትናንሽ ዋሻዎች ተደንቆ ሳያባራ ፥ አውቶቡሱ ከረጂሙ ዋሻ ዘው አለ ። ዋሻው ከወደሚገቡበት በኩል ሆነው ሲያዩ ፥ ከሌላው ጫፍ ያለው የመውጫ በር ጠበብ ያለ የፉካ ቀዳዳ መስሎ ይታያል ። አንዳንድ መንገደኞች ስለ ዋሻው እርዝማኔ ፥ የተጋነነ አስተያየት ይሰጡ ነበር ።

“አዬ ሥራ ሆዬ!” ሲል ምንዳዬ ተገርሞ ፥

“ጣልያን ምን ያልሠራው ሥራ አለ? እሱ ነው የሠራው” አሉት ያጠገቡ ሽማግሌ ሳይጠየቁ ። መኪናው ትንፋሽ መለስ ያደረገና አቅም ያገኘ ይመስል ፍጥነት ጨመረ ።

ምንዳዬ ፥ ደረቱ ላይ አንዳች ነገር እየተንተከተከና እየተጉላላ አቅል አሳጣው ። ታመሰ ። ሽቅብ—ሽቅብ አለው ። ሁኔታው ስለ ገባው ደነገጠ።

“ወይኔ ምንዳ! ገና ዛሬ ተዋረድኩ!” አለ ። ከፉኛ አጣደፈው ። ከፊት ለፊቱ ከመስኮቱ በኩል የነበረውን መንገደኛ ከወደ ትከሻው



ነካ ነካ አድርጎ ፥ “ወንድሜ፤ እንደዬ ብትቻገርልኝ ፥ ሊጣላኝ ነው መሰለኝ ይተናነኸኛል ። ሽቅብ—ሽቅብ ይለኛል ። የሰው መኪናና ሰው ታላበለሻሽ እንዳፍታ ብትነሣልኝ” አለ እየፈራ ።

“እኔም እንዳንተው ይጣላኛል ብዬ ነው ፥ መስኮቱን ሙጥኝ ብዬ ደይ—ደጁን እማየው” አለው ዘወር ብሎ ።

“ምን ያህል ብቆይ ብለህ ነው ፥ ሳንዳፍታው ነውዪ ፥ እያው ተኸምጨ አልቀር — — —” አለ ደረቱ ላይ እየተንተከተከበት ። እንደገና መለስ ብሎ አይቶት ፥ በርግጥም እንደ ተቸገረ ገባውና ተነሣለት ።

“ምን ያለው ሰውዬ ነው ወንድሜ፤ እንዳያመልጥህ አፍክን አፍኚ —— በል ቶሎ ዞረህ ና!” ሲል ፥ ሌሎቹም ፈጠን ብለው የጉን ዮሽ እየተንፏቀቁ ማለፊያ ለቀቁለት ።

ምንዳዬ ፥ በግራ እጁ አፉን ግጥም አድርጎ መርጎ እየተንገዳገደ እንደ ምንም መስኮቱ ጋ ደረሰና ፥ ራሱን በመስኮቱ አውጥቶ ደብረ—ሲና የበላትን ሙልጭ አርጎ ዘረገፋት ። ዐይኖቹ እንባ አቅርረው ላቡ ግንባሩ ላይ ችፍ አለ ። ነፍሱ መለስ አለች ። እየተኾጎደጎደ የሚከተለበው ቀዝቃዛ አየር ላቡን አትንኖ አቀዘቀዘው ። ምራቁን በተደጋጋሚ ጢ—ቅ! ብሎና አፉን በነጠላው ጫፍ አባብሶ ዐረፍ አለ ።

“ጥኢት ቆየት በል ፥ በወጉ ይለይልህ ! ሙልይ ብሎ ቲወጣልህ ነው ደጉ !” አለው ቦታ የለቀቀለት ። በአቅራቢያው የነበሩት ሰዎች ፥ በተጠየፈ ስሜት አፍና አፍንጫቸውን በሸማቸው አፍነዋል ።

“መኪና ላይ እሚወጣ ሰው ዐመሉን ታወኸው ፥ ምናምኒት መእመስ የለበትም” አለ አንዱ ።

“አሂሂ ! መይ በሱ ሆነና ! እንዲያው አንዳንዱን እንዲሁ ይጣላዋሊ ፥ ይኸው ስንቱ ሰው እማዶል ወይ እምብርቱ እስቲገለበጥ በልቶ አሁንም እሚያሻምደው !” አለ ሌላው ቀበል አርጎ ።

ምንዳዬ ፥ ቀለል እንዳለውና ሆድ ዕቃው እንደ ተረጋጋ ፥ ወደ ቦታው ተመልሶ ሎሚውን እያሻሸ ማሽተት ጀመረ ።

አውቶቡሱ ከቀኑ ዐሥር ሰዓት ተኩል አዲስ አበባ እንደ ደረሰ ፥ አንዳንድ መንገደኞች ሾላና ቀበና ወርደው ፥ ጉዞውን ቀጠለ ። ምንዳዬ “አዲስ አበባ ገባን” ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ከመንገዱ ግራና—ቀኝ ያሉትን ቤቶች አፉን ከፍቶ ሲመለከት ፥ አንዱን አጣርቶ ሳያይ ሌላው እየተተካ መኪናው ሲገሠግሥ የሚያየው ነገር ሁሉ ወደኋላ እየተፈተለከ

ያመለጠዋል ። በዚያን አኳኋን የሚያልፋት ልዩ ልዩ መኪናዎች ውልብ ሲሉ ትኩር ብሎ ያያቸዋል ። በሁለቱም አቅጣጫ የሚጓዘውን ሕዝብ አይቶ ፣ ‘እንዴት ያለ ትልቅ ገበያ ቢኖር ነው ቢጓዝ—ቢጓዝ እማያልቀው’ አለ በሐሳቡ ። አውቶቡሱ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ሰሜናዊ በር ፊት—ለፊት ደርሶ እንደቆመ ፣ ጥቂት ሰዎች ጓዛቸውን እየያዙ ወረዱ ። እንደገና ወደ ቀኝ ታጠፈና ጥቂት ተጉዞ ቆመ። እውታንቲው ወርዶ ወደኋላ ዞረና መኪናው ላይ ተለጥፎ የታዘለውን መሰላል ዘረጋው ። ቀደም ብለው የወረዱት ቀኛዝማች በተከፈተው የኋላ—በር ወደ ውስጥ ብቅ ብለው ፣

“ምንዳ! ደርሰናል እኮ! ናውረዲ!” አሉት ። ሲወርዱ ባለማየቱ ደንግጦ ተገረመ ። የስንቅ ከረጢቱን አንጠልጥሎ በፍጥነት ወረደና ዱላውን ይዞ ከበስተኋላቸው ቆመ ። የሚያየው ነገር ስለ በዛበት ግር አለው ።

ሁለት ዕቃ አውራጅ ሸቃዮች የቀኛዝማችን ጓዝ አውርደው አንድ ላይ ደበሩት ። “ይኸው ነው፣ የቀረ የለም፣” አሉ አንጋጠው እያዩ ።

“የለም! ይኸው ነው!” አለ እውታንቲው ፣ ዕቃውን አስተካክሎ ሸራውን እየዘረጋ ። አውቶቡሱ ጉዞውን ሲቀጥል ፣ ምንዳዬ ትኩር ብሎ እያየ ባይኑ ሸኘው ።

በተቀለለው ጓዝ ዙሪያ የቆሙት ደረተ—ገላጣና ጭቅቅታም ጸጉረ እንጭብር ፣ አዳፋ ለበሶች ፣ ፍም የመሰሉ ዐይኖቻቸውን አጉርጠው ያያሉ ።

“በነዚህ በቀፈታሞቹ ይብሳል ፣ ምድረ—አባሕና !” ይላሉ እንደ ተለመደው ። የሥስቱም ሱሪ እተለያዬ ቦታ ላይ ተቀዳዶ ፣ በማይመሳሰሉ ጨርቆች ተጥፏል ። የጀርባና የትከሻቸው ላይ ልብስ ፣ የቀድሞ ቀለሙ ጠፍቶ ጤፍ መስሏል ። ምንዳዬ የቀኛዝማች ሎሌዎች መስለውት በአቀባበልና በሁኔታቸው ተገርሟል ። “ያዲሳባ አሽከር ጌታውን አያከብርም ማለት ነው፣ ምን ይመሳሰላሉ ደሞ ?” ብሎ በንቀት አያቸው ። እንደኛው ኩሊ የቀኛዝማችን ግቢ የብረት በር አንኳኩቶ አስከፈተ ። ዘበኛው መንገዱን ተሻግሮ እጅ ነሣና ገለል ብሎ ቆመ ።

“ቤቱ ይኸ የምታዩት ነው” አሉ ቀኛዝማች ።

“እኮ ስንት ይከፍላሉ፣ ከአውቶቡሱም ላይ አውርደናል” አለ አንዱ አሸቦ ፊት ።



“እናንተ ተናገሯ! ብታወርዱም ቤቱ ቅርብ ነው!” አሉ አቶ ወርቅነህ ኮራ ብለው ።

“በያንዳንዱ ስምንት—ስምንት ፍራንክ ትከፍላላችሁ!” አለ አጠር ያለ ቀይ ዳማ ደንደሳም ።

“እንጦጦ አድርሱልን እኮ አላልናችሁም! ቤቱ ይታይሃል!” አሉ አቶ ወርቅነህ ቆጣ ብለው ።

“እንጦጦ ድረስማ ሦስትና አራት ሰይቼንቶ ያስፈልጋችኋል” አለ አንደኛው የተመለመለ አጠና የመሰለ ከሲታ እየሣቀ ።

“የምን ንትርክ ነው! ትወስዳላችሁ አትወስዱም!” አሉ ቀኛዝማች ጮክ ብለው ።

ምንዳዬ ፣ ሰውዬው ሲቆጡ በማየቱ ዱላውን ጠበቅ አድርጎ ተመቻችቶ ቆመ ። ማንም አላየው ። ኩሊዎቹ እርስ በርስ ተመካከሩና ፣ “በሉ ስድስት—ስድስት ፍራንክ ትከፍሉናላችሁ” አለ ቀይ ዳማው ደንደሳም ።

“ትወስዱ እንደሁ ውሰዱ! አለበለዚያ ዞር በሉ ከዚህ! እንግዶች መሰልናችሁ እንዴ ፣ ከነሱ እኩል ቆመን ስናወራ ጊዜ?” አሉ አቶ ወርቅነህ ደማቸው ፈልቶ ።

ኩሊዎቹ ተበሳጭተው ገለል—ገለል ሲሉ ፣ አንዱ ወደ ምንዳዬ ቀረብ በማለቱ፣ “ወሒድ ታጠገቤ!” ብሎ ዱላውን አዙሮ አፈጠጠበት።

“ይቺ ፋርጣ እንዳትነፋሽ! እነሱ ጋ ቀልድ የለም” አለ ቀጭኑ። እነቀኛዝማች ሣቅ አሉ ።

“በሉ እናንተ እንዳላችሁ ። ዛሬ ቤሽቲያ ቀን ነው! እናቱን! ጮርናቄና አቦስታ ከተገኘ ይበቃል” ብሎ አጠር ያለው ወፍራም ሊሸከም ጐንበስ ሲል ፣ አንዱን ስልቻ ጤፍ አሸከሙት ። ሦስት ሦስት ጊዜ ተመላልሰው አደረሱና ፣ ከዘበኛው ጋር አጥሩ በር አጠገብ ቆሙ ። እነቀኛዝማች ወደ ግቢ ገባ ብለው ፣ “በደንብ አስቀመጡት?” አሉት ዘበኛውን ።

“አዎ” አለ ባጭሩ ።

ምንዳዬ ፣ መንገዱን ከተሻገረ በኋላ አብሮ ወደ ግቢ በመግባት ፋንታ ፣ ካጥር ውጪ ግንቡን ተደግፎ ቆመ ። ኩሊዎቹ ገንዘባቸውን ተቀብለው ሲወጡ ፣ ወፈር ብሎ ዐመድ የነዛበት መሳዩ ፣ ምንዳዬ በማያውቀው አኳኋን ከእጅና ከትከሻው እንደ መናጥ መንዘር

እያለ ፣ “እጠቃቀስኩ!!” ብሎ የሚመታው አስመስሎ ለቀልድ ያህል ሲቃጣው ፣ ምንዳዬ ከፉኛ ደንግጦ ባነነና ፣ “ምንዳ ገላግሌ!!” ብሎ በያዘው ዱሻ ጀርባው ላይ አቦነነው ። ደህና አድርጎ አቅምሶት ኖሮ ፣ “አ!!” ብሎ ከትከሻው ልምጥ አለ ። ምንዳዬ አጠገብ የደረሰው ረጂም ቀሸረር ኩሊ ፣ እጅግም ባልከረረ ፈጣን ምት ምንዳዬን እጉንጩ ላይ ሲያቀምሰው ፣ ብዥ አለበት ። በነጠላው አንቆ ሊደግመው ሲል ቀኛዝማች ዘለው ወጡና ፣ “ልቀቀው!” ብለው ሽጉጣቸውን መዘዙ ። “እከካም ሁሉ! ማን አባቱ ነው እሚነካው? አንድ ባንድ አነጥፍሃለሁ!” ሲሉ ደንግጦ ለቀቀው ።

በመመታቱ ደንገጥ ያለው ምንዳዬ መለስ ስላለለት ፣ መኻል አና ቱን ሊከካው ሲል በዘዴ ወደ ጐን እመር ስላለበት ሳተው ። ኩሊዎቹ እየሣቁና እየዛቱ ሲሔዱ ፣ “ምን ይሆናል! አላገሩና አለቦታው ተገኝቶ ነው እንጂ ፣ በቁምህ ነበር ሽንትህን እሚያሸናህ” አሉ ቀኛዝማች ሙክ ብለው ። ምንዳዬ ከንፈሩን እንደ ነከሰ ቀኛዝማችን ተከትሎ ወደ ቤት ገባ። እነ አቶ ወርቅነህ ሳሎኑ ውስጥ ፎቴ ወንበሮች ላይ ተዝናንተው ሲቀመጡ ፣ እሱ ግን ፈንጠር ብሎ እንጨት ወንበር ላይ ፀረፍ አለ ። “ዋ ባዶ እጅ መሆን! ይኸነዬ በጥይት እማንጠራራውን!” አለና እንዴት በዱላው እንደ መታው ሲታወሰው ፣ ‘አላስተረፍኩትም ፣ አንጀቴን አርሻለሁ ፣ እሳቸው ባይደርሱልኝ ግን ፣ ለሦስት አፈር መሬት ያስግጡኝ ነበር’ አለ በልቡ እየሣቀ ።

የስንቁን ከረጢት እግሩ ሥር አኑሯታል ። ቀስ በቀስ ክፍሉን ተመለከተና ፣ ከወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ይበልጥ ተደነቀ ። ተወልዶ ያደገበት መንደርና አካባቢ ፣ ልኬለሽ ፣ ልጆቹና ቸርነት ታዩት ። ገና ካሁኑ ትዝታቸው ሰቦት ፣ አዲስ የናፍቆት ዘር በልቡ ውስጥ ተዘራ ።

* * *

“ከእንግዲህ ወዲያ መጠንከር ነው” አሉ አቶ ወርቅነህ ። “ ሰው ሁሉ ተሻሽሎ ያደገው ፣ በብልጠትና በብልሃት ነው ። አዳዲስ ወዳ ጅና ዘመድ ባገኙ ቁጥር ፣ ጠቃሚ ጠቃሚውን መምረጥ ያስፈልጋል። ማግበስበስ አያስፈልግም ። ምንም ይሁን ምን የውለታ ትንሽ የለውም። አንድ ሰጥቶ ሁለትና ሦስት መቀበል ነውር አይደለም ። ማንኛውም ሰው በቅድሚያ የሚያስበው ስለራሱ ነው ። ዋናው ቁም—ነገር ታዲያ ፣ እስኪይዙና እስኪደላደሉ ድረስ እንደ ሐረግ ቀስ ብሎ ነው መንጠ ላጠል” ብለው ወደ ኋላ ተለጠጡ ።

“እውነትዎን ነው! መቼም መሰንበቻውን ፣ ብዙ ቁም—ነገር እጫውቾዎታለሁ ። ለእንደርስዎ ያለ ብልህ ሰው ደግሞ ፣ በመጠኑ



ከነገሩት ይበቃዋል ። በዚህ ላይ ከሩቅ ጮማ የቅርብ ቆሎ ይበልጣል ። መቼም ነገሬ ሳይገባዎት አይቀር ። ሩቅ ቦታ ያለ ርስት የማንም መቀ ለጃ ነው” አሉ ቀኛዝማች ።

“ያ ያባት ርስት ፣ ያባት አገር መሬት ነው ። ለልጅ ፣ ለልጅ—ልጅ የሚተላለፍ ነው ። ሰው ጫማ ጠበበኝ ብሎ እግሩን አይከረክምም ፣ ባይሆን ጫማ ይለውጣሊ! እና ያኛው ፣ መሠረትና ማረፊያ ነው ። እኛ እኮ መነጽሩ ያለው በእጃችን ነው ። ጥሩ—ጥሩው መሬት የት ቦታ እንደሚገኝ እናውቀዋለን ። እያጣራ የሚነግረን ሰው ይዘናል ። መስነ ፍና ችላ—ችላ ማለት የለብንም ። እኔ እንኳ የያዝኩትን ይባርክልኝ ። እንኮይ የመሰለች ልጅ ጀባ ስንለው ፣ ውለታችንንማ ካልከፈለን ምን ዋጋ አለው?” አሉ አቶ ወርቅነህ ፈገግ ብለው ።

“እረ የውለታው ጋጋታ ቀርቶብኝ በገዛ ገንዘቤ!” አሉ ቀኛዝማች ውስጥ ውስጡን ተደስተው ፣ ላይ—ላዩን እየተኩራሩ ።

“በገንዘብዎም በኩል ቀስ ብለው ይደርሳሉ ፣ እሱን ለኔ ይተዉት” አሉ አቶ ወርቅነህ ፣ በወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ፣ በሞገስና በላቀች ምክንያት የሚገኘው ጥቅም እየታያቸው ። ቀኛዝማችም ባላሰቡት ሁኔታ ስለሚ ገኘው ጥቅም እየተገረሙ ልባቸው ተስፋ አቋተ ።

ከወደ ማድቤት በኩል ባለው በር የሚገባው አየር ፣ የቡናና የወጥ ሽታ እየወሰደ ቤቱን አወደው ። የግቢው የብረት በር አአአ! ኢኢኢኢ! የሚል ድምፅ ከማሰማቱ በጓሮ በር በኩል ወ/ሮ መንበረና ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ተከታትለው ገቡ ።

አቶ ወርቅነህ መዘውር ፣ ካንገት በላይ ሣቅ—ፈገግ ቢሉም ውስ ጣቸው ተከፋ ። ‘እስቲ ምን አስቸኮላቸው ፣ ባለቤትዬዋ ብትኖርስ?’ አሉ በሐሳባቸው ። ሴቶቹ ከነቀኛዝማች ጋር ከተሳሳሙ በኋላ ፣ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ መለስ አሉና ፣ “ውይ ምንዳ! መጣህ? እሰይ! እሰይ! እንኳንም የመጣህ?” ከማለታቸው ተነሣና ተሳሳሙ ። ደስ አለው ።

“ምነዬ ገባችሁ?” አሉት ።

“ጥኢት ቆየት ብለናል” አለ ምንዳዬ እንደ ቆመ ።

“በል ተኽመጥ ፣ ሚስትህ ደህና ነች? ልጆችህስ?”

“ደህና ናቸው ። አንቱስ ደህና ነሁ?” አለ አቀርቅሮ ።

“ደህና ነኝ! እዝጊሐር እምስጌን! ተኽመጥ!” ብለው ተመለሱ ።

* * *

እነ ቀኛዝማች ፣ ደብረ ቢና ቁርስ በልተው ሲወጡ ፣ የይፋትና ጥሙጋ አውራጃ ፍ/ቤት ዳኛን ያገኟቸውና ዳኛው ካሏጋበዝኩዎት ይላሉ ። የአውቶቡሱ መነሻ በመድረሱ ቀኛዝማች አመስግነው ፣ ነገር ግን ፣ አቶ ወርቅነህ መዘውር ቤት ስልክ ደውለው በመንገድ ላይ መሆናቸውን እንዲነግሩላቸው በትሕትና ይጠይቋቸዋል ። ዳኛውም ስልክ ቁጥሩን ከመዘገቡ በኋላ ፣ "ባለቤትዎ ደህና ናቸው ?" ይላሉ ።

"ደህና ነች ፣ ለሚካኤል ድግስ እዚሁ ሰንብተን ፣ እኔ ቀደም ብዬ መመለሴ ነው ። እሷም ሰንበትበት ብላ ትመጣለች" ይሏቸዋል ። ዳኛው ከእኩለ ቀን በፊት መልእክቱን ሲነግሩ ፣ "ሁሉም ናቸው የመጡት?" አሉ ወ/ሮ መንበረ ።

"አዎ! ቀኛዝማችና አንድ እንግዳ ሰው አብረው አሉ ፣ ባለቤትዬዋ ግን አልመጡም" አሉ ሚስትዬዋንም የተጠየቁ የመሰላቸው ዳኛ ። ወ/ሮ መንበረም ስለ ወንዶቹ እጠይቅ ብለው የወ/ሮ እልፍ—ይከንዱንም አለመመለስ ሰሙ ። ሴቶቹ ይህን ማረጋገጫ በማግኘታቸው ስተት ብለው ወደ ቀኛዝማች መኖሪያ ሔዱ ። ሆኖም ዘው ከማለታቸው በፊት ዘበኛው ባልገባው የአጠያየቅ ዘዴ የሴትዮዋን አለመምጣት ዳግመኛ አረጋግጠዋል ።

* * *

ከ'እንደምን ሰነበታችሁ' በኋላ ፣ አንዷ ለባለቤታቸው ፣ ሌላዋ ለአስቀማጫቸው ፣ በስልክ የተነገረውን መልዕክት ነገሯቸው ። ቅር ተሰኝቶ የቆየው የአቶ ወርቅነህ ልብ ተረጋጋ ።

ሠራተኛይቱ እጅ አስታጥባና ገበታ አቅርባ ጠላ ቀዳችላቸው ። ምንዳዬ በሚያየው ሁሉ በመገረም እንዳንድ ውል—የለሽ ሐሳቦች ሲያስብ ቆየና ዐይኑን ወደ ጐን ጣል ሲያደርግ ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑን ያያቸዋል ። "እኝህ ሴትዮ ፣ ብለው ብለው እንዲህ እሚያጥበረብር ቤት ገብተው ዓለማቸውን ያዩ ጀመር ። ለካ ሁሏም የተባላችው ለዚህ ኖሯል ? በዚህ እያያዛቸውማ ቀስ በቀስ ሊያስለቅቋቸው ነው ?" አለ ወለሉን በአድናቆት እያየ ።

እነቀኛዝማች በዝግታ እየበሉና እየጠጡ ፣ ወሬውንም እህሉንም ጠገቡት ። እነሱ እንደ ጨረሱ ፣ ሠራተኛይቱ በቁርስራሹ ላይ አንድ እንጀራ ጣል አድርጋና የነካ የነካካውን አስተካክላ ለምንዳዬ ስታቀርብለት ፣

"እቴ ?" አላት ድምፁን አለስልሶ ። "ይኸን አፌን ጐመጥመጥ ብለው ።"



እሱንም እንደነቀኛዝማች አጐንብሳ ማስታጠቡ አልታይሽ አላት ። "ና! ተከተለኝ" ስትለው ቀስ ብሎ ተከተላት ። የለበሳት ባለ ሰማያዊ ጥለት ነጠላ ከትከሻው ላይ ተንሸራታ ተንዘርፋለች ። እነስ ያለ በር ከፍታ ወደ ሌላ ክፍል ይዛው ገባችና ፣ "ያውልህ ታጠብ!" ብላው ተመለሰች ። አካባቢውን ቢያይ ውሃ አጣ ። ከፊት ለፊቱ ፍንጃል የመሰለ አፈ—ገላላ ቀሪ ግድግዳው ላይ ተለጥፏል ። ከወደ ግድግዳው በኩል ፣ ከጠርዙ ላመል ታህል ዝቅ ብለው ሁለት ብርግ የተቀቡ ባለ መስቀል ጉትያ ቁልም ብረቶች አፋቸውን ከፍተው አንገታቸውን ደፍተዋል ። አለፍ ብሎ ነጭ የገላ መታጠቢያ ገንዳ አየና ፣ "ይኸስ ጣጣ ቲኖርባቸው ፣ ቡሆ ማብኩያቸው ነው መሰል" አለ በግምት ። "እዚህ ውሃ እሚሉ ነገር የታል? ምን አረግ እቆያለሁ ፣ ምን ያለችው ናት ወንድሜ?" ብሎ ሊወጣ ሲል ፣ ሠራተኛይቱ የዘገየ ስለ መሰላት ፣ "ምነው አለመታጠብህ? ወሃው ሔደ እንዴ?" አለችው ድንገት ገብታ ። አንዱን ቧንቧ ከፈት አድርጋ ፣ "እንዴ አለውኮ! ና! ታጠብ ይኸውልህ" ብላው ወጣ ከማለቷ የሚንቆረቆረው ውሃ በቀዳዳው በኩል ሲሰርግ በማየቱ ፣ ወዴት ይሆን እሚገባው በማለት ጐንበስ ብሎ ቢመለከት ምንም አጣ ።

ነጭ ስኒ በሚመስለው ንጹሕ ዕቃ ላይ ብታጠብ ይቆሽሻል በማለት ከውሃው ላይ በቀኝ እጁ እየጠለፈ ወለሉ ላይ ታጠበና አፉን ሁለት ሦስትዬ ጉመጠመጠ ። ቧንቧውን ለመዝጋት እየፈራ ጉትያውን ይዞ ከወዲያ ወዲህ አዞረው ። በመጀመሪያ በዝቶ ፣ በድጋሚው የተቃራኒ ዙር ጥምዘዛ ቀንሶ ስለ ተዘጋለት ደስ አለው ። እጁን በሸማው ጠራርጎ ሊወጣ ሲል ፣ ከፊት ለፊቱና በግራ ቀኙ ሦስት በሮች በማየቱ ግራ ገባውና ፣ "ወየው ጉድ ፣ በየትኛው በር ይሆን የመጣሁት? የዋለ አፌን ጠልቼው ነውዬ— — —ምነው በኸረብኝ ወንድሜ!" እያለ ቁሞ ሲያጉተመትም ሠራተኛይቱ እንደገና መጣችና ፣ "ታጠብክ ወይ?" ብላ በሩን ልትዘጋ ጠጋ ስትል ፣ ወለሉ ላይ ውሃ ፈስሶ በማየቷ "ምነው ወለሉ ላይ አፈሰስከው? የወለወልኩትን አበላሸህብኝ" ብላ ቆጣ አለች ። ምን እንዳበላሸ አልገባውም ።

"ምን ዓይነት ነገር ነው? የማንንም አንኮላ ባላገር ያመጡና ሰው ያስቸግራሉ ፣ ሴትዮዋን ሳሠለጥን ሰነበትኩ ፣ አሁን ደሞ ይኸን የባሰበት ይዘው መጡ" አለች በልቧ ።

ከቀረበለት ወጥ መኻል ፣ የጥቅል ጐመኑን አልጫ ወጥ ትኩር ብሎ አየው ። የሰባ ሥጋ ነው እንዳይል ፣ ሥጋ—ሥጋ አልልህ አለው ። ጐመን ነው እንዳይል ነጣበት ። "ይኸ ደሞ ምን እሚሉት ይሆን ጌታዬ? ብዬ—ብዬ ዘንድሮ ኸን እንዳይ ነገር ሳልበላ እቀራለሁ?" ካለ

በኋላ ፣ ጣዕሙን ለመለየት ያህል ሁለት ሦስትዬ ቆንጥሮ ጉረሰና ወደ አደገበት ወጥ መለስ አለ ።

ሠራተኛይቱ ለነቀኛዝማች ቡና ስጥታ ፣ ለሱም አነስ ባለች ጀሬም ስኒ ከነመቀመጫው ወስዳ እግሩ ሥር አኖረችለት ። በሦስት ቶትታ ጨለጣት ። በደንብ በልቶ ሳይጠግብ ፣ እጁን ወደ ወንበሩ የኋላ እግር ሰደድ አድርጎ አባበሰና ደገፍ ብሎ ተቀመጠ ። ገና ላይን ሳይዝ መብራቱ በራ ። ጣራው ላይ ተለጥፈው የሚበሩትን ቁመተ— ዱላ መብራቶች እንዳየ ተደነቀ ። ሌላ ክፍል የበሩትን ድቡልቡሎቹን ወደዳቸው ። 'እንዲህ ያሉት የጠፉ ከብት መፈለጊያ ቢገኙ ጥሩ ናቸው' አለ በሐሳቡ ።

ቀኛዝማች ፣ አቶ ወርቅነህ መዘውርንና ባለቤታቸውን ለመሸኘት አብረው ሲወጡ በማየቱ ፣ ምንዳዬ እሱና ቀኛዝማች በእንግድነት የገቡ መሰለውና ፣ ዱላና ከረጢቱን አንጠልጥሎ እስከ ግቢው መኻል እንደ ደረሰ ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ባጋጣሚ መለስ ሲሉ ስላዩት ፡—

"ወዴት ትሔድ ልጄ? አንተኮ እዚሁ ነው ቤትህ" አሉት እየ ፈገጉ ። ቀኛዝማችም ፣ "የኛኮ ቤታችን ይኸ ነው ። በንግድነት የገባን መሰለህ እንዴ? በል ተመለስ!" አሉት ያ የሣር—አምባው ብልህና አስተዋይ በማያውቀው አካባቢ በመሳሳቱ የጓደኛው ያህል ቅር እያላ ቸው ።

የቀኛዝማች ዘበኛ ፣ የአቶ ወርቅነህን የልብስ ሻንጣና ደብረሲና የተገዛውን ሙዝ ፣ ትርንጎና ሸንኮራ አገዳ የያዘ ባለ ማንጠልጠያ ቅር ጫት ተሸክሞና አንጠልሎ ወጣ ። ቀኛዝማችና ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ እነ አቶ ወርቅነህን በታክሲ አሳፍረው ሲመለሱ ፣ አቶ ወርቅነህ ደስ አላላቸውም ። እቤታቸው እንደ ደረሱም ፣ "እሷስ የራሷ ጉዳይ ፣ አንቺ ለምን አብረሽ ሔድሽ? ይህን ያህል ድፍረት ጥሩ አይደለም ። እስከ ዛሬም መመላለሷን አልወደድኩላትም ። ከዚህ ሁሉ በርትታ አጠቃል ላቸውም ። ካልሆነም እሷን የመሰለች ሴት ወይዘሮ ስንቱ ነው ፈላጊዋ ። ቀስ ብለሽ ንገሪያት ፣ እኔም ዋል አደር ብዬ እመክራታለሁ" ሲሏ ቸው አልመለሱላቸውም ።

ቀኛዝማችና ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ጥቂት ካወሩ በኋላ ፣ የሕይወት አካል የሆነውን ልፊያቸውን ለመላፋት መኝታ ክፍል ገብተው ከብ ርድ ልብሱ ሥር ያልተጠበሰ ሸክላ መሰለዋል ።

ሠራተኛይቱ ፣ ለራሷና ለዘበኛው ራት ስታቀርብ ምንዳዬንም ጠርታ "ራት እንብላ" አለችው ። እሱ ግን ፣ "እኔ ይበአኛል ፣ የበላሁትም አልጎደለ" ብሎ ተግደረደረ ።



'ካእኛ ጋ ይሻልሃል ብዬ ነው እንጂ ፣ ለብቻህ ላቀርብልህ ነበር" አለችው በችኮላ ።

"ተበላሁማ ተሰው ጋ ነው ደጉ ። እኔ አይሻኝም ብዬ ነውዴ!"

"ቢሆንም እኛን ደስ እንዲለን አብረኸን ብላ" አለ ዘበኛው ።

"ተምሬ ነው ፣ በእቶኝ ነው ። በያ ላይ መኪናው ሲያነዝጠኝ ውሎ..."

"ባይሆን እንኳ ቅመሰው ——— ራት አይደለም እንዴ?" አለው ።

"ቅድም የበላኸው አልጣፈጠህም እንዴ?" አለችው እየሣቀች ።

"እረ ተየቱ —— ለጥፍጥናውስ ምንም አይወጣለት ።"

"ባይሆን አንድ ሁለተዬ 'ንኳ ጉረስ — — የገባ አይጎዳም" ሲለው ዘበኛው እንደ ተባለው አደረገ ።

"የጌቶች ዘመድ ነህ?" አለ ዘበኛው ። በሥራው ላይ ጠርጥሮ ታል ።

"አዎድ!"

"መቼ ተነሥታችሁ ነው?" አለችው በተራዋ ።

"ተቤት የወጣነውማ ትላንትና ነው ፣ ማጀቴ አድረን ነውዴ—"

"ዛሬ ሰባት ሰዓት አካባቢ ነው ስልክ ተደውሏል ብለው የላኩ ብን" ስትለው ነገሩ ስላልገባው ዝም አለ ።

"ሴትዮዋሳ? እዚያው መቅረታቸው ነው እንዴ?" አለ ዘበኛው እያላመጠ ።

"የማ ሴትዮ?" አለ ድንገት ።

"ሚስትዮዋ!"

የወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ አመጣጥ ቶሎ ገባውና ፣ "መሰንበቻውን ይመጣሉ" አለ የወንበሩን ጠርዝ እያሻሸ ። ምንዳዬ ከራት ጋ የቀረበለትን ጠላ ወድዶ የብርጭቆውን ማነስ ስለ ጠላው ፣ "በዚህ ምን ያህሉ ቢጠጣ ያጠግባል?" አለ በልቡ ።

ሠራተኛይቱ ፣ "ገበሬ ነበርክ?" አለችው ።

"አዎድ!"

"እኝህን ቤትዮ ታውቃቸዋለህ እንዴ?" አለችው ።

ያልሰማ መስሎ ዝም አላት ። በሆዱ ግን ፡ "ይቺ ደሞ የማን ናት ፍየል? አሁንኮ ዐቃቸዋለሁ ብላት ፡ ነገር ተወዲያ ወዲህ ልታቋልፍ ይሆናል" ብሏል ።

"እያኛው ቤት ተበትሬ ጋ ከረጢት ቢጤ ነበረችኝ" አለ ሠራተኛይቱን እያየ ።

ከመናገሩ ፡ "ላምጣልህ እንዴ?" ብላ በፍጥነት ሔዳ አምጥታ ሰጠችው ። ከረጢቱን ፈታና ፡ ባቄላ አክል ድብልብል ዳቦ ቆሎ ሁለት ሁለቴዬ ዘግኖ ሰጣቸውና ራሱም ሲበላ ፡ "እኔኮ መጀመሪያ የመጡ ዕለት እኝህ ቤትዮ ዘመዳቸው መስለውኝ ነበር" አለች ስላልመለሰላት ።

"ሆሆ! ኧረ ዝም በይ እባክሽ? አሁንስ ምን ታውቂያለሽ?" አለ ዘበኛው ።

"ኡኡቴ! ጣቱን እሚጠባ ሕፃን አረከኝ ፡ በመጀመሪያ አልኩህ እንጂ አብረው እየተኙ ነው እሚጠፉኝ? ሞኝህን ፈልግ!" ብላው ያላመጠችው እስኪታይ ሣቀች ።

"በይ ትደግሚኝ እንደሁ ድገሚኝና ልሒድበት— — አንቺ እንደሁ ——"

"ወዮ ጉድ! የዕድሌ ሆኖ ሙጢ አፍ አያጣኝ? ስንቱን ለፈለፈችው?" አለ ምንዳዬ ። ዘበኛው ጠላውን ጨልጦ ሲነሣ ምንዳዬ ዳቦ ቆሎ ጨመረለት ። "በሉ እንግዲህ እዚያቹ እጎጆዬ ልግባ ፡ ደህናደሩ" ብሎ ወጣ ።

ስለ ገጠር ኑሮ እየጠየቀችው ሲያወሩ ሠራተኛዋ የመጥሪያ ደወል ሰምታ ስትወጣ ፡ ቀኛዝማች ጋቢ ለብሰው ምንዳዬ ወዳለበት ክፍል እየተራመዱ ፡ "እዚያች እትንሺ ክፍል ውስጥ እንጥፊለት ፡ ለዛሬ እንደ ምንም ይደር" ብለው ወደ ተቀመጠበት ክፍል ስለገቡ ፡ ብድግ ብሎ ተቀበላቸው ።

"እህ! ራትህን በላህ?"

"እዎድ!" አለ አቀርቅሮ ።

"አይዞህ ትለምዳለህ! ትዝ አሉህ መሰል ልጆችህ?" አሉ እየሣቁ።

ዝም አለ ። ተመልሰው ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡ ።



ትንሺ ክፍል ከሳሎኑ በስተሰሜን ምሥራቅ ማዕዘኑ ላይ የምትገኝ ሲሆን ፡ ቀኛዝማች ዋበትና ንጽሕናዋን አይተው የጸሎት ቤት አድርገዋታል ። ሠራተኛይቱ ጆንያዎች አራግፋና የመጋረጃ ትራፊ ወፍራም ባለቀለም ጨርቅ በላዩ ላይ ዘርግታ አነጠፈችለት ። ከረጢትና ብትሩን ይዞ ወደ ተነጠፈለት ክፍል ገባና በሩን መለስ አድርጎ መኝታው ላይ ተቀመጠ ። መስኮቱ አጠገብ አንዲት ጠረጴዛና ወንበር ተቃቅፈዋል ። ብቻውን እንደ ተጎለተ ሐሳብ ወረረው ። እንዱን አስተንትኖ ሳይጨርስ ሌላ ይደነቀርበትና በእግረ—ሕሊና ይንገላታል ። ለማረሳሻ ያህል ዳቦ ቆሎ ማላመጥ ጀመረ ። ከሐሳብ ግን አልገላገለውም። "ምነው ባልመጣሁ ኖሮ?" አለ በቀላሉ ተስፋ ቆርጦ ። ከረጢቱን ቋጥሮና በተነጠፈለት የመጋረጃ ልብስ ላይ ነጠላውን ደርቦ ጋደም አለ ። ኮረኮንች ላይ የተኛ ይመስል በተደጋጋሚ ተገላበጠ ። ግራው ላይ የተንጠለጠለችውን የልኬለሽን ያደስ ቅል የምታህል አምፑል ገለጥ ሲል አያትና ፡ "እዚያው ነዳ—ነዳ እንደ ፍጥርጥሯ ትሁኒ የማላኽውን ነገር አልነሃካም" ብሎ ተከናነበ ።

በሌላው ሰፊና ምቹ ክፍል ውስጥ ቀኛዝማችና ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ልፊያቸውን ተላፍተው አንጀታቸውን እንዳራሱ ፡ "አንቱማ ተመችቶሁ ከረምኩ ፡ እኔ ነኝ ብቻዬን — —" አሉ በወቀሳ ።

"ምን ላርግ ብለሽ ነው ፡ የማይቀር ነገር ሆነብኝ ፡ ያለሱ ማን አለኝ? ሁሉስ ቢሆን በሱ አይደል? ለሌላው ብዬ መሰለሽ ለሚካኤል ብዬ ነው?"

"እኔ አልወጣኝም ፡ ምን አባቴ ቆርጦኝ! እኔ ያልኩት ሌላ ሌላውን — ሆ!"

"አንቺ ደሞ ክፉ ዐመል አለብሽ! እኔ ብቻ ሔጄ እሷ እዚህ አትቀር የቤቱ ጣጣ ያለሷ — — —" ብለው ሳይጨርሱ ፡

"እንዲያው ጨዋታውን ማለቴ ነውዬ ፡ ማ ከሷ እኩል ልጄ? 'ቂል ዘመድ ከልጅህ እኩል አርገኝ' ይላል አሉ ። ምንስ ቢሆን — —ዋ! —እቴ! እስኪ ይኸውም እንዲህ እንዳያያዙ ይሰንብት — — አሁን ሌላ ሌላውን — —" አሉ ።

"ሆሆይ! እስቲ አሁን ምን አንደልኩብሽና ነው ፡ ይኸ ሁሉ የነገር ዳር ዳር — — ልብስም ቢባል ከሰው በላይ አለሽ ፡ ቤትክም እንደ ሞላ ነው ። ሰውዬው እኔ ሆኜ አላፈናፍን ብያት ነውዬ — —ኡኡ! ያገር ያለህ ማለት ያለባትስ እሷ ነበረች ፤ ነገሩን ባታስላስይው ይሆናሊ ፤ ያንቺ ነገር ቢብሶብኝ እኮ ነው አስቀድሜ አንቺን መላኬ! እያሰላሰሉ ነው መናገር — —"

የሰውዬውን ቅሬታ የሚያስወግዱበትን የንግግርም ሆነ የሩካቤ ብልሃት አሳምረው ያውቃሉ ። ወንድዬው የሴትዮዋን ትርፍስፍስ ገላ ሲያዩና ሲዳብሱ ፡ ይይዙ ይጨብጡት ይጠፋቸውና ሕሊናቸው ይነሆልላል ። በእሳት ዙሪያ በርራ—በርራ እላዩ ላይ እንደምትማገድ የሳት ራት ፡ ሴትዮዋ ባዘቶ ገላ ላይ ተንፈላሰው ፡ ሩካቤ ምድጃ ላይ እንደ ስብ ሲቀልጡ ይረካሉ ። ከዚያ በኋላ የሚጠየቁትን እነሆ ፡ የሚታዘዙትን እሺ በማለት የልግስናቸውን ከረጢት ይፈቱታል ።

ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ ፡ አንድ ነገር አስበው ካልጋ ላይ ወረዱና ፡ እዚያው መኝታ ቤት ውስጥ ግድግዳ ላይ ተለጥፎ በተንጠለጠለው ቁመት ልከኛ መስተዋት ፡ ፊትና ደረታቸውን ፡ ሻሽና ክናዳቸውን እየደባበሱ ሲመለከቱ ፡ ጀርባቸው ወደ ሰውዬው በመዞሩ ፡ ሳሳ ባለው ልብስ በኩል የሚታየው ከመር ፡ ጠፍጠፍና ጋደም ያለው ዳሌና መቀመጫቸው ፡ የሰውዬውን ቀልብ መንጥቆ ወሰደው ። ባይናቸው የሠረፀው ገላ፣ እንደገና የሩካቤ አምሮታቸውን እንሸከሸከው ።

“ምነው መጥተሽ ብተኚና ዐረፍ ብንልበት ፡ አውቶቢስ ሲያን ገላታኝ እኮ ነው የዋልኩት” አሉ በጋባዥ ስሜት ። ልፊያቸው ሲቀዘቅዝ ሁለቱም እፎይ አሉ ።

*   *   *

ቀኛዝማች ፡ የወ/ሮ ደጅ ይጥኑን ገላና ፡ የተለየ ነፍስ እንዳለው ፍጡር እሽክም እያለ የሚንቀሳቀስ ቂጥ ሲመለከቱ ፡ የልጅነታቸው ጊዜ ትውስ ይላቸዋል ። ባጁ ፡ አጠር ብላ ፈርጠም ያለች ፡ ጤፍ ስትሰልቅ ፡ እሻሮ ስትድስ ፡ ክክ ስትከካ ፡ ወይም አጎንብሳ ቤት ስትለቀልቅ ፡ የሚያዘበጥጥና የሚርገፈገፍ ቂጥ የነበራት ያባታቸው አገልጋይ ነበረች ። ካባታቸው ሎሌዎች መኻል ጥርሰ—ዘርዛራ ፡ ክንደ—ጠንካራና አካለ ደልዳላ የነበረው መርጦ የባጁ ወዳጅ ነበር ።

“ገና አንድ ፍሬ ልጅ ነው” ይባሉ በነበረበት ጊዜ ካገልጋይና ከልጆቻቸው ጋር እንደልብ ይዛለሉና ይጫወቱ ነበር ። ያን ጊዜ መርጦ የበላይነህን ዕድሜ በማየትና ‘ቢያይስ ነገሩን የት ዐውቆት’ በማለት ባጁ በገባችና በወጣች ቁጥር ዙሪያውን መልከትከት ያደርግና ቂጧን ጠፍ—መታ ፡ ጡቷን ቆንጠር ያደርጋታል ። ይዋደዱ ነበር ። ቤቱ ጭር ካለ ደግሞ ድሪያው ይባባሳል ። ያቺን ሁሉ እንደ ቀልድ ተመልክተዋል።

ቀስ በቀስም ነገሩ ስለ ገባቸው ፡ ባጁ እና መርጦ የሚያደርጉትን ሁሉ ለማየት ይጓጉ ጀመር ። ዕድሜያቸው በጨመረ ቁጥር የባጁ ገላ አማራቸው ። የተመኙትን አላጡም ። መርጦ ቢከፋው ቢከረፋውም



በግኖ ዝም አለ ። ባጁ በልዩ ልዩ ሥራ እዚያው ቤት ለቤት ፡ ከጠላ ቤት ጐተራ ቤት ፡ ከበረት ጉረኖ ፡ እያለች ስታደዘድዝ ላያት የአካሏ እንቅስቃሴና ሙላት አጓጊ ነበር ። “ያላሳብ እየዋጠች ተውለከለከች” በተባለችበትና የወንድ ዐይን በሳበችበት ወቅት ፡ የበላይነህም ዐይን በባጁ ላይ ማረፉ ስለ ታወቀ ሁኔታው ተባብሶ ስም ከማስበሩ በፊት ፡ እንደ ጊዜው ‘የመኳንንት ልጆች’ የአምሮት ማብረጃ ሴት በግርድና ስም ተቀመጠችላቸው ።

ያ በልጅነታቸው የተጠናወታቸው የትልቅ ቂጥ አድናቆት አብሮ አድጎ አብሮ ጐልምሷል ። ከጥቂት ዓመታት በፊትም ማጀቴ ተወልደውና አድገው ፡ ወደ ደጋው አገር ተድረው ሁለት ሴቶች ከወለዱ በኋላ ተፋትተው ከተመለሱ ወዲህ ፡ ከወደ ደሴ የመጡ ልብስ ሠፊ አግብተው ለሁለት ዓመታት የኖሩትንና ዳግመኛ የተፋቱትን መልከ—መልካሟንና ዠርጋዳዋን ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑን አግኝተው ፡ በመጀመሪያ ወሽመው የኋላ—ኋላም አስቀመጧቸው ።

ሁኔታቸውን አይቶ የሚገዝት ካህን ፡ ተገቢ አይደለም ብሎ የሚገሥፅ ሽማግሌ ሳይታጣ ፡ ‘ብንናገር ይብስባቸው ይሆናል ፡ ወይም ከልጃቻቸው እናት ይፋታሉ’ በሚል ሥጋትና ጥርጣሬ ፡ እንዲሁም በአካባቢው የተለመደው የቅምጥና የቀላቢት ማስቀመጥ ልማድ ተደጋግፈው የልብ ልብ ሰጣቸው ። ሚስትዬዋንም ፡ “አንቺ ቤት ንብረትሽን አጥብቀሽ ያዢ ፡ ማየት ያለብሽ ልጆችሽን ነው ። ምን አጥተሽ? ምን ጎሎብሽ? ከዚህ ካንቺ ተርፎ ለሚሔደው ነው ሽጉዱ! ለነዳይ የተሰጠ ያክል ቁጠሪው ። እሳቸው እንደሁ ዘለው ዘለው ሲበቃቸው የት ይሔዱ መሰለሽ? የምር አይምሰልሽ ፡ ሁላችንም አይተነዋል ። ወንድና ብረት ምጣድ ቶሎ ይበርዳል” እያሉ የሚመክሩ የቅርብ ዘመዶች ቢበዙም የወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ልብ ግን እልህና ቅናት አረገዘ ።

*   *   *

ምንዳዬ ስሜቱ ተመሳቅሎ እንደ ባነነና በቅዠት እንደ ተንገላታ ነጋ ። ማለዳም ወጣ ብሎ አትክልቱን ፡ ግቢውንና የዘበኛውን ቤት ተመለከተ ። ከቁርስ በኋላ ቀኛዝማች ወደ ሥራ ለመሔድ ሲነሡ በማየቱ ግቢው መኻል ዱላውን ይዞ ጠበቃቸው ።

“ወዴት ልቱድ ነው?” አሉት አቋቋሙን አይተው ።

“ልከተልሁ ብዬ ነዋ! መሔድሁም አደል እንዴ?”

“የለም! የለም! ወደ ሥራ ስሔድ—ስሔድ ተከታይ አያስፈልገኝ”።

“ምነው ሰው እንደሌለው ሰው ብቻሁን መሔድሁ?”

“ዘመድ ጥየቃና ወደ ሌላ ሌላ ቦታ ስሔድ እነግርህና አብረኸኝ ትሔዳለህ — — አሁን ግን ግባና ቁርስህን ብላ” ብለውት ወጡ ።

ከቁርስ በኋላ ፣ “ና ደሞ ወደኔ ቤት እንሒድ” አሉት ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ ። እግድም ወደ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያንና ቁልቁል ወዳራት ኪሎ ሲጓዙ ፣ በሚያየው ነገር ሁሉ እንደ ተደነቀ ከቤታቸው ደረሱ ። ከላቀች ጋር ሲሳሳሙም ፣ እማያውቀው አገር መጥቶ የማያውቀውን ሰው በማግኘቱ ተደሰተ ።



# ምዕራፍ ሠላሳ ስምንት

አስካደች በጉጉት የጠበቀቻት ዕለት በመድረሷ ጥብቆ እንደተገዛለት ልጅ ቦረቀች ። ቤቷም በተስፋ ተከበበች ። ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ በራሳቸው እንሣሽነትና በአፈሣ ግፊት የገቡበት ጣጣ ተቃሎ እሱ ወደ ቤቱ በሚመለስበት ቀን ፣ አንዳንድ ተራ ሥጋት ቢታያቸውም ደስ ብሏቸዋል ።

“ቀኛማይ ብቻቸውን ሔደው ምንዳዬ ቢቀር ኖሮ አፈሣ እየችግድም ድርሽ አይልም ነበር” ሲል አንድ ሐሜተኛ ፣

“ቅዘናም ሆኖ ነውዬ በገዛ አገሩ እንዲህ ይንገላታ ነበር? ዘር አሰዳቢ! ሙትቻ” አለ ሌላው ።

“ከሰው ባለ ጊዜ ጋ ማ ተጋፋ አለው? እንሽላሊት እገል ብሎ እዘንዶ አፍ መግባት ነው ። ከሳቸው ጋ መጣላት ፣ ከንጉሥ ጋ የመጣላት ያክል ነው ። ነገሩ ወዲህ ነው ፣ መች ምንዳዬ ብቻ ሆነና!” ብሏል ሌላው ፈርቶ አስፈሪ ።

“ምንዳዬ ፣ ካልሔደማ በየት አባቱ ሊላወስ? የሠራትን ሥራ መች አጣትና! ከቀኛማይ ጋ በቄስ በመነኩሴ ብሎ መታረቅ እቅቶት መስላችሁ? የምንዳዬ ነገር አንከላፋ ሆኖበት ነዉ” የሚለው የስሚከሚ ወሬ ደግሞ ፣ ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱንም አበሳጫቸው ።

አሚታና አሉባልታውን ሁሉ ‘እህ’ ስለሚሉ ፣ “ሰውዬው እንደ ሔዱ እግራቸውን ጠብቀህ አትምጣ ፣ ለሰውም አፍ—ቢሆን ዋል—አደር ብለህ ስትመጣ ይሻላል” ብለው ልከውበት ነበር ። እሱም ሁለት ሰዎች አስከትሎ እቤቱ የገባው ቀኛዝማች ከሔዱ ከሳምንት በኋላ ነበር ።

ልኬለሽ ካንገት በላይ እየሣቀች ፣ “ኧረ አንተ እንኳ ሔደህ እንኳን ደህና መጣህ በለው ፣ ዝም ብለህ ስትቀር የሌላ ያስመስልብሃል” አለችው ቸርነትን ፣ እንደ ቀልድ ።

“እኔ አቶ ሰውዬው! ባልልስ ምን እንዳልሆን? ማ [illegible] ብዬ ነው በይ! ምንዳዬ ባይኖርም እኮ እኔና [illegible]” አ[illegible] የእልህ ሣቅ እየሣቀ ።

"እኔስ ደስ ብሎኝ መስለህ? ሰው እሰው አገር ተኽምጦ — —" ከማለቷ፤

"ማነው የሰው አገሩ ሰው? ይኸ ጀምበር ከጠለቀች እሚደረስበት አገርሽ ሩቅ ሆነና ነው እንዲህ እምትዪው?" ብሎ ሊቀጥል ሲል፣ አሻጋሪ ከወደ ደጅ ብቅ አለ። "እየሁ ኖረሃል እንዴ አሻጋሪ" አለ ቸርነት ወደ ውጪ እያየ።

"እማምዬ ተየህ ተግቢ ትወጣና — — ዋልህ ብላኝ — — እየሁ ነው የዋልኩት" አለ ተናዶ።

"ምነው ልጄ? ምን አጠፋ?"

"ምነው ነገሩን ስታኸው? ፈራኋ?" አለች ተክዛ።

"እነማንን?"

"ካፈሣ ጋር የመጡትኮ የዞን አምባ ሰዎች ናቸው፣ ባላጋሮቻችን አይደሉሚ!"

"እስቲ ሙት በይኝ! እኔ የታባቴ አወ ኩ?" ብሎ ወዲያው ተነሥቶ ሔደ።

ጠበንጃውን ይዞ እንደ መጣ፣ "አሻጋሪ! ና ሒድ ውጣና ተጫወት! ማባቱ እንደሚነካህ አያለሁ! ሱሪ አልታጠኩማ!?" ብሎ ካጥር ውጪ ይዞት ወጣና፣ "ሒድ ከባልንጀሮችህ ጋ ተጫወት" አለው። ልኬለሽ በአለኝታነቱ ተደሰተች።

ቸርነት ከአፈሣ ቤት በታች ዲብ ላይ ተቀምጦ፣ ረባዳው ጠባብ ሜዳ ላይ የሚጫወቱትን ልጆች ሲመለከት ደስ አለው።



## ምዕራፍ ሠላሳ ዘጠኝ

ምንዳዬ፣ አንድ ሁለተዬ ቀኛዝማችን ተከትሎ በሔደበት ጊዜ ባየው የከተማ ሁኔታ በጣም በመገረሙ፣ ሰውዬው ወጣ ባሉ ቁጥር፣ "ምነው ና እንሒድ ባሉኝ" በማለት ተከትሎ ለማየት በጣም ይጓጓ ጀመር። በተለይም አንድ ቀን ቀኛዝማችና አቶ ወርቅነህ መዘውር ምንዳዬን አስከትለው በራስ መኮንን ድልድይ አልፈው ፒያሳ እንደ ደረሱ፣ ስን ኳንና አዲስ መጤው ምንዳዬ ቀርቶ፣ በተደጋጋሚ ተመላልሼ አይቻ ዋለሁ ሲሉ የኖሩት ቀኛዝማች እንኳ በሚያዩት ልዩ ልዩ ብልጭልጭ የዕቃ ዓይነትና ብዛት፣ በየሱቁ የተደረደረውን ልብስና፣ ሽክ አርገው አልብሰው ያቆሟቸውን አምሳለ—ፈረንጅ አሻንጉሊቶች ሲመለከቱ በጣም ገርሟቸዋል። የሱማ ምኑ ተነግሮ! እነ ቀኛዝማች ከአንድ መደብር ፊት—ለፊት ቆመው፣ "ይኸኛው ይሻላል፣ ያኛው ይጠነክራል" እያሉ የሱፍ ጨርቅ ሲያማርጡ፣ ምንዳዬ ግን ዳለቻ የሱፍ ልብስ ለብሶና ባርኔጣ አድርጎ፣ አንድ እጁን እሱሪ ኪሱ ውስጥ ወሽቆ የቆመውን መጠነ—ሰው አሻንጉሊት ትኩር ብሎ ያይ ነበር።

በመጀመሪያ፣ "እንዴት አምሮበታል ይኸ ፈረንጅ! አዬ አቋቋም ሆዬ!" አለ። ነገር ግን፣ ቢያየው ቢያየው ንቅንቅ አይልም። "እቤት አሠለጣጠን! እንዴት ሰው አንደዬ'ንኳ ንእንቅ አይልም!" እያለ ሲገረም፣ ለካስ እነ ቀኛዝማች መንገድ ቀጥለዋል። ደግነቱ አልራቁም ነበር።

የሰዉና የመኪናው ብዛት፣ የቤቱ ንጽሕናና አሠራር እየገረመው ሲከተል ሌሎች አሻንጉሊቶችም በማየቱ፣ "እንዴት ፈረደበት ይሄ ሁሉ ፈረንጅ ወንድሜ" እያለ ሲያዝግም፣ አንድ ሱቅ በር ላይ እንደ ደረሱ፣ አንድ ሽማግሌ ፈረንጅ ብቅ አሉ። ምንዳዬ ትኩር ብሎ አያቸውና፣ እስከዚያች ቅፅበት ያልታየው በቀል ትዝ ስላለው ብልጭ አለበት። ወዲያው ጉዞ በመቀጠላቸውና ከሌላ ትርዒት ጋር በመገናኘቱ ትዝታው ጥሎት ነጎደ።

አንዳንድ ቀን ከቀኛዝማች ጋር ወደ ፒያሳ ወይም ወደ አራት ኪሎ ሲሔድ፣ የገረመውን ነገር መለስ ብሎ ወይ አሻግሮ ሲመለከት፣ ሳያስበው ከሰው ጋር ይጋጭ—ይጋፋና በጣም ይደነግጣል። ገጠሬነቱን የተገነዘቡ ሣቅ ብለው ያልፉታል። አንዳንዶቹ የየራሳቸው የቀድሞ

ሁኔታ ትዝ ይላቸዋል ። በዚሁ ምክንያት ስለሚሳቀቅ አብዛኛውን ጊዜ ከቀኛዝማች ጋር ለጠፍ ይላል ። በተለይም ደግሞ የመኪና መንገድ ያቋረጡ እንደሆን ፣ እሱን ነጥለው ይገጩት ይመስል መኪና መኪናዎቹን ሲመለከት ከቀኛዝማች ጋር ይጋጫል ፣ ወይም ቀድሟቸው በሩጫ ይሻገራል ። ብዙ ሰው በሚተላለፍበት አካባቢ ደግሞ የወጪ— ወራጁ መንገደኛ ትርምስ ያደናግረውና ተከታይ መሆኑ ቀርቶ ፣ ከቀኛዝማች ጎን አብሮ ይራመዳል ። ዘወር ብሎ ሲያይ ፣ ይደነግጥና ቶሎ ብሎ ያቺኑ እውቅ ቦታውን ይይዛል ።

ቀስ በቀስ መሔጃና መመለሻውን እያስተዋለ ፣ ምንም አደናጋሪና ዘወርዋራ ጐዳና የሌለበትን ከቀኛዝማች እስከ አቶ ወርቅነህ ቤት ያለውን መንገድ በሚገባ ለመደው ። በሁለቱ ቤቶች መካከል ሲመላለሱ ፣ ቀኛዝማች ፣ “የምሠራው እዚህ ውስጥ ነው” ብለው ያሳዩትን የምክር ቤት ሕንፃና ፣ “ይኸ ደሞ ያጤ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ነበር” ብለው የነገሩትን አካባቢ ሲመለከት ‘ምነው አንድ ቀን ገብቼ ጉዱን ባየሁት’ ይላል ። ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ቤት በሔደ ቁጥር ፣ ቤትዮዋ ሎሌነቱን ለማሳወቅ አወራርተውት ወጣ ሲሉ ፣ ሥራዋን እየሠራራች ከምታጫውተው ከላቀች ጋር ሲያወሩ በቀላሉ ይግባባሉ ።

ከማር—እምባ ማጀቴ ሲላክ ፣ መልክና ደም—ግባቷን ነገሬ ብሎ አይቶት አያውቅም ነበር ። እሷም እንዲሁ ። ተከጃጅለው አያውቁም ። ዛሬ — ዛሬ ግን ፣ ትኩር ብሎ ይመለከታትና ይገርመዋል ። የማጀቱ ልብሷን ቀይራና ጸጉሯን እንደ ነገሩም ቢሆን ጐንጉና ከመለሎ አቋቋሟ ጋር ሲያያት ፣ “ይኸ የከተማ እህል ውሃ ወዘና ያሳምራል ልበል ፣ ወይስ ይኸ ጨርቋም ምኑም ነገር አለው ይሆን ?” ይላል በሐሳቡ ። ባያት ቁጥር ልቡ ደንገጥ ማለት ጀመረ ።

ቀኛዝማችም ፣ “ከዚህ ከዘበኛው ጋር ይኸን አታክልቱን ኮትኮት ፣ ኮትኮት እያረጋችሁ ግቢውን ትጠራርጉና ፣ ሲመችህ ሲመችህ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ቤት እየሔድክ ዋል” ብለውት ስለነበር ፣ ለጊዜው እንደ ልቡ ነበር ። የምንዳዬ ቢጋለ በየጊዜው መመላለስና ከላቀች ጋር ማወራራት ያልታሰበ ቅሬታ በማስከተሉ ፣ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ፣ “ኧረ እግር አበዛህ ብለው እንዳይቆጡህ! ባይሆን ተሳቸው ጋ አብረህ ና” አሉት ሰወር አድርገው ። ለኔው አስበው ይሆናል በማለት ነገሩን አዞሮ አላየውም ። ቤትዮዋ ግን ፣ ደስ አላላቸውም ። ሞገስ እምባቸው ብቅ ባለ ቁጥር ፣ ላቀች ምንዳዬን እስከ ጋርላማው ፊት—ለፊት ሸኝታው ስትመለስ ፣ ወይም ከልቧ እየተንከተከተች ሲያወሩ ስለሚያጋጥመው ፣ ውስጥ — ውስጡን በግኖ ፣ ፀይኑ መቅላት በመጀመሩ እንዲህ ያለችውን በቀላሉ የሚያውቋት ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑም ፣ “ይኸ



ሰው ነገር ያበላሻል!” በማለት አሳብ ገብቷቸዋል ። ሆኖም ገፍተው የማይናገሩት ፣ ታማሠው የማይዘልቁት ጉዳይ ስለ ሆነባቸው ፣ ምንዳዬን ከሚገሥፁ ላቀችን ማጮሉ ስለሚቀል ፣ ቶሎ ብለው በተግባቡ ቀንዱን አሷት ። ምንዳዬ ግን “እኝህም እንደ ቀኛማች ተመርጠው የመጡ ናቸው መሰል! ያስታውአሉ ። እንዲያውም እኝህኛው ታይበልጡም እይቀሩ! መኺናም አላቸው” በማለት ሞገስ ወደ ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ቤት ገባ ሲል ‘ኖር’ ብሎ እየተቀበለ እጅ ከመንሣት በቀር ፣ ፀልፎ—ተርፎ በላቀች ላይ እጠረጠራለሁ የሚል ምንም ግምት አልነበረውም ። የሞገስ ነፍስ ግን ፣ በጥርጣሬ አበሳዋን ጨለጠች ። ፍቅርና ናፍቆት ወደ ቅናት በመለወጡ ምንዳዬን ክፉኛ ጠላው ።

* * *

“አሁንስ አገሩን ለምደኸዋል ፣ ቤትዮዋም መምጫቸው ደርሷል መሰል?” አለችው ላቀች ፣ ቀኛዝማችና ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ መኝታ ቤት እንደገቡ ።

“ተንግዲህስ ምንም አልል ፣ መኺና ላይ መበርገጉንም ትቻለሁ ፣ የታከተኝስ ተወዝፎ መዋሉ — — — ግብርትና በስንት ጣሙ — —”

“ለመሆኑ እማናቸው ጋ ትሆናለህ ብለው አመጡህ?”

“ይኸ ምን ይጠየአል! እያው እሳቸው ጋ መሆኑ ነዋ! — — አይፍረድ'ኮ ነው ፣ እዚያ ሥር—ሥሩን በነገር እየተነኳኮሱ ሲያተኹኑኝ ኖረው ፣ ይኸው ደሞ እየሁ መጣሁላቸው ። እንደሳቸውማ ቢሆን እያቀባብርም — —”

“አዎ ልጄ! እኔም በነገር—ነገር ተነሥቶ ፣ ሽው ብሎኛል” አለችው ዝቅ ባለ ድምፅ ።

“እንዴት ሰማሽ?”

“አንድ ቀን ሲታ እሳቸው ፣ ለቴዋ ሲነግሩ ሰምቼ ነዋ! አለያማ ከየቴ!”

“እኝህኛዋ ቴሰሙ ምን አሉ?”

“ዘመድ የምታቸው ያክል አለቀሱ ። ንድድ አላቸው” ብላ ጥቂት ዝም ካለች በኋላ ፣ “አንተ እዚያ ተተኽመጥክ ፣ እኝህኛዋ ተማን ጋ ይሆናሉ! እዚህ ተኽምጠህ እየተላላክ እንድታይላቸው ነውቁ ፣ እዚያማ እሳቸው ራሳቸው አሉ ።”

“እእ! እኝህኛዋ ጋ ምን አሳብ አለ ፡ የቤትዮዋ ዘመድ አሉ ። በያ ላይ አንቺ አለሽ ። ምን እሚያሳስብ ነገር አለ?” ብሎ ዐይኑን ስክት አድርጎ አያት ።

“የኔ እየሀ መቆየት’ንኳ ያጠራጥራል ፡ ብኖርስ ማ እንደ ወንድ ልጄ?” አለችው በዝግታ እየሣቀች ።

“ወዴት ልኬጂ?”

“ባል ታላገባሽ እያሉ — —” ብላ ሳትጨርስለት ፡

“ማንን?” አላት ተገርሞ ።

“አንድ ሰውዬ እዚህ ቲመላለስም አላየኸው?”

“የትኛው? — — መሰንበቻውን ብዙ ሰው አይቻለሁ ።”

“ለዘግ ብሎ ግራ እግሩን ላመል ጎተት እሚያረግ ሰውዬ ፡ አፍንጫው አጠር ያለ ደርፏጫ ቢጤ — — አላየኸውም እንዴ?”

“እኝህ ባለመኪናው?” አለ ባጋጣሚ ግምት ።

“አዎድ!” አለች ፈገግታዋ እየጨመረ ። ያቺ የሚያውቃት ላቀች ድንገት የተለወጠች ፡ እዚያው በዚያው ከሱ በልጣ እንደ ቀኛዝማች የከበረችና የተሾመች ፡ እንዲያውም ከዘመዷ በላይ የሆነች መሰለውና “አንቺ ደህና ቀን ወጣልሽ” አላት ሣቅ ብሎ ። ረጋ ብሎ ጠየቃት ። ዘርዝራ ነገረችው ።

በርግጥም ከሁለት ወር በኋላ ቀኛዝማችና ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ፡ አቶ ወርቅነህና ባለቤታቸው ፡ እንዲሁም አንዳንድ የጐረቤት ሰዎች በተገኙበት ፡ በሞገስ በኩል አቶ ወርቅነህ ፡ በላቀች ወገን ቀኛዝማች በላይነህ ታፈስ የውል አባት ሆነው ፡ እሱ በብርዕ ፡ እሷ ቀለም በተቀባ ዐውራጣት ፈርመው ፡ እሱ ለሦስተኛ ፡ እሷ ለሁለተኛ ጊዜ አገቡ ።

ላቀች ጥበብ ኩታና ቀሚስ ለብሳ ፡ ጸጉሯን ተሠርታና ጥቁር ተረከዘ አጭር መጫሚያ አድርጋ ላያት ፡ ዋልካ ዐፈር ላይ የበቀለች የነጭ አበባ እምቡጥ ትመስል ነበር ። ያላንዳች ዕልልታና ጭፈራ ፡ ሞገስ በሁለት ተጨማሪ አውቶሞቢሎች ጓደኞቹን ፡ እነ ቀኛዝማችንና መቅረት የሌለባቸውን ጐረቤቶች ይዞ ወደ ቤቱ ሔደ ። እዚያው አብሮ የዋለው ምንዳዬ ወደቤቱ ሲያመራ ፡ “ወይ መአየት! እነ ቀኛማይኮ አጅበዋት ሔዱ!” አለ ተገርሞ ።



## ምዕራፍ ዐርባ

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ፡ ከዛሬ ነገ አዲስ አበባ ይገባሉ እየተባለ ዘበኛውና ምንዳዬ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በየዕለቱ ከዐሥር ሰዓት ጀምሮ ይጠባበቁና አለመምጣታቸው ተረጋግጦ ወደ ቤት ሲመለሱ ፡ ቀኛዝማች “ምን ሆና ይሆን?” ይሉና የማታ—ማታ ምንዳዬን ወደ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ቤት ይልኩታል ።

ቤትዮዋም ከነባር የምኞትና የቅናት ሐሳባቸው ጋር ይጨቃጨቁ ይነታረኩና ፡ “መቼስ ምን አረጋለሁ” ብለው ይነሣሉ ። ምንዳዬን አስከትለው ሲሔዱ ምኞታቸው በተስፋ አብቦ ያሸተና ፡ ከቀኛዝማች ጋር እንደ ልባቸው ሲኖሩ ይታያቸዋል ። ምኞታቸው ከዘወትር ልምዳቸው ስለማይርቅ ፡ ከሰውዬው ጋር ቤተ ክርስቲያን እየሳሙ ፡ ግብዣና ድግስ ተጠርተው ከመኳንንት ሚስቶች ጋር ሲጋበዙ ፡ እሳቸውም ደግሰው ሲያበሉና ሲያጠጡ እየታያቸው ፡ አእምሯቸው በተስፋ ረክቶ ፡ ልባቸው በደስታ ይንደቀደቃል ። በዚህ የምኞትና የተስፋ ትርዒት መኻል ፡ ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ውልብ ሲሉባቸው ፡ “መድኃኒዓለም እባቴ በዚያው ያስቀርሽ!” ብለው ይሳሉና አእምሯቸውን ያረጋጋሉ ።

የቤትዮዋ መመላለስ ድንገት ተሰምቶ ፡ አዲስ እንካ ስላንቲያ እንዳያስከትልና ከቤት የሚነሣውን ወሬ አዳፍኖ ለማስቀረት ሲባል ፡ የቤት ሠራተኛዋና ዘበኛው በተለያዬ ተራ ሰበብ ከሥራ ተሰናበቱ ።

ወ/ሮ መንበረ ፡ ለወደፊቱ ወሬ እምታቀብል ሠራተኛ ሲወስዱላቸው ፡ ምንዳዬም በዘበኛው እግር ተተካ ። ከሰነበተባት የጸሎት ክፍል የመኝታ ምንጣፉንና ዳለቻ ስስ ብርድ—ልብሱን ጠቅሎ ወደ ዘበኝነት ቤቱ ተዛወረ ። አታፈናፍንም ።

ከጣራዋ ቅርበት የተነሣ ፡ አጠናይቱ አልጋ ላይ ቆሞ ልብስ ማውለቅ አይቻልም ። በሌሊት ቅዝቃዜና በቀን ግ'ቃትነቷ የተነሣ የቀድሞው ዘበኛ ፡ “አምስሽ አሹቂኝ” ብሎ ስም አውጥቶላት ነበር ። ምንዳዬ ትልቅ ሳጥን ከምትመስለው ክፍል ሲገባ አእምሮው ይጨነቅና የሐሳብ አሸን ይወረዋል ።

ዘበኝነቱን በጀመረ በሁለተኛው ሳምንት ፍጻሜ ላይ ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ሸዋርካብሽን አስከትለው ፡ ካውቶቡስ ሲወርዱ በትሕትና ተቀብሎ ከሁለቱም ጋር ተሳሳመ ።

"ሀ! ተናናርናታ! እዚህስ ጠበንጃም ሰውም አያስፈልገኝ" አሉ የመጡትን ኮተት ሲያስወርድ ከበስተጀርባው ቆመው ። "ያንማህ! አይይይ! የለህማ—የለህም!" ብለው ለዚያው ለማር—እምባ ጊዮርጊስ ሲነግሩት ፣ "መች አጣሁት! ግድ—የለሽም!" የሚላቸው ይመስላቸዋል ።

ዕቃቸውን ምንዳዩና ሦስት ኩሊዎች ተሸክመውላቸው ወደ ቤት ሔዱ ።

ቀኛዝማች ፣ ከሞገስ አምባቸውና ከአቶ ወርቅነህ መዘውር ጋር ሆቴል ውስጥ ተቀምጠው ፣ ወደፊት ስለሚገኝላቸው የገጠር መሬትና የከተማ ቦታ ሲወያዩ ከቆዩ በኋላ ፣ ሞገስ አቶ ወርቅነህን እቤታቸው አድርሶ ፣ በዚያውም ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑን ይዞና ቀኛዝማችንም ከሚጠብቁበት ቦታ አሳፍሮ እቤታቸው እንደ ደረሰ የመኪናውን ጥሩንባ ነፋ ።

ምንዳዩ ፣ በሩን ከፍቶ ብቅ ሲል ቀኛዝማች ከሴትዮዋ ጋር ሲመጡ በማየቱ ክፉኛ ደንግጦ ተርበተበተ ። በሩን ቶሎ ዘግቶ ከፊት ለፊታቸው ቆመና ፣ "እንዴ! ኧረ ወዴት ነው ቀደም—ቀደሙ? ባልተቤቲቱኮ መጥተዋል! ምን ሆናችሁብኝ!" አለ እጁን ግራ—ቀኝ ዘርግቶና ተንፈራጦ ።

ሴትዮዋ ብርክ ያዛቸው ። ድንገት በሩን ከፍተው ፣ "ደሞ ብለሽ ብለሽ እቤቴ ድረስ ምናባሽ ታረጊ መጣሽ? እ!!" የሚባሉ መሰላቸውና ውሃ ሆኑ ።

"ምነዉ ገባችና" አሉ ሰውዬው ፣ ድንጋጤአቸውን ውጠው ።

"ጥኢት ቆየች አሉ ።"

ቀኛዝማች ፣ በምንዳዩ መኖር ተደስተው ፣ 'እንዲያው ምን ላርግህ!' አሉ በልባቸው ። "አሁን ይኸ ሰው እዚህ ባይኖር ፣ ወይም ሌላ ዘበኛ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ጉድ ፈልቶ ነበር ። ወይ ቅሌት! እነሱስ እንደ ፍጥርጥራቸው! እኔ ግን ፣ በዚህ በማይረባ ጉዳይ ክብሬ ተዋርዶ ስሜ መሰበሩ ነበር" አሉ ፣ አሁንም በውስጣቸው ።

ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ፣ "አበስ ገበርኩ ጌታዬ! አለመጠርጠርን የመሰለ ምን መጥፎ ሞኝነት አለ? ይኸነዬኮ ምንዳ ባይሆን አሳር ጉብተን ነበር! እናንተስ ያው እንደ ፍጥርጥራችሁ — — እኔን ምን ይውጠኝ ነበር! እሰው ቤት ምን ታረጊ ገባሽ ብባል ፣ ምን እመልስ ነበር? የኔ መድካኒያለም ሰወረኛ! ሰወረኝ! እኔም ቅር—ቅር እያለኝ ነበር የመጣሁት" ብለው ምልስ አሉ ። ሞገስ ወሽኩቶ እንደ ተጋለጠ



ሰው ፈዝዞ ቆሟል ። ሴትዮዋ በተዋረድኩ ባይነት እንጀታቸው እንደ ጨሰ ፣ ሞገስ "ምን አጉል እግር ጣለኝ? በሰው ነገር ጣጣ ገብቼ ነበር" እያለ ሴትዮዋን ይዞ ተፈተለከ ።

ቀኛዝማች ፣ ምንዳዩን አስከትለው ወደ ቤት እንደገቡ ከባለቤታቸው ጋር ተሳሳሙ ። ፈንጠር ብላ ተቀምጣ የቆየችው ሸዋርካብሽ ቀኛዝማች ሲገቡ ዝም ብላ በመቆሟ ፣ "ምነው ዝም ብለሽ መቆምሽ ልጄ! አይ ያንቺ ነገር! መላቢስ ፣— — ይኸነዬኮ ፈርተሽ ነው! ቢይ ነይ ጫማ ሳሚ!" አሏት ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ፣ ባይዞሽ ባይነት ሁኔታ። እሳቸውና ምንዳዩ የመጡ ዕለት ግር እንዳላቸው ሁሉ ፣ እሷም ግር ብሏት ስለነበር ፈዛለች ። ፈርታለችም ። ወለሉን እየደለቀች ሔዳ ፣ የቀኛዝማችን ጉልበት ልትስም ጐንበስ ስትል ፣ ቀበል ብለው ሳሟትና "እኔኮ ስገባም አላየሁሽ ፣ ደህና ነሽ ወይ?" አሏት ያመጧዉ ነገር እየገረማቸው ።

"ደህና ነኝ !" ብላ እንዳቀረቀረች ተመለሰች ። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ፣ በምንዳዩ መምጣት የተነሣ ላደረባቸው ብስጭት እሳቸውም ሸዋርካብሽን ያስከተሉት እልሃቸውን ለመወጣት ነበር ።

* * *

ምንዳዩ ፣ ዘበኝነቱንና የአትክልት ኩትኳቶውን ፣ ሸዋርካብሽ ቤት ውልወላውን ተያያዙት ። እሱ ኩትኳቶውን ጨርሶና ግቢ ማጽዳቱን አዳርሶ ዐረፍ ሲል ፣ ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱን ወጣ—ገባ ሲሉ ስለሚያያቸው ፣ የማር—እምባ ድርጊታቸው ትዝ ይለውና ደሙ ይፈላል። ቢሆንም ፣ አኗኗሩን አይቶ ንዴቱን ዋጥ ያደርግና ፣ 'ጅብ እስኪነክስ ያነክስ' በማለት ግንባሩን አይቋጥርም ። ሴትዮዋም የጥላቻቸውን ያህል ሳይሆን ፣ "ነገር ከተበላሸ ወዲያ እምቡር—እምቡር ቢሉት ምን መላ አለው?" ብለው ከፊታቸው ፈገግ ፣ ከጃቸው ለቀቅ ማድረግ ጀምረዋል ።

"አንቺ ሸዋርካብሽ! እንግዲህኮ አንቺ እሚሉሽን አትሰሚም ። መቼ ይሆን አንገት እምታበጂው ። ነግሬሻለሁ ኋላ! ደሞ በሀል ውሃ በደሉት እንዳታስብይኝ ። ለሞተ እህል እሰው አፍ እንዳታስገቢኝ ። ሰው በሆዱ አይቀጣም ። ነወር ነው ። እሳቸውም ቢሆኑ ደስ አይላቸው ። ታንዳንድዬም ከኛ ወጥ አበስ አርጊለት — — የሰማይ ቤቱን እንዳታዘጊብኝ" ይላሉ ። በቀኛዝማች ፊትም ፡ "ምንዳ ራትክን በላህ? ማን እንዳይገባ ብለህ ነው? ዛሬ ሙያህን ስትንገላታ ነው የዋልከው ፣ ግባና ጋደም በል" ሲሉ ሰውዬው ደስ ይላቸዋል ።

* * *

ሞገስ እምባቸው ፣ ስለ ምንዳዬ ማንነትና አኗኗር ፣ ከገዛ ባለቤቱና ከቀኛዝማች ከሰማበት ዕለት ጀምሮ ያ ያንድ ሰሞን ቅናትና ጥርጣሬው ወደ ልባዊ ርኅራኄ ተለውጦ ወዶታል ። ወደ ቀኛዝማች ቤት በሔደ ቁጥርም ፣ አትክልት የሚያይና አካባቢውን የሚቃኝ መስሎ እንደዘበት በማውራት ፣ የምንዳዬን ጠባይ ከተረዳ ወዲህ በወደደ ሰሜትና በፈገግ ፊት እጁን ዘረጋለት ። ሁለት አርጀት ያለ ካኪ ኮትና ሱሪ ከነ ሸሚዙ የሰጠው ዕለት እንኳን ተቀባዩ ቀኛዝማችም ደስ ብሏቸዋል ።

"አሁን ምን አርጌልሁና በምን አቀሁኝ ነው ይኸን ኩላ አምጥተህ መስጠትህ?" ብሎ ሲያመሰግን ፣ "እንደ ትልቅ ስጦታ አትየው ፤ ቀላል ነገር ነው ፤ ለወደፊትም እረዳሃለሁ" አለው ።

ልብሱን ማደሪያው ውስጥ አስቀምጦ ፣ አንዳንድ ቀን ሥራውን ሲጨርስ እየቀያየረ መልበስ ጀመረ ። ቦላሌውን ታጥቆ ሸሚዙን ወደ ውጭ ይለቅና ፣ ቁልፎቹን በሙሉ ይቆልፋቸዋል ። ኮቱን ሲለብስበት ደግሞ ሸሚዙ እሱሪው ላይ ይለጠፍና ጠርዙ ይጠቀለላል ። ይህን ዋል አደር ብሎ አረመ ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፣ የሸሚዙ አንገትጌ ሸቅብ ታጥፋ ትቆምና የነጭ ፍየል ግልገል ጆሮ ትመስላለች ።

ቀኛዝማች ፣ ከላይ ደህና ለብሶ ያለ መጫሚያ የሚከተላቸውን ምንዳዬን ለማስደሰት ተረከዙ ባንድ ወገን የተበላ አሮጌ ጫማቸውን ሰጡት ። ያን እንደልቡ እየተዘረጋ እንዳሻው ሲረግጥ የኖረ እግሩን አሮጌ ሽፍን ጫማ ውስጥ ያለ እግር ሹራብ ይደነቅርና ጥርቅም አድርጎ ያስረዋል ። ልብሱን ቀይሮና ጫማውን አጥልቆ ቀኛዝማችን የተከተለ ዕለት ፣ አንድ እጁን ሱሪ ኪሱ ውስጥ ከትቶ ሲሔድ በጣም ደስ ይለዋል ።

ሸዋርካብሽ ፣ ቀደም ብላ ምስጢሩን የማታውቀው የመልእክት ጉዳይ ያስከተለባት ችግር እያንገበገባት ፣ ቀስ በቀስ መግባባትን ሊፈጥር በሚያስችል ሁናቴ ፣ ከምግብና ከመጠጡ ደበቅና ጠቀም እያደረገች ትሰጠው ጀመር ። በሴትዮዋ ሰበብም ያቄመባት ስለሚመስላት ፣ እሷ እንዳሏት አዳሪና በይ እንዳሏት መስካሪ መሆኗን እንዲያውቅላት በሰበብ ባስባቡ ጠጋ ጠጋ አበዛች ። አልሸሻትም ። ሲወጡላት ሔዳ ማውራትና ሲያስቀይሟትም ጠጋ ብላ ማማት ጀመረች ። እሱም ቀስ በቀስ ነገሩን እየተረዳ ፣ ከቀን ወደ ቀን ልቡን አላላላት ።

* * *

ቀኛዝማች በላይነህ ፣ ኑሮአቸውን የማሻሻልና ከነእከሌ እኩል ወይም በላይ መሆን አለብኝ የማለቱን ውጣ—ውረድ አሙቺ በመሰ



ላቸው ጊዜና ቦታ ሁሉ ተያይዘውታል ። የከተማ ኑሮ ዕውቀትና ልምድ ካላቸው ሰዎች ጋር በተዋወቁ ቁጥር ፣ እንዴት ባለ ብዙ ንብረት ለመሆን እንደቻሉ ለመስማትና ለማወቅ ፣ ሁለመናቸው ጆሮና አእምሮ ይሆናል ። ከዓላማቸው ጋር የሚጣጣም ሰው ካገኙ ደግሞ እጃቸው የልግስና መዓዱን ያወርደዋል ።

በገጠር ያሳለፏቸውን አያሌ ዓመታት በከንቱ እንደ ባከኑ በመቁጠር ፣ የኑሯቸው ሥርና ግንድ የሆነውን ሕዝብና አካባቢ እያማረሩ ይጸየፉታል ። የፍላጐታቸውን ማከናወኛ መሰላል ግን እዚያው መሬት ላይ ተክለው ፣ በገጠሩ ሕዝብ ትከሻ ላይ ይረማመዳሉ ።

"ሰሙ ቀኛዝማች" አለ ሞገስ አቶ ወርቅነህ ቤት ተቀምጠው ሲያወሩ ። "ዛሬ እርስዎን በጣም የሚጐዳዎት ይኸ በየወሩ የሚከፍሉት የቤት ኪራይ ነው ። ቀላል ገንዘብ አይደለም ። በአራትና በአምስት ዓመት ራሱን የቻለ ቤት ያሠራል ። እናም የመጀመሪያ ሥራዎ የመኖሪያ ቤት መግዛት ቢሆን ጥሩ ነው" አለ ።

"እኔም ቀደም ብዬ ነግሬያቸዋለሁ" አሉ አቶ ወርቅነህ ለማስታወስ ያህል ።

"በሱማ ምነው ተስማምተን! አካባቢው የጨዋ ሠፈርና ውካታ የሌለበት እንዲሆንልኝ በማለት ነው ረጋ ያልኩት ። አሁን ያለሁበትን ቤት የወደድኩት ስለ አካባቢው ነው" አሉ ቀኛዝማች ።

"በኔ በኩል ሁለት ቦታ ተገኝቷል ። የሚሻለንን መምረጥ የኛ መብት ነው ። በዋጋም ረገድ የሚጎዳ አይደለም" አለ ሞገስ ኩራ ባለ ድምፅ ።

ከተደጋጋሚ ምክክር በኋላ ጂማ ፣ መንገድ የተገኘው መኖሪያ ቤት የተሻለ በመሆኑ ተገዛ ። በአሠራር ደረጃውም ሆነ በቤቱ ስፋት መጠን ከተከራዩት ቤት ያነሰ ሲሆን ፣ በምድረ—ግቢ ስፋት ግን ይበልጣል ። ዋናው ቤት ከቀይ ጡብና ድንጋይ ፣ የበስተጀርባዎቹ ትናንሽ ክፍሎች ከእንጨት የተሠሩ ናቸው ። የዋናው ቤት ወለል በተላገ ሣንቃ የተነጠፈ ሲሆን ፣ የፊት ለፊቱ ሰበሰብ ግን ፣ በጠጠርና ስሚንቶ ድብልቅ የተስተካከለ ሻካራ ወለል አለው ። ዋናው ቤት ቀለም ተቀባብቶ ከታደሰ በኋላ ፣ የአዲሱ መኖሪያቸው ጐረቤቶችና ጥቂት እንግዶች በተገኙበት ፣ ሰው ሳይበዛና ግብዣ ሳይንዛዛ ቤቱ ተመርቆ ፣ ቀኛዝማች ቤተሰቦቻቸውን ይዘው ገቡ ።

ቤቱ አነስ ያለ ሳሎንና የገበታ ቤት ፣ ሦስት የመኝታ ክፍሎች ፣ ከበስተጀርባም የዕቃና የሽንት ቤት ፣ ሁለት ማድቤቶች ፣ ተጨማሪ የዘበኛ ቤትና የሠራተኞች ማደሪያ አነስተኛ ክፍሎች አሉት ።

በቤቱ መገዛትና በማይደበቀው ወሬ መዛመት ፥ የወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ልብ ከቅናትና ከብስጭት ላመል ታህል ቀንሶ መጠነኛ እፎይታና ተስፋ አገኘ ።

ሸዋርካብሽ እንደ ሌሎች መሰሎቿ ፥ ኑሮዋ ተወስኖና ተስፋዋ ተጭ ለምልሞ የተለመደ አኗኗሯን ስትቀጥል ፥ 'ነገ' እንዲህ እሆናለሁ የምት ልበት ምኞት ጠባብ ነበር ። ምንዳዬ ግን ፥ ቀኛዝማችንና የሞገስን አይዞህ ባይነት ይዞ ነገን እንደሩቅ አዝመራ በተስፋ ይጠባበቃታል ።

ቀኛዝማችና ላቀች ፥ እነሰም በዛ አዳዲስ ነገር እያዩና እያገኙ ነገንም ተስፋ ባለመለመው ስሜት ዘና—ፈካ ብለው ሲጠብቁ ፥ ወ/ሮ ፥ ደጅ—ይጥኑ ግን ፥ በሰሙት ወሬ ሳቢያ እየተበሳጩና በቀኛዝ ማች እግር ማሳጠር እየቀኑ ፥ የነበራቸው ጉራም እየሟሸሸ በመሔዱ ፥ ነፍሳቸው በሥጋት ተከረከረች ።



## ምዕራፍ ዐርባ አንድ

"አንቺ እማምዬ?" አለ አሻጋሪ እናቱ ዘወትር የምታሰማው ተስፋ ባዶ ስለ ሆነበት ፥ "አባብዬ ይመጣል ፥ ይመጣል ስትዪ የታል እሚመጣው? ይኸው ስንትና ስንት ጀን ሆነው እማዶል?"

"ውሸቴን አይደለም አሻጋሪ ። እሱ የሔደበት መኪና ወደዚህ አልተመለሰም ። አባታችሁ እሚመለሰው በሔደበት መኪና ነው ። ነግሮኛል ።"

"አቤት ይቺ እማምዬ ስታሞኝ? ምነው በያ ሰሞን አብዬ ቸር ነት ልብስ ሊገዛልን የወሰደን ለታ ቆሞ አይቼው" አለ ትልቁ ።

"እሱ እቴ! አይ የልጅ ነገር! እምሳያውን አይተህ ነው ፥ እኔም መስሎኝ ነበር ። ሁሉም ቅጠልያ ናቸው ።"

"አይ ይቺ እማምዬ! ምሁኜ ነው እምሳሳተው? በደንብ እየዞ ርኩ አይቸዋለሁ" አለ ኮስተር ብሎ ።

"ምነው ያንተና የወንድምነህ ጫጨቶች ይመሳሰላሉ? በጫጨት አቅም እንኳ እየተሳሳታችሁ ፥ ያቺ የኔ ነች ፥ ይቺ ያንተ አይደለችም እየተባባላችሁ ትጣሉ የለ? ያውም ከጫጨት አቅም —— መኪናውም የዚያ ቢጤ ሆኖብህ ነውቁ ፥ አባታችሁ የሔደበት ተመልሶ አልመ ጣም —— ቢመጣማ—— —" አለች የውስጧን ሣቅ ደማቅ ፈገግታዋ እያጋለጠው ።

"እሱ ታያ መቼ ነው እሚመጣው?" አለ ትንሹ ።

"መሰንበቻውን ይመጣ ይሆናል?"

"እሱ ብቻ ነው ፥ እነ አባባ ቀኛማይም ይመጣሉ? —— እሱ ብቻ በመጣ? — —" አለ አሻጋሪ ።

"ምነው እሳቸውስ ቢመጡ ምን ቸገረህ?"

"እሳቸውማ ተመጡ ፥ ና እንሒድ ተከተለኝ እያሉ ይወስዱታል— ባልመጡ!" አለ በምሬት ።

ልኬለሽ ፥ ይህን በመሰለ ጥያቄ መፋጠጥና መዋሸቱን ለምዳዋለች። ቸርነትም የአፈሣን ወሽመጥ የበጠሰና የምንዳዬን ጥቃት የተወጣ

እየመሰለው አይለያቸውም ። ሁለቱም ልጆች ይከቡና አንዱ ከበስተ ጀርባው ትከሻውን ተደግፎ ፣ ሌላው እግሮቹ መኻል ቆሞ ዐይን—ዐይኑን እያዩ ይላፉታል ። ቦታ ይቀያየሩና ይቀጥላሉ ። አይሰላቹም ። እንኳን የመታቸውን የሰደባቸውን ሲሙቱ ይነግሩታል ።

"አንተ አብዬ ቾርነት ፣ ይኸ ቀማቸው የጋሼ አፈሣ ልጅ ካል መታኋችሁ እያለ ያስፈራራናል ።"

"ለምን ልጄ? ምን አረጋችሁኝ ብሎ?"

"ምንም ታናረገው ፣ እሱ ራሱ ነገር እየከጀለ ነው ።"

"ዝም አላችሁት እንዴ ታዲያ?" አለ ቾርነት ነደድ ብሎት ።

"ይቺ እማምይ የሱን ሳታይ እየተእጣችን ነውዪ —— እሳየው ነበር !" አለ ትልቁ በድጋሚ ።

"ልማታ ብሎ ሲመጣ አቀለጥመውም ኖሯል ? ኧረይታባቱ ! ከነ ካችሁ በሉት!"

"እሱ እኮ አባቱን እያየ ነውዪ እያእተኝም! የቀልድም የምርም ትንታገል እያነሣሁ አፈርጠዋለሁ! — —አባብይ ብሎ ቲጣራ እፈራና እሮጣለሁዪ!— —ሀሀ! አባቱ ከያዙኝ ይለቁኝ መስሎሃል? አንድ ኧን ለታ ብቅ ቲሉብኝ ጊዜ — —" ብሎ ሳይጨርስ ፣—

"እኔ እያለሁ ማባቱ ነው እሚነካህ! ፈሪ ከሆንክማ — —" ከማለቱ ቾርነት ፣

"ምን ታረጋቸዋለህ?"

"እያረገውሚ!— —ካረገውማ እኔ ዐቃለሁ!" አለው ቾርነት ።

"ኧረ ተው እንዲህ — እንዲህ እያልክ የልብ ልብ አትስጠው?" አለች ልኬለሽ ።

" 'ባለቤቱን ካልናቁ ፣ አጥሩን አይነቀንቁ' አሉ ። ልጅኮ የወላጁን ፊት ነው እሚያየው ፣ በኋቸው ይሉ እንደሆነስ ማ ያቃል? " አለ ከንፈሩን ነከስ አድርጎ ።

"እሱማ እውነክን ነው ። የሰው ሰው ሔደው እንዳይተነኩሱ ብዬ ነውዪ !"

"ይቺ እማምይ እኮ ነች ፣ እንዲህ—እንዲህ እያለች እምታስፈራራን" አለ ትንሹ ።



"እናንተም ሳይነኳችሁ አትንኳቸው" አለ ቾርነት የልኬለሽን ፊት እየና ።

"የፈሪ ልጆች ፣ አባታችሁ ሸሽቶ ሔደ እያሉን አደል?" አለ አሻጋሪ በቁጭት ንዴት ።

"አየሽ! አየሽ ይኸን ነገር! ልጅ እኮ አይዋሽም! እነዚያም እቤታቸው ሲወራ የሰሙትን ነው ። የኛ አባት ሸሽቶ አያቅም! — — ውሸታሞች በኋቸው ። ሀ! 'የሳትን ልጅ ገለባ ጉበኘው አሉ!' " ብሎ ተናዶ ወጣ ።

* * *

እርም አይቀሬ ቤተሰቡን ይዞ አንደኛው አዳራሽ ውስጥ ከገባ ሰንብቷል ። አረጋሽ እልፍኙንና ሌላውን አዳራሽ ትዘናከትበታለች ። ቾርነትም ለይስሙላ ቆጡን አጠባብቆ ሰው እያየው ወጥቶ ቢተኛም አካባቢው ጭር ሲልለት ፣ እየወረደ ከአረጋሽ ጋ ማደር ከጀመረ ቆይቷል ። ድርጊቱን ቤተኛ ነኝ ባዩ ሁሉ ከመጠርጠር ዐልፎ ቢያረጋግጥም ፣ አፍ አውጥቶ የተናገረ ፣ ያገባኛል ብሎ "ሃይ!" ያለ ግን አልነበረም ። ቾርነት ቢናገሩት የሚመልስ ፣ ቢቃጡበት የሚማታ በመሆኑ ፣ ሁሉም አፉን ያዘ ። ምንዳዬ ቤትም እንደልቡ መግባት መውጣቱን ፣ ማሳውን ማረሱንና ጠበንጃውንም መቀበሉን የተመለከተው አፈሣ የን ረጥ ይመለከተው ጀመር ።

# ምዕራፍ ዐርባ ሁለት

የቀኛዝማች ኑሮ በተስፋ ተከበበ ፡፡ ጥቅምና ዕድገት ማነፍነፍ ዋነኛው ተግባራቸው ሆነ ፡፡ ምክር ቤቱ ውስጥ ተቀምጠው ሳለ ፣ ከልዩ ልዩ ባለሙያዎች የሚቀርቡ ጥናቶች ፣ ክርክሮችና ተቃውሞዎች ሲነበቡም ሆነ ሲነሡ በሙሉ ልብ አድምጠው አያውቁም ፡፡ አንዳንድ አባላት የሚያቀርቡት ሐሳብና ክርክር ከማናደድ ዐልፎ ፣ "እንዲህ ያሉትን ጋጠ ወጦች ለምን ያስገቧቸዋል ፣ 'ጭሰኛ ተጎዳ ፣ የጭሰኛ ግብር በዛ ፣ ሥራ አጥ በረከተ ፣ ሴት አዳሪነት ተስፋፋ ፣ ሕግና ፍትሕ ተንደለ ፣ የሕዝብ ገንዘብ ባከነ' እያሉ መለፍለፍ ምን ይባላል? ንጉሡ ይኸ ሁሉ ጠፋቸውና ነው? ደህና ዐርፎ የሚገዛውንና ስጥ—ለጥ ብሎ የሚያድረውን ሕዝብ አጓጉል ነገር እያሰሙ አገር ሊበጠብጡብን ነውዴ! እኔ ብሆን ሰብስብ አርጌ ወህኒ ነበር እማጉራቸው" ይላሉ በልባቸው ፡፡

የምክር ቤቱን ጉዳይ ችላ ብለው ወደ ራሳቸው ሐሳብ ሲመለሱም ፣ "ምንጊዜም ራስን ከማስቀደም አለመቦዘን ፣ በማንኛውም ብልሃት እየገፈተሩና እየጐናነጡ ፣ ኑሮን ማቃናትና መካብ እንጂ ፣ ሰዎች ይቀየሙኛል ወይም አያ እንቶኔ ያስብልኛል ብሎ መዘናጋት እያደር መሸርሸርና ፍጻሜ ማበላሸት ነው" የሚለው የአቶ ወርቅነህ አባባል ቀልባቸውን ከመቀስቀስ አልፎ እንደ በቅሏቸው ይዟቸው ይሰግራል ፡፡ ወደ ከተማ ዘግይተው በመግባታቸውም ፣ "ዕድሜ ልኬን ከማንም ኋላ ባላገር ጋር ታረመ እንዴ ተገመሰ እያልኩ ስነታረክና የስልቻ እህል ስቆጥር ፣ እዚህ ስንቱ ግፍንት ሽቅብ ወጣ!" በማለት ይጸጸታሉ ፡፡ ዕድሜያቸውን ሲያስቡትማ ምን ያህል ቀረኝ በሚል ስሜት በንዴት ቢል ይላሉ ፡፡ አእምሯቸው ተረጋግቶ ቀልባቸው ሲሰበሰብ ደግሞ ፣ የፍላጐታቸው ማስፈጸሚያ ፈር በሁለት ይከፈላል ፡፡

አንዱ ፣ ገንዘብና በገንዘብ አማካይነት በሚገኙ ሰዎች በኩል ሲሆን ፣ ሌላው ደግሞ በዝምድናና ባገር ልጅነት ድጋፍ ሊካሔድ የታቀደ ነበር ፡፡ ለመኖሪያ ቤት መግዣ የተከፈተው የብር ማሰሯቸው እያደር አፉ እየሰፋና እየተዘረገፈ የሚከራይ ሦስት ክፍል ቤት ገዙ ፡፡ ፓርላማው ለዕረፍት ከመዘጋቱ በፊትም የሦስት ክፍል ቤት ኪራይ ሲቀበሉ ፣ "እንዴት ተጎድቼ ኖሯል? የማትነጥፍ ላም ማለት ይቺ ነች! ቆይ—ቆይ—ቆይ—ቆይ!" አሉ ፡፡

ጉዳዩ ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱን የማይመለከታቸውና መብታቸውም እንዳልሆነ ሁሉ ፣ ግዢው ሲጀመርም ሆነ ሲፈጸም አልተነገራቸውም ። ሴትዮዋም ቢሆኑ ሰውዬው ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑን ከወሽሙ አንሥቶ ትዳራቸውን ሳይሆን ቅናታቸውን ስለሚያሰላስሉ ፣ "ሀብትና ንብረት ቢበዛ ለኔ ምኔ ነውና የማንም ጋለሞታ ተጋምሳ ልትበላው ለማባቱ ብዬ እለፋለሁ" ስለሚሉ ፣ እንዴት ሆነና ምን ተደረገ ማለቱን ትተውታል ። በዚህም የተነሣ ሞልቶ ቢከነበል ፣ ተጢያጢሶ ቢቃጠል ደንታ አልነበራቸውም ። እንዲያውም ለጣውንታቸው እህል መላኩን ከሰሙ ፣ እሳቸውም በድግስና በጠበል—ጠዲቅ ስም ጐተራ አስከፍተው አጠፌታውን በመዛቅ እልኻቸውን በገዛ ንብረታቸው ስርቆት ሲወጡት ቆይተዋል ። ብሶታቸውን አድምጠ ቁጭቱን ለገለጸላቸው አንዳንድ ተቆርቋሪም እጃቸው ዝቆ ጥርሳቸው ሥቆ ይሸኙዋል ።

ምንዳዬ ፣ የአዲሱን ቤት አትክልት ለማሳመር ዘወትር እንደ ኮትኮተ ፣ ግቢውን በጨፌቃ ቢጤ እንደ ፎከተ ነግቶ ይመሽለታል ። በዚያውም ሐሳብና ብቸኝነት ፣ ትዝታና ናፍቆት በየተራ ይቀራመቱታል ። ያ እንዳሻው ሲዘዋወር የኖረ እግሩ ተሰንክሎ ፣ ያ የሚስት ፣ የልጅና የጓደኛ ፍቅር የለመደ ልቡ በመታፈኑ ፣ ስሜቱ ቀዝቅዟል ። በዚህ ሁኔታ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ስለማያውቅ ሐሳብ ገባው ። ሴትዮዋም ሰው ሲኖር መፍካቱን ፣ ጭር ሲል ፊት መንሣቱን ያውቁበትና ይገለባበጡበት ጀመር ። ሁኔታቸውን የምታውቀው ሸዋርካብሽም ነገሩ ስለገባት ምሳውን አቅርባለት ዘወር ፣ራቱን አድርሳለት መለስ ማለት ጀመረች ። እሳቸውም የምታቀርብለትን ምግብ ፣ የምትቆነጥርለትን ቆሎ አየት ያደርጉና ፣ "እንቺ እንደሁ አሳብ የለሽ ! ቢያልቅ—ባያልቅ አንቺ ምን አሻሽ? ምን አረግሽው ለማን ሰጠሽው እያሉ እሚያንገበግቡኝ እኔን ——" በማለት የሚሰጠውን ምግብ መገመት አበዙ ። ለሱ ግን ፣ አካባቢውን መልመዱ በጀው ። ያቺን ምንም ያህል ያልተቆነጠረላትን የራሱንና የቸርነትን ብር ፣ የከፋው ለት መመኪያ ፣ የራበው ዕለት መተኪያ እያደረገ ተጋደደ ። የኑሮው ማነቆ ግን እያደር ጠበቀ ።

አንድ ቀን ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ፣ ሸዋርካብሽን አስከትለው ዘመድ ጥየቃ እንደሔዱ ፣ ቀኛዝማች ባጋጣሚ ወደ ቤት ይመጣሉ። በተደጋጋሚ የተመኘው ቀን ነበር ። ተከትሎአቸው ገብቶ ስለነበር የቀድሞው ቀኛዝማች አልመሰልህ አሉት ። እየወደዳቸው ፈራቸው ። ሊናገር ያሰበውን ትቶ ሊመለስ ሲል የሚስትዬዋ ፊት ታየውና ከቀኛዝማች ፊት ለፊት ቆመ ። ቀና ብለው በጠያቂ ገጽታ አዩት። ዳሩ ምን ያደርጋል ፣ ይሉኝታና ያልታሰበ ፍርሃት አንደበቱን አፈነው ። የመጣበትን ጉዳይ ትቶ ፣ "አሁን መጣሁ ብለው ነው ከሷ ጋ ወጣ ያሉት ፣ እስታሁንም እቆያለሁ አላሉ ነበር" አለ በልልኝ ያላሉትን በመናገሩ ራሱን እየታዘበ ።



"ቆይታለች?" አሉ በደንታ ቢስነት ።

"ኧረ ጥኢት ነው ቆየት ያሉት ፣ ያጋጣሚ ሆኖ ወጣ ከማለታቸው — —"

"በል እንግዲያው ትንሽ ጋደም ልበል — — ደክሞኛል" ብለው ወደ መኝታ ቤት ገቡ ።

"እስቲ ምን አስፈራኝ? አልቀጠፍኩ ፣ አልሰረኩ ፣ ምን በወጣኝ ነው እንዲህ መሆኔ? ለዚያውም እኮ እንግልቱ ላይቀርልኝ! የሀል—ውሃ ጉዳይ ሆኖ ነውዬ ፣ የትስ ይኖር አልነበር" ብሎ አጠና አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ ተከዘ ።

* * *

ከአንድ ወር በኋላ ሌላ አጋጣሚ አገኘ ። እንደከዚያ ቀደሙ አልፈራም ። "ዛሬስ የልቤን ተናግሬ ይለይልኛል" ብሎ ከቀኛዝማቹ ፊት ቆም እንዳለ ፣

"ምነው ይኸን ሰሞን ደህና አይደለህም እንዴ? ቅር ያለህ ትመስላለህ?" አሉት ትኩር ብለው እያዩ ።

"አይ!—— ለደህንነቱስ ደህና ነኝ" አለ ቅሬታው በፊቱ ላይ እየታዩ ።

"ቅርስ—ቅር ያለህ ትመስላለህ ፣ —— ምን ሆነሃል? ንገረኝ!" አሉት ሁኔታውን እያጤኑ ።

"አንቱም አልተመቸሁ ብዬ ነውዬ ፣ ቅሬታማ ምን ይጠፋል ! እንዲያው ተዛሬ ተነገ እነግርኋለሁ ስል ——" ብሎ አንገቱን ሰበር አደረገ ።

"አትነግረኝም ኖሯል ታዲያ? —— ንገረኝ ምን የቸገረህ ነገር አለ?"

"ያው ስለ ራሴው ችግር ነው" አለ ።

"ምንድን ነው ችግሩ? —— ልጆችህ ናፈቁህ እንዴ?"

"መናፈቅማ የት ይቀራል? በያ ሰሞን ወረኸት አስጥፌ ልኬላቸው ነበር ። እነሱም ወዲህ የሚመጣ ሰው አጥተው ነው መሰል ፣

ሳይልኩልኝ ቆዩና አሁን በእኸደም ለታ የመጡት የማጀቴው ሰውዬ ይዘውልኝ መጡ ። እነሱስ ደህና ናቸው ። ዕድሜ ላንቱ ምንም አላጡ ።”

“ዝም ዝም እኮ ያልኩህ ፣ ወጪ ገቢው ስለበዛና ለሌላ ጨዋታ ስለማያመች ነው ። ሥራ እንደሚበዛብኝ ታያለህ ። ደሞዝም እያሰብኩልህ ነው ፣ ነግሬህ የለ? ጠርቀምቀም ቢልልህ ይሻላል በማለት ነው ። ዐሥራ አምስት ብር ምን አላት? እናት እናቷን ታኳት እልቅ ትላለች ።”

“እረ እኔ መች የሱ ችግር ያዘኝ ፣ እነሱን አለባብሰበት ካገኘሁ ለኔ ምን ይሆነኛ” አለ መሬት—መሬቱን እያየ ። ወደ ዋናው ጉዳዩ እንዴት እንደሚገባ ግራ ገብቶት ሳለ ፣

“ንገረኛ! ምንድነው የቸገረህ?”

“እንዴት ብዬ ልንገርሁ ስል ብዙ ጊዜ ሆነኝ ። አንቱ መቼም የውዴታሁን አርገሁልኛል ፣ አሁንም ቢሆን ያጓደልኩብኝ ነገር የለም ። እኔም አመጣጤ አንቱን ብዬ ነውዴ ፣ ሌላማ ማን አለኝ?”

“እሱንማ መች አጣሁት! — — አሁን የቸገረህ ምንድን ነው? አትነግረኝም ወይ?” አሉ በለዘብታ ።

“እሱማ አመጣጤም ልነግርሁ ነበር — —”

“በላ! በል ንገረኝ — — ምን አስፈራህ?”

“እይ — — እንዲያው ከሳቸው ጋ — —” ብሎ ጥርቅም አለ ። ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱን እንደሆነ ገባቸው ።

“ምነው? ተናገረችህ እንዴ?” አሉ በመጠኑ ቅጭም ብለው ።

“አፍ አውጥተው ባይናገሩም እያደር ነገራቸው አላማረኝም ፣ ተዛሬ ነገ ሆዳቸው ይፈታል በማለት ነበሬ ፣ እንዲህ ፊት ይነሱኛልስ አላልኩም ነበር ። እገዛ ቤታቸው ተቀምጬ ፣ የገዛ እህል ውሃቸውን እየበላሁና እየጠጣሁ ፣ እንዲህ ተሚሆኑ ፣ አንድ መላ ብታረጉልኝ ብዬ ነው። ሰው አፍ አውጥቶ ና ሒድ ተቤቴ እስተሚል ዝም አይባልም ። እኔም አንቱን አይቼ ነበር አመጣጤ ፣ እዚያ ሳስቸግርሁ ኑሬ አሁን ደሞ እዚህ ———” ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ ፣

“ምንድነው የሆንከው? እስቲ ንገረኝ?”

“እእ! እኔማ እንዴት ብዬ ልንገርሁ ፣ የኔን እዚህ መቀመጥ አልወደዱትም ፣ ቀድሞውንም ፣ ያንቱን ፈቃድ ልፈጥም ብዬ ነውዴ ፣ ሆዳቸው ከጎሸ ቆይቷል ። የኔ መምጣት አልተዋጠላቸውም ። ይኸን ወራትማ ላይናቸውም ተጠይፈውኛል” አለ አንገቱን እንደ ሰበረ ።



“ግድ የለህም! አትበሳጭ ፣ ረጋ ካሉ ለማንኛውም ዘዴ አይታጣም ። አንዳንድ ጊዜ እኮ የበደሉንም ሰዎች ፣ እንዳይታወቅባቸው የተገላቢጦሽ ያኮርፉናል ። አንተ ግን ማየት ያለብህ እኔን ነው ፣ ምነው ስንትና ስንት ነገር ስታውቅ! ትዕግሥት ያለው ሰው ጥሩ ነው ። ሰው ብዙ ፣ ብዙ ነገር እየቻለ ነው ለቁም—ነገር እሚበቃው” በማለት ያላሰቡትን ጭምር ተናገሩ ።

“አንቱ እማታኡትና ያልሰማሁት ምን ነገር አለ? የምቀየምማ ብሆን እምቀየመው እኔ ነበርኩ ። ትንፋሼን ያሰነበትኳትና አይዞህ ፀርታ ፣ ማባቱ ይነካሃል ብለሁ ፣ ጥላ ከለላ የሆንኩኝ አንቱ ነሁ ብዬ ፣ የሆነውን ሁላ እርግፍ አርጌ ትቸዋለሁ ። ምንስ ቢሉና ምንስ ቢያረጉ” እንዳለ ሐሳቡ ተማታበትና ዝም አለ ።

“የቤቶችን ነገር ታቀው የለ? ላመል ታህል ትበቃቸዋለች! በሆነ—ባልሆነው ቅጥል ነው እሚሉት ። እኔ ጥፋት ያጠፋሁት ደጅ—ይጥኑን ቅደሚ ብዬ ወደዚህ ማምጣቴ ... በኔ ግምትማ ፣ ይቺ እዚያው እቤቷ ትቀራለች ብዬ ነበር ። እኔ! ይቺኛዋን አስቀድሜ ፣ ያቺኛዋን ‘ሰንበት ብለሽ ነይ’ ብላት ይሻል ነበር ። ዘዴው ተበላሽ ። አንተን ታዲያ ዐይን ህን ላፈር ያለችህ በሌላ አይምሰልህ ። እኔ ዐውቄዋለሁ ። አሁንም እንደዚያው እንዳገር ቤቱ እየመሰላት ነው ። ሞኝነቷ ነውዴ ፣ እዚሁ እጠገቧ ደፋ ቀና ስትል እያየችህ ምን አናደዳት ። እኔ ደሞ ባየሁህ ቁጥር አሳብ የሆነብኝ እንደ ዕውር ድመት እቤት ውስጥ ተጨብጠህ መዋልህ ነውዴ ፣ እንዲህ ያለውን ነገር በምን አስቤው ! እንግዲህ ለማንኛውም እኔ አንድ መላ ፈጥሬ የሆነው እስተሚሆን እንደ ምንም ታገሥ ።”

ቀንበሩ ሳይቀልና ማነቆው ሳይላላ አያሌ ቀናት ዐለፉ ። የተከፈተ እንደበቱ ፣ ካንዴም ሁለት—ሦስቴ አስተዛዝኖ ተናገረ ። ቀኛዝማችም አሳብ ገብቷቸው ፣ “አይዞህ ትንሽ ታገሥ ። ረስቼ አይምሰልህ” እንዳሉና እሱም ‘የምኞቴ ፍጻሜ ምን ይሆን’ በማለት በሐሳብ እንደ ተንገላታ መስከረም ጠብቶ አደይ—አበባ ፈነዳ !

* * *

“ኤዲያልኝ ኤዲያ! እኮ ለኔ ምን ጠቀመኝ! — — ለኔ ምን ፈየደልኝ? እሳቸው ቤት ገዙና ፣ ርስት አገኙና ለኔ ምን ያረግልኛል? ‘ሺ ቢታለብ ያው በገሌ አለች’ አሉ ድመት ። ዞሮ—ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ ነው ፣ ምንስ ቢሆን ማ እንደ ሚስት ማለታቸው አይቀር ። እኔ ነኝዴ ኩቲዋ ፣ ወንድ አምኜ መምጣቴ ! ያን የመሰለ ቤቴንና ኑሮዬን

አዳፍኜ — —" አሉ ወይዘሮ ደጅ — ይጥኑ፣ ቀኛዝማች የከተማ ቤት እንደ ገዙና የገጠር መሬት እንዳገኙ በመደሰት ፈንታ ልባቸው በጥር ጣሬና በቅናት እየተኰማተረ።

"አሁንስ ቢሆን ምን ጎደለብሽ? ዝናብ ሲጥል እኮ ነው ምንጭ በደንብ እሚመነጨው፣ እንዲህ እምትጠራጠሪ ከሆነ በፊት ነበር መጠንቀቅ" አሉ አቶ ወርቅነህ ነገር ሲጀምሩ።

"ምን ጐደለሽ ትለኛለህ እንዴ ጋሼ? እስቲ ምን አገኘሁና ነው ምን ጐደለሽ የምባለው? ይኸን የማጀቴ ባቡር ፈጪ የማያጣውን ዱቄት አገኘሁና ነው ምን አጣሽ እምትለኝ? አበስ ገበርኩ እቴ! ይኸው ይኸ ቤትም፣ ዕቃውም ያንተ ነው። 'ዐይን አይቶ ልብ ይፈርዳል —' ለሳቸው ስል ስንቱን ሲሳዬን ትቼ —— ወይኔ!" አሉ በምሬት።

"እንግዲህኮ የናንተ ነገር ይኸው ነው። እንደ ስብ ቶሎ ትቀልጡና ወዲያው ደሞ ወይኔ—ወይኔ! ምንድነው ባጭሩ መከንዳት? ሰውዬው ስንትና ስንት ነገር አስበዋል። አንቺ ሌላ ነገር ታውጠነጥኛለሽ! እኔስ ምን እሠራ መስለሽ? ላንቺም ቢሆን ብዙ ነገር አስበዋል። እስቲ አሁን ላሚታ የሚያደርስ ምን ነገር ሠሩ? የኖሩት ገጠር፣ ገና እየነጋላቸው ነው። እዚያ ከኔ እኩል ማንም የለ ሲሉ ኖሩና እዚህ መጥተው ሲያዩት ጊዜ በጣም ተበሳጩ። ገና ዛሬ አሐዱ ብለው መጀመራቸውና ያዝኩት ጨበጥኩት እያሉ ነው" በማለት ቀኛዝማች በወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ላይ ያላቸውን እምነት ለማረጋገጥ በውክልና ቢጤ ፈገግ አሉ።

"አንተ አታአቸውም ጋሼ! የዋዛ ሰው መስለውሃል። እኛ ሆድ ለሆድ እንተዋወቃለን፣ አንተ ያየኸው ቆዳቸውን ነው። እእእ! ሞኝ መስለውሃል! እስቲደላደሉና እስቲመቻቹ ነው። የያዙትን ሲይዙ ዐይናቸው ይባከናል። እልህና ይሉኝታ ይዞኝ ነው በዳውላ እህል ዝም ያልኩት። ስሙ ይቢቃኛል እያልኩ አብሬ ኖሬ ዐመላቸውን አጣሁትና ነው?" አሉ የተመኙት ሁሉ በከንቱ የቀረ እየመሰላቸው።

"ግድ—የለሽም በኔ ይሁንብሽ! ትልቅ ግንድ ተፈልጦና ተማግዶ እሚያልቀው ቀስ በቀስ ነው። አንቺ ብልሃቱን ሳታውቂበት እየቀረሽ ነው እንጂ፣ ሚስትዬይቱንስ ማስወጣት መች ያቅትሽ ነበር! እልህ ያለ ብልሃት ምን ያደርጋል?" አሉ መካሪና መሠሪነቱንም እየደባለቁ።

"ሚስት ተብየዋማ፣ አልሆን እያላትና የኔ መድካኒዓለም እየከለለልኝ ነውዪ — — ዋና ተብታቢ መተተኛ ነች፣ እስተዛሬም በመሰንበቴ አገር ጉድ ይላል፣ እሰው ቤት ሔጄ ተሰውጋ ታልሆነ በቀር እንዲች ብዬ አፌ አላረግ! ጋኔኑን ቲያስለፈልፍና እንጨት ቲያስግዘው፣ ውሃ ቲያስቀዳው እሚያድር ዘመድ እደጋው አገር ተንሳው በላይ አላት አሉ። እኔ ላይ ብቻ አልይዝልህ አለው መሰል ይኸው ደህና ነኝ። ሰውዬው እንደሁ አሙን አሙን ሲሉ በምን ያገኛቸዋል። አሽከርዬውም ቢሆን ጥፌት ቢጤ ታይኖረውና የእጅ—ሰብ መከላከያ ሳይቀምስ አልቀረም" አሉ። እሳቸው ግን፣ እዚያው ማጀቴ መድኃኔ—ዓለም በሚያውቁት አንገተ—ብርሌ በሚባል ደብተራ 'በስመ—አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ ጸሎት በእንተ መፍትሔ ሀፍት ወግርማ ሞገስ፣ ወመድግ ወመስተፋቅር፣ መድግ፣ መጥቅ፣ መትፍ፣ አገጽጽያ አለሁማ ጅር—አላጅር፣ መጅር፣ ሰዓቦሙ ወአቅርቦሙ ወአራጎርጎ ልቦናሆሙ፣ አሆ! አሆ! አሆ! ይቤሉኒ ሰበ ከተማ ——' የሚል ጽሑፍ ያለበት ኪታብ በነጭ ፍየል ቆዳ አጽፈው እንደያዙ ልባቸው ያውቀዋል።

"ለማንኛውም እኔ አለሁ — — ይኸ ቀላል ጉዳይ ነው። 'ፌንጣ ብትቆጣ እግሯን ጥላ ሔደች' እንዳይሆን፣ አንድ ደህና ነገር እጅሽ እስኪታገቢ ድረስ መታገሥ አለብሽ። አለበለዚያ ነገር ታበላሻለሽ" አሉ አቶ ወርቅነህ መዘውር፣ የቤትዮዋ ለሁለት ማደር እየቆጫቸውና ለወደፊት አንድ ነገር ማድረግ እንዳለባቸው እየወሰኑ።

ወይዘሮ ደጅ — ይጥኑ፣ በሰውዬው ምክርና ተግሣፅ እየተጽናኑና ተስፋቸውን እያለመለሙ፣ ከቀድሞው በበለጠ ፈገግታና አቀራረብ የልብ ሰለባ ዘመቻቸውን እንደ ተያያዙት፣ ለሳቸውም መስከረም ጠብቶ አደይ አበባ ፈነዳ!

*　　*　　*

የሞገስ አምባቸውና የላቀች ተገኔ ትዳር በሱ ፍላጎትና አስተሳሰብ እየተመራ፣ በሷ ወደ አዲስ አካባቢ መግባትና ሰዎች ባደነቋት ኑሮ ውስጥ መገኘት እየጠነከረ፣ በፍቅር አብቦ በመግባባት ደመቀ። እሱም ባረማመድና ባለባበሷ ከተማ—አደግ እንድትመስልለት እንደ ቀልድ እየመከራት፣ ቀድሞውንም የከተማ ልጅ ለመምሰል ከነበራት ፍላጎት ጋር ተጋግዞ የልቡ እየደረሰ፣ የሷም መላ ወዘናዋ እያማረ፣ የቤት አያያዝንና የእንግዳ አቀባበልን፣ የመኪና ውስጥ አቀማመጥንና የመልስ አሰጣጥን እያወቀችበት የአምስት ወር ነፍሰ—ጡር ሆና መስከረም ጠብቶ አደይ አበባ ፈነዳ!

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱም፣ "አንፏቃቂ ሁሉ አንፏቆ አንፏቆ ቀረዪ፣ እኔስ እልሄን ተወጥቻለሁ" በማለት ራሳቸውን እያጽናኑ፣

በስጨት ያሉ ዕለት ደግሞ ፤ ማር—አምባ ጊዮርጊስን እየተማፀኑ በዘልማድ ሲኖሩ ፤ ሸዋርካብሽም እንዳሏት እየሆነችና ባንዲት ቀሚስ እንደ ተወሰነች ፤ ትበላው ሳትቸገርና ታወራው ሳታጣ ቀኑ ቢገፋም ፤ ከተስፋዋ ይልቅ ትዝታዋ እየበዛ ፤ የመኰብለያ መንገድም እንደ ፈለገች፣ ለሁሉም መስከረም ጠብቶ አደይ አበባ ፈነዳ!

ልኬለሽ ፤ በባለቤቷ ትዝታና ለምኖ ባጸፈው የደብዳቤ ተስፋ እየተጽናናች ፤ ልጆቿንም "ያባታችሁ መምጫ ደርሷል አሉ ፤ የሔደበትም መኪና ተበጅቷል" እያለች ፤ ቤቷ ሳይቀዘቅዝና መብራቷ ሳይደነግዝ ፤ ማሳዋ ታርሶና ቡቃያው አምሮ ባካባቢዋ እንደ ተከበረች ፤ ቸርነትም የባልንጀራውን አደራ እንደ ጠበቀና ከአረጋሽ ጋር የጀመረውን ፍቅር እንዳጠናከረ ፤ በመጨረሻም ምንዳዬ በሦስት ወር ደመወዙ ለልኬ ፤ ለልጆቿና ለቸርነት የላከላቸውን አዲስ ልብስ ለብሰው እንደ ተደሰቱ ፤ መስከረም ጠብቶ አደይ አበባ ፈነዳ!



## ምዕራፍ ዐርባ ሦስት

ቀኛዝማች ፤ የምክር ቤቱን ደንብና የአሠራር ሁናቴ ከዕለት ወደ ዕለት ስለ ለመዱት ፤ እንዴትና በምን ቀላል ዘዴ ሊያስፈቅዱና ያለ ፈቃድም ሊቀሩ እንደሚችሉ በሚገባ ዐወቁ ። እንዲያውም ለሦስትና ለአራት ወራት ያህል ከሥራ ገበታቸው የተለዩ አማካሪዎች ፤ ባሻቸው ጊዜ ሔደው ደመወዛቸውን እንደሚወስዱ ተረዱ።የወ/ሮ ደጅ—ይጥኑንም አንዳንድ ቅሬታ በልዩ ልዩ ስጦታና የማዝናኚያ ተስፋ ሰቅስቀው ጣሉት ። ድርጊታቸውን ሌት ተቀን የሚከታተሉት አቶ ወርቅነህ መዘውር ግን የሰውዬውን ለግል ጥቅማቸው ብቻ መራወጥ አንድ ባንድ ስለ ደረሱበት ለወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ያላቸው ተቆርቋሪነት ተጠናከረ ። የሴትዮዋን በጥበብ ልብስና በሱቲ ጨርቅ መደለል እያዩ ተበሳጩ ። "ለካ ሰው እንዳኖሩት አይገኝም ፤ ቁም—ነገረኛ እየመሰሉ የጊዜ ማሳለፊያ አደረጓት — — ቆይ! ቆይ! ቆይ! ቆይ! " አሉ ቀኛዝማችንም ለመዘወር ። የሰውዬውን ጠባይና ያላቸውን ወዳጅነትም በርጋታ ሲያሰላስሉት ፤ ቀኛዝማች አዳዲስ ወዳጆች ባገኙ ቁጥር ጨሌ እንዳየ በሬ ዘወር እንደሚሉ ታያቸው ። ስለዚህም ሴትዮዋን ቀስ በቀስ አራርቆና አላቆ ሌላ የመተዳደሪያ ዘዴ መስጠት አስፈላጊ ነው እስከ ማለት ደረሱ ። ሐሳባቸው ከንቱ ሆኖ እንዳይቀርም ፤ ትልማቸውን ከጥቅማቸው ጋር በተያያዘ አዲስ ዕቅድ ውስጥ አስገብተው የመተግበሪያውን ስልት ማውጠንጠን ጀመሩ ።

* * *

ምንዳዬ ተስፋው እየጠወለገ፤ኑሮው በምሬትና በብስጭት ተቀነበበ። በቀድሞ ሥራው ላይ የቀኛዝማችን ልጆች ወደ ት/ቤት ማመላለሱም መረረው ። ሴትዮዋም ከግርመማ ወደ ግልምጫ በመሸጋገራቸው አካባቢና ኑሮው አስጠልቶት የትዝታው አድማስ ሰፋ ። ከራሱ ጋር ሙግት ገጠመ ። ሴትዮዋም የሳቸውን እጅና ፊት አይቶ አዳሪ ስለሆነላቸው እልሐቸውን የተወጡና የተበቀሉት እየመሰላቸው ፤ ከመደሰትም የልብ ልብ ተሰማቸው ።

"ምንዳ" ብለው ይጠሩና ፤ "እስቲ አታክልቱን ኰትኩተው፤ ምነው ግቢው ቆሸሸ? ምናለ ጠረግ—ጠረግ ብታረገው፤ ዛሬ ደሞ በሩን ከፍቱን ጥለኸው ወዴት ውለህ መጣህ? ምናለ አንዳንድ ቀን

ጨርቅ አጠባውንም ፣ ቤት ውልወላውንም አገዝ ብታረገን? ዛሬስ ብለህ—ብለህ ቀድመኸን ተኛህ እንዴ?” በማለት ያንገረግቡት ጀመር።

አንድ ቀንማ ሆን ብለው ፣ ያላያቸውና ያልሰማቸው አስመስለው፣ “ምን ጭብጥ ኩርምት ይልብኛል ፣ ኧረ ንሺ እልፍ ይከንዱ! ካልጣመው አይሔደውም? እኔ ናልኝ ብዬ አላመጣሁት? እከከከከከ!” ሲሉ በመስማቱ ፣ “ምናባቱ! ምነው ይህን ያህል መሽቆጥቆጤ! ቢሻው አሞራ ፣ ቢሻው አውሬ ይብላኚ እንዲህ ሆኜስ አልዘልቀውም” ብሎ ለመጨረሻ ጊዜ ቀረጠ ።

ቀኛዝማችን ለማነጋገር አጋጣሚ አልጠበቀም ። “እኔ እንግዲህ” አላቸው ግቢው መኻል ቆመው ወጉ እንዳይቀር የአበባ አትክልት ሲመለከቱ ። “እኔ እንግዲህ እያው አገሬ ልመለስ ፣ አለያም አንድ መላ ፈልጉልኝ ። እስተመቼ ሰው አስቸግሬ እዘልቀዋለሁ?” አለ የበጠቃትን ቅጠል እያልመዘመዘ ።

“የረሳሁ እይምሰልህ ፣ የሰው እጅ እማያሳይ ፣ ደህና ሥራ እስኪገኝልህ ብዬ ነው ። ለደህና ደህና ፍሬ ሰዎች ነግሬልሃለሁ ። ሁሉም ተስፋ ሰጥተውኛል ። እኔማ ከኔጋ ብትኖር ደስ ይለኝ ነበር ። ከሚስትና ከልጆችህ ነጥዬ ያመጣሁህም ——” ብለው ሳይጨርሱ ፣

“እኔስ እየሁ እንቱጋ መኖሬን መች ጠላሁት? ችግሩ ———”

“ያንተን መቸገር አጥቼው መሰለህ ። ካይንና ከግንባርህ ነው እማቀው ። ከኔጋ ወጥተህ እንዲሁ አገርህ አትመለስም ። ትልቅ ሐሳብ የሆነብኝ ደግሞ ፣ ሥራው ቢገኝስ እማንጋ ይቀመጠዋል እያልኩ ነው” ብለው የቀዘዘ ፊቱን ትኩር ብለው አዩት ።

“ኧረ የትም አስጠጉኝ ብዬ አድራለሁ ! ለለት ወስፋቴ ታገኙሁ ይበአኛል’ አለ አቀርቅሮ ። ‘እሳቸውን አስደስት ብዬ መንፈሬ ለምንድን ነው” እያለ በልቡ ።

“ግድየለህም ፣ አነሰም በዛ እንዱ ጋ አስቀጥርሃለሁ” አሉት ተስፋ ባለው ፈገግታ ።

“ተዚያ ሁላ ውለታና ቁም—ነገርሁ አይበልጥ ። እኔም የዕድሌ ነገር ሆኖ ነው መሰል ፣ ሁለዜ እንቱኑ እንዳስቸገርኩ ነው” ብሎ ከነገራቸው እያሌ ቀናት አለፉ ።

* * *



መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ፣ ምንዳዬ ሽማግሌ ልኮ ከባላንጦቹ ጋር እንዲታረቅና የደም ማድረቂያ ወጀ ከፍሎ አገር እንዲቆረርለት (የተወሰነ የመኖሪያ ክልል) መኮይ ሽፍቶች መኖሪያ ድረስ ሁለት ጊዜ መልዕክተኛ ልከው ካስመጡት በኋላ ፣ ዞን አምባ ድረስ ሔደው የሚያስታርቁ ጉምቱ ሽማግሌዎች ለመኑ ።

ነገሩ የቆየና ሥር የሰደደ በመሆኑ በጥንቃቄ ተመከረበት ። መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ጉዳዩን በብልሃት ይዘው ከአካባቢው አብያተ ክርስቲያናት ፣ ተሰሚነትና ታዋቂነት ያላቸውን መነኮሳትና ቀሳውስት አዘጋጁ ። ከካብ ሥላሴ አባ ተክለ—አብን ፣ ከከላይ ጊዮርጊስ መምሬ ማርዬን ፣ ከውቢት ሚካኤል አለቃ ዘነበን ፣ ከዞን አምባ ተክለሃይማኖትና ከየገልዳ ኢየሱስ መምሬ በየነንና አባ ምንውየለትን ለሽምግልና ሲያዘጋጁ ፣ በአካባቢው የተከበሩትን ቀኛዝማች በላይነህንም ለዚሁ ጉዳይ አማከረዋቸው ፣ እሳቸው በወቅቱ ባጋጠማቸው የርስት ክርክር ጉዳይ ስላልተመቻቸው ፣ በምትካቸው የገምዛ ወረዳ ጸሐፊና እንዲሁም የወረዳው ዳኛ እንዲገኙላቸው በማድረግ በዕርቁ ላይ ከፍተኛ ሚና የሚያሳድሩ ሰዎች ወከሉ ። የሁለቱ ባለሥልጣኖች በሽምግልናው መግባትም ዕርቅና ውሉን ሕጋዊ መሠረትና ጥንካሬ ሰጠው ።

ምንዳዬ ይህችን ሁሉ አንጠርጥሮ ያውቃታል ። ስለዚህም በማንኛውም ረገድ ቢሆን ፣ ቀኛዝማችን የሚያስቀይም ድርጊት ለማሰብ ሕሊናው ይጨነቃል ።

ሞገስ የምንዳዬን የገጠር ኑሮና የነበረበትን ችግር ከገዛ ባለቤቱና ከወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ፣ እንዲሁም በሥራ ፈልግለት ሰበብ ከራሳቸው ከቀኛዝማች አንጠርጥሮ በመረዳቱ ፣ በሚያውቃቸው ሰዎች በኩል የዘበኝነት ሥራ ሲያጠያይቅለት ሰንብቶ ነበር ። ተስፋው አጎነቆለ ።

ምንዳዬ ወገገለት ።

ቀኛዝማች የሥራውን መገኘት እንደሰሙ የት እንደሚቀመጥ ሐሳብ ሆነባቸው ። ከወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ጋር እንዳይቀመጥ ፣ አቶ ወርቅነህ መዘወር የሱን ለቀኛዝማች ማድላት ስለሚያውቁና ከውጥናቸው ውስጥ አንዳንድ ወሬ ሊያቀብልብን ይችላል በማለት ስለሰጉ ፣ ለሁሉም ያሰቡ በመምሰል ፤

“እሱን የሚያህል ሰው ብቻዋን ከምትኖር ሴት ጋር ፣ አብረህ ተቀመጥ ማለት ያልታሰበ ችግር ያስከትላል ። ሰው ነውና ከብዙ ቀን አንድ ቀን ሊሳሳት ይችላል ። ምነው ስናውቀው ፣ ሴት ሆነን ባናየውም በወንድነታችን እናውቀዋለን ። ሥጋ ያሳስታል ። ሌላ እነስ

ያለ ቤት ቢኖረን እንኳ ምንም አልነበረም ፡ አለበለዚያ ግን እሱንም አስገድዶ ለስህተት መዳረግ ይሆናል" በማለት የማጨናነቃ ሐሳብ ስለጋረጡ ፣ ሌላ ቦታ መፈለግ የግድ አስፈላጊ ሆነ ።

ከቀኛዝማች ጋር ወዳጅነቱን በማጠናከር ላይ የነበረውና ለላቀች መገኘት እንደዋነኛ ምክንያት የሚመለከታቸው ሞገስ አምባቸው ፣ ችግሩን እንዳወቀ ፤ "ማደሪያማ ምን ይቸግራል ? ይህን ችግር ነው ብለው አያንሱት ። እኔ ጋ አለ" ብሎ ሲገላግላቸው ፣ ቀኛዝማች "ውቢት ሚካኤል ሰው ተመስሎ መጣ መሰል" ብለው ደስ አላቸው ።

ላቀች ሁለት ወር የሆነውን የበኩር ልጅዋን አቅፋ ስታጠባ ፡ ምንዳዬ የዘበኝነት ሥራ እንደተገኘለትና ለጊዜው እነሱ ዘንድ መጥቶ እንደሚቀመጥ ባለቤቷ ፈገግ ብሎ ሲነግራት ፤ ካንጀት ተደሰተች ። "እንዳንድዬ እንኳ እሚያነጋግረኝ ያገሬ ሰው ታገኘሁ ጥሩ ነው" አለች በልቧ ። የእናቷ አገር ዞን—አምባ በመሆኑ ዘመዷም ጭምር ይመስላታል ።

"መቼ ተገኘለት! እንኳንም የተገኘለት ፡ የሱ ነገርስ ያጸድቃል ለነፍስህም ቅልቅል ነው ፣ ሴትዮዋ አካይስት ቢጤ ናቸው አሉ ። መቼም የሰውዬው ነገር ሆኖበት ነወዪ ፡ እንደ ሴትዮዋ ባሕሪስ ፡ እንዲች ብሎ እግሩን አያነሣም ነበር አሉ ። ከጭቅጭቁም እፎይ ይላል — — ደግ አርገሃል ።"

ምንዳዬ ሥራ እንደተገኘለት እንደሰማ ፡ ቀን በልቡ እንደፈነጠዘ፡ ሌሊት እንቅልፍ ባይኑ ሳይዞር ነጋ ። ሞገስና ቀኛዝማች በላይነህ ፡ ምንዳዬን አስከትለው ወደተገኘለት የዘበኝነት ሥራ ቦታ ለመሔድ ሲነሡ ፣ እእምሮው በደስታ ሰከረ ። መኪና ውስጥ ፡ እነሱ ከፊት ፡ እሱ ከኋላ በመቀመጡ ተጨንቆ እንዳቀረቀረ ፡ ሠንጋ ተራ ደረሱ ። ወለል ብሎ ከተከፈተው የብረት በር አናት ላይ "የካርሎ ቤርናርዲኒ ጋራዥ" የሚለውን የማስታወቂያ ቅስት አልፈው ወደ ግቢ ገቡ ። ምንዳዬ የቀድሞ ልብሱን ቢለብስም ዱላውን አልያዘም ። ከመኪና እንደወረዱ ከበስተኋላቸው ቆሞ ፡ በምስቅልቅል ስሜት ይበረግጋል ። ሁኔታው ባይገባውም ተጨነቀ ። "ምናባቱ! ያፈቀደው ይሁን! ከሰው ዝግን የራስ ጎመን ይበልጣል" አለ በልቡ ።

"ሰላም! ታይዳስ! እመጣችሁ? ይኸ ኖው ያ ሰውዬ ያላችሁ ?" አለ በብረታ—ብረት ቅባት ማሰሻ የመሰለ ቱታ የለበሰው ግንባረ—ፈጣጣና ጸጉረ—ሉጫው ሕድሩ ወደነ ሞገስ እየመጣ ። ረዘም ፡ ቀጠን ያለ መልከ—መልካም ነው ። ግራ—ቀኝ ቅንጡና ሺፋሉ ላይ ተቆርቋል ።



ሕድሩ በገራገር ፈገግታ ተቀብሎ በቅባት የተጨማለቀ እጁን አንሥቶ ፣ አንገቱን ሰበር በማድረግ ሰላምታ ሰጣቸው ። እነሞገስም ካንገታቸው ሰበር ፣ ከፊታቸው ፈገግ ብለው ሰላምታ ሰጡት ። ምንዳዬ ቀጥ ብሎ ቆሞ ሁሉንም በየተራ ያያል ። ሕድሩ የጋራዥ ሠራተኞች ተቆጣጣሪና የሥራው ዋና ኃላፊ ሲሆን ፣ እሱ የወደደው ሠርቶ ፣ የጠላው ይሰናበታል ። አብዛኛውን ጊዜ በቀላል ጉዳይ ፈጥኖ ቢቆጣም ፣ ቶሎ ይበርዳል ። ግልጽና ቅን ፣ ሥራ ወዳድ ነው ። ነገር ማዞር አይሆንለትም ። ሠራተኞች ሲለግሙም ሆነ ሲሰንፉ ካየ ፣ ተናዶ ስለሚናገር ያቺው የሚያውቃት አንዳንድ ያማርኛ ቃላት ትጠፋበትና ፣ የስድቡን መዓት በትግርኛና በጣሊያንኛ ያዥጎደጉደዋል ።

ገና ከልጅነቱ ጀምሮ አብሮው ባደገችውና ካፉ በማትጠፋው የጣሊያንኛ ስድብ ፣ "ፊሴ ዲ ካኔ" ሲል ተግ ይልለታል ። ቀደም ሲል የሚያውቁት አብሮ አደግ የአሥመራ ባልንጀሮቹ ፣ "መንከሽከሽ!" ይሉታል ። ባንዳች ምክንያት ተበሳጭቶና ሠራተኞቹ ላይ አንባርቆ ዘወር ሲል ፣ "ዛሬ መንከሽከሽ ተነሥቶበታል ፣ ሲንከሸከሽ መዋሉ ነው" ይላሉ ። አንዳንዶቹ ምን እንደሚሉት የሰከሩ ዕለት ይነግሩታል ። እሱ ታዲያ "ፊሴ ዲ ካኔ! ለቄማየት!" ብሎ ዝም ይላል ። ቶሎ ቂም አይዝም እንጂ ከነከሰ አይለቅም ።

የሞገስ መኪና ስትበላሽ የምትጠገነውም ሆነ አዲስ ዕቃ የሚቀየርላት ፣ ሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ ጋራዥ ነው ። ሲኞር ካርሎ የመንግሥት ባለሥልጣንና ሹማምንት መተዋወቅ ስለሚፈልግ ፣ ለሚጠግኑላቸው የግል መኪናዎች የዋጋ ቅናሽና ፣ ለቀላል ብልሽትና ስንክልም እስከ ነጻ ግልጋሎት ይሰጣል ።

ሞገስ መኪናውን ባስጠገነና እንዲሁም በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ከሕድሩ ጋር በተገናኙ ቁጥር ስለሚገባበዙ ፣ ተግባብተው ወዳጅ ሆነዋል ። ሕድሩ ሲጋብዝ ልክ የለውም ። "ምስታይና ካልቀረ ብደንቢ አድርገን ንጠጣ" ማለት ያበዛል ።

"አንቱም በዓል—ሥልጣን ናቸው ፣ እኛ ምን አሎና ? መሸኪን ለራእሳችን" ሲለው ሞገስ ልቡ ፍርስ እስኪል ይሥቃል ።

ሕድሩ እነሞገስ ፊት ቆሞ ሲታይ በሰው ቁመት ልክ የተጠቀለለ ማሰሻ ይመስል ነበር ።

"ጌና ከሀገረ—ሰብ የመጣ እንግዳ ኖውን" አላቸው ትናንሽ ዐይኖቹ ጭምር እየፈገጉ ።

"ከመጣስ ቆይቷል ፣ ብቻ" ብሎ ሞገስ ንግግሩን አንጠልጥሎ ተወው ።

"ከመጣ ስንት ጊዜ አደረገ?" አለ ምንዳዬን ከወደ ጐን እያየ ።

"ዓመት አልፎታል" አለ ሞገስ ፈጠን ብሎ ።

"ማኬ! ይኸም አገር ለምዷል ማለት ኖው —— ድንቂ !"

"ብዙ ወጣ—ወጣ አላለም እንጂ ፣ ለሥራስ ትጉኅ ነው" አሉ ቀኛዝማች ምንዳዬን እያዩ ።

"እዚህ እኛ አሎና በቀላል ይለምዳለ ፣ ዋና እሚፈለግ ያለ ነገር ከሱ ፣ እሙን ሰው ምኳን ቢቻ ኖው ። ላይ የሚያሸግር ነገር የለም ።"

"ስለሱ ግድየለም ፣ ለሚያደርሰው ማንኛውም ጥፋት ተጠያቂና ኃላፊ ነን" አሉ ቀኛዝማች ኮራ ብለው ።

"ድንቂ ! የሱ ሥራ ብጣዕሚ ቀሊል ኖው ፣ እንተኾነም ምጥንቃቕ እስፈላግ ኖው ።"

ምንዳዬን ፣ ልዩ ልዩ የመኪና ቅባቶች ፣ የነዳጅ—ዘይቶችና የብየዳ ጢስ ሽታ አወከው ። ሕድሩ ፣ እነ ሞገስንና ምንዳዬን አስከትሎ ወደ ግቢው በር በመሔድ ፣

"ይኸ ኖው እሱ ይጠብቅበታል አቦስቶ ፣ የሥራ" ብሎ ዙሪያዋን በቆርቆሮ የተሠራች አነስተኛ ቤትና እበሯ ላይ የቅባት እባሽ የጠገበች ገዳዳ አግዳሚ አሳያቸው ። የምንዳዬን ባዶ እጅ መሆን አይቶ ፣ ገባ ብሎ የባሕር ዛፍ ዱላ ካወጣ በኋላ ፣ አገላብጦ አይቶ ሰጠው ። እጅ ነሥቶ ተቀበለ ።

"አይዞሃ ፣ የሚሸግረካ ነገር ዘበለ ፣ ለኔ ትነግረኛል!" ካለ በኋላ እነ ቀኛዝማችን ተሰናብቶ ወደ ሥራው ተመለሰ ።

ሞገስ ፣ "እንግዲህ ነቃ ነቃ ማለት ነው ። አይዞህ ። ሁሉም የለ መደው እንዲህ እንዲህ እያለ ነው ። በል በርታ ! ያቅትሃል እንዴ ?" አለው ።

"ኧረ አያእተኝም ፣ ይኸ ደሞ ምኑ ያእተኛል" አለ ምንዳዬ ዱላውን በጥንቃቄ ጨብጦ ።

"በል እንግዲህ አይዞህ! አጅሬ እንኳን ለዚች !" ብለው ቀኛዝማች እየፈገጉ ተሰናበቱት ። ምንዳዬ ሆዱ ባባ ። ዐይኑ ቃበዘ ።

የጋራዡ ግቢ ሜዳ ጠጠር ፈሰስ ሆኖ ፣ በልም የመኪና አቧራ ርጋፊና ጥራጊ ፣ በቅባት ዝቃጭና ፍሳሽ ተለዋውሶ በመደምደሙ ፣ ቅጥራን ያፈሰሱበት ይመስላል ። ምንዳዬ ወለል ብሎ በተከፈተው



በር በኩል ወጪ ወራጁን እየት ያደርግና ፣ እንደገና ወደ ግቢ ዘወር ይላል ። እንዴት ዐይነቶቹ ሰዎች ሲመጡ እንደሚያስገባ ለማወቅ አሳብ ያዘው ። "በምን አቃቸዋለሁ ፣ ይግቡ ወይ ብዬ እጠይቅ እንደሁዴ" አለ በሐሳቡ ።

ሠላሳ ያህል የሚሆኑት የጋራዡ ሠራተኞች ፣ በየተመደቡበት ሥራ ዓይነትና አካባቢ ተፍ—ተፍ ይላሉ ። ቅጥቀጣና ብየዳ ፣ እጣባና ጥገና ፣ ቅብና ሞተር ፍተሻ ይሠራሉ ። ምንዳዬም የዚያ ኑሮ አካል በመሆኑ አንዲት ኦፔል ሬኮርድ የቤት መኪና እየተገፋች ወደ ጋራዡ ልትገባ ፊቷን ወደ በሩ ስታዞር ፣ ዱላውን ይዞ ጠንቀቅ አለና ልክ በሩ ጋ ስትደርስ ፣ ኮስተር ባለ አነጋገር ፣—

"ቆይ! ቆሙ! ታይፈእዱላችሁ አትግቡ! መጀመሪያ ልጠይእላችሁ" አለ ።

ማንም ነገሬ አላለው ። ከቁም—ነገርም አልጻፉት ። የመኪናዋ ከፊል አካል የበሩን ደፍ እንዳለፈ ፣ ነጂው ራሱን በመስኮት ብቅ አድርጎ ፣ "ምንድነው እምትለው ?" አለው በሲጋራ የበለዘ ዝርዝር ገጣጣ ጥርሱን እየገለፈጠና ጨምዳዳ ማጂያታም ፊቱን ይበልጥ እያ ጨማደደ ።

"ልጠይእላችሁና ነው እምትገቡት ነው ያልኹት!" አለ ቁጣ—ቁጣ እያለው ። እየሣቁበት ገቡ ። የምትገፋውን መኪናና ሰዎቹን እያየ ነደደው ።

"ቢተዋወኡ ይሆናሊ ፣ እንዲያው ያለ ብላት ሰተት ብለው አይገቡ" አለ በግምት ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ሕድሩ እየሣቀ ሲመጣ ፣ ቀጥ ብሎ ቆሞ ጠበቀው ።

"ማኪና ይዘው ሲመጡ ሳለ መግባት አይትከልከላሸው ፣ ሀዲሽ መሆንካ አይተው ኖው የሣቁብኽ ። አጀኻ ! እንተ መንም መንገደይና ልግባ ሲለካ አይታስገባ — ተረዳኸ?" አለው በሚያግባባ ፈገግታ እያየ ። ሕድሩ የተናገረው አማርኛ ግር ቢለውም ፣ ነገሩ ስለ ገባው "እሺ ! ማ አስገባቸው አለህ እንዳትሉ ብየ ነውዴ ፣ ሌላውስ አይጠፋኝም" አለ ምንዳዬ ። ሕድሩ ተመልሶ ሲሔድ ትክ ብሎ አየውና ፣ "እምኑ ውስጥ ዶሎ ቢለውሰው ነው ልብሱ እንዲህ አሙካ የመሰለው ? ያሸታተቱ ! ስባትላብ ጌታዬ!" ብሎ ቅልብሽ እያለው ተቀመጠ ። ቀስ በቀስ ስሜቱ ተረጋጋ ።

አሻግሮ ወደ ሠራተኞቹ ሲመለከት ፣ የሕድሩን ዓይነት ልብስ ለብ ሰው ከመኪና ሥር የተንጋለሉና እናት ላይ የወጡ ፣ ዙሪያውን እየ

ታከኩና አቀርቅረው የሚሠሩ አየ ። ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች ከቆሙት መኪናዎች መካከል ፣ አንዳንዱ ከወደ ኋላው ቂጡ ተገልቦ ሌላው ሽንት እንደ ሸተተው ወደል አህያ ከወደ ፊቱ ምንጭሩን ሽቅብ እ—ኝ! አርጎ ፣ ሌላው ከሥሩ የብረት ዘነዘና ጉማጅ ተመርኩዞ ፣ የቆመና የተጋደመ ፣ የተቃናና ፣ የዘመመ ፣ የብረታ—ብረትና የዕቃ እንክትካች ቁልል አይቶ ተገረመ ። ከየው ሁሉ በጣም ያስደነቀው ግን ፣ እንደ መብረቅ እየተብረገረገና የእሳት ፍንጥቅጣቂ እየረጨ የሚንተገተገው ነገር ነበር ። “ምኑን ይሆን እንዲህ የሚያረጉት ጌታዬ?የሰማዩን ላይ ነገርዮ በምን ይዘውት ይሆን? እንዲያው ይኸን ነገር ለማየት አብቅቶኛ” እያለ ሲገረም ፣ ድንገት አንድ ነጭ ሚሌቼንቶ የሚነዳ ጸጉረ—ስስ ሸበቶ ፣ አፍንጫው እንደ ጎራዴ የቆመ ፣ ዘንጋዳ የመሰለ ፊተ—ሸካራ ፈረንጅ እፊቱ ድንቅር ሲልበት ፣ ድንግጥ ብሎ በንቃት ቆመ ። በወጉም ሳያየው ዝም ብሎ ገባ ።

የጋራዡ ባለንብረት ሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ ነበር ። ፈረንጁ ከመኪና ወርዶ ወደ አንድ ክፍል ሲገባ አየውና ጸጉሩ ቆመ ። ተመልሶ ቁጭ ከማለቱ አባቱ ትዝ አሉት ።

‘ዱሮ ካባቴ ጋ ካራቶሪ የተደባደበው ፈረንጅ ፣ የዚህ ዓይነቱ ነው መሰል’ አለ በልቡ ። እናቱ ወይዘሮ ማንጠግቦሽ እንኳታቸው ቅጥል የመሰለ መልከ—መልካም ነበሩ ። ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረች ባመቱ “ቆሪ ገበያ ጨርቅ ጥንቡን ጥሏል አሉ” ተብሎ በመወራቱ፣ አቶ ቦጋለ ባለቤታቸውን ወይዘሮ ማንጠግቦሽን አስከትለው ካራቶሪ ገበያ ይወርዳሉ ። ልብስ በያይነቱ ተጠቅልሎና ተበትኖ ይታያል ። ባልና ሚስቱ ያይን ዐዋጅ ይሆንባቸውና ፣ “እኔ ተዚህ ታቡዝዲው ይሻለኛል ፣ - - አንቺ የትኛውን ትመርጫለሽ ?” ይሏቸዋል ።

“አንተ ደህናውን አይተህ ምረጥልኝ ፣ እኔማ ምኑን አቀዋለሁ” ይላሉ ሚስት ። ባልና ሚስቱ እየዞሩ ሲመርጡ ፣ አመዳይ የመታው በርበሬ የመሰለ ጸጉረ—ዝንጀሮ ፊተ— ጉርብርብ ፈረንጅ ገበያተኛውን ቆሞ ያያል ።

ልብሱ የወታደር ይሁን የሲቪል አይታወቅም ። አብረውት በካሚዮን የመጡ ሁለት ባንዶች ገበያ ገብተው የራሳቸውን ጉዳይ ያከናውናሉ ። ጣሊያኑ እግር—ጥሎት ጨርቅ ተራ እንደ ደረሰ ፣

“ቤኒኳ!ሲኞራ!” አለ በእጁም እየጠቀሰ ። ምን እንዳለ ማንም አልገባው ። ሰዉ ሁሉ በፍርሃት ፣ በጥርጣሬና በጥላቻ አየው ።

“እንዴት አባቱ ሰው ቢንቅ ነው ፣ ብረት ሳይዝ እንዲህ ሚጎማለለው?” አለ አንድ ገበያተኛ ።



“ባንዶቹ ታጥቀውለታል ፣ እነሱን ተማምኖ ነው” ብሎ መለሰለት ሌላው ። የምንዳዬ እናት ሰዎቹ ያሉትን ቢሰሙም ነገሩ አልገባቸውም ። የአቶ ቦጋለ ዐይን ከጨርቅ—ጨርቅ ይንከራተታል ። ፈረንጁ በትዕቢትና በትምክህት ሰዉን እየገረመመ ሲራመድ ፣ አብዛኛው ከንፈሩን እየነከሰ ገለል አለ ። በቀጥታ ሔዶ የወይዘሮ ማንጠግቦሽን ተርፋሳ ክንድ ያዝ አደረገና ፣ በቀኝ እጁ መጀመሪያ ጉንጫቸውን ጫን ነካ ፣ ቀጥሎም ቂጣቸው ላይ ቸብ አደረጋቸው ። ሴትዮዋ ለጊዜው ደንገጥ ካሉ በኋላ ፣ “ልእእ ! ቅሌታም ! የሰው ቅሌታም !!” ብለው ሊመነጭቁት ሞከሩ ።

አቶ ቦጋለ ዘወር ሲሉ ፣ አንድ ፈረንጅ የባለቤታቸውን ክንድ ይዞ ‘በልቀቀኝ አለቅም’ይታገላሉ ። ከመቅጽበት በቁጣ ጋዩና ፣ እንደወትሯቸው “ዘራፍ!!” ብለው የፈረንጁን ጉሮሮ ሰቅዘው ያዙት ። አካባቢው ታመሰ ። የጣልያኑ ዐይን ፈጠጠ ። አቶ ቦጋለም አጠበቁ ።

“አንቺ ጥፊ ! አንቺ ተየህ ግድም ወግዲ !!” አሉ ከግድንግዱ ፈረንጅ ጋር ቁልቁል እየወረዱ ። ጣሊያኑ እንደ ምንም ተወራጭቶ ጉሮሮውን አስለቀቀ ። “በይፍራታ መንገድ ሒጂ!” አሉ ጮክ ብለው። ከጣሊያኑ ጋር ዐፈሩ ላይ ያህያ ውድቂያ እየተንደባለሉ ጸጉሩን ጨምደው ያዙት ። አንድ ሁለቴዬም በደህና ቡጢ ደሰቁት ። በመኻሉም በአመልካችና በትልቁ ጣታቸው መኻል በወጣው ያውራ ጣታቸው ጠንካራ ጥፍር ምት ፊቱን ስለ ጓጉጡት ደማ ። እሱም ያንኑ ያህል ደህና አድርጎ መደወታቸው ። እየተገለባበጡ ሲንከባለሉ ፣ ኢጣሊያዊው ወታደር ገልብጦ ከላይ ፊጥ አለባቸው ። “ኧረ አንድ በሉልኝ ! ኧረ ገላግሉልኝ !” እያሉ ዙሪያውን ሲዞሩ የቆዩት የምንዳዬ እናት አንድ አነስ ያለ ድንጋይ አንሥተው ሲወረውሩና ድንገት አቶ ቦጋለ ሲገለብጡ አንድ በመሆኑ ፣ ትካሻቸው ላይ አቀመሷቸው ። ወዲያው ሌላ ድንጋይ አንሥተው አሻቅቦ እያየ የሚታገለውን ፈረንጅ ራሱ ላይ አቀመሱት ። ምቱ ባይጠነክርም ደሙ ቡልቅ በማለቱ የተጎዳ መሰለ ። አቶ ቦጋለ ተስፈንጥረው ተነሡ ። ሰውዬው ግን የዋዛ ሰው አልነበረም፣ ወዲያው ተነሥቶ አቶ ቦጋለን ለመያዝ ሲወራጭ ፣ የወደቀ ዱላቸውን አንሥተው ቀኝ እጁን ቀሸመዱት ። ወገቡን ፈታተሸና ፣ “ማማሚያ!! ዲስክራሲያቶ !!” ብሎ አንባርቆ ፣ “ሶልዳቲ! ሶልዳቲ! ቦርኮ !!” አለ። ባንዶቹ ርቀው ሔደዋል ።

“ሰውዬ አምልጧ! ምን ያቆምሃል! እየሁ ነው መስቀልክን ብሎ ሬሳህን እሚያሰጣው! አላየም መሰል በያ ሰሞን!!”አለ አንድ ገበያተኛ ።

“መንገድ አሳክረህ ጥፋ!” አለ ሌላው ።

አካባቢው ተሸበረ ። የጨርቅ ተራ ነጋዴ ጓዝ—እክቱን ሰብስቦ ፥ "አንድ ፈረንጅ ተፈነከተ እሉ!" እያለ ከፊሉ ሩጫውን ተያያዘው ።

"ማባቱ ሲለቀው! የሰው ፈረንጅ አስፈንክቶ! ደሞ በሱ ዳፋ!" አለ አንዱ ከየትም ።

"ማባቱ ሲነኻው ! የማ ወገን መሰለህ?" አለ ሌላው ከሌላ አቅጣጫ ። በግርግሩ መኻል አቶ ቦጋለ ሚስታቸውን አስቀድመው ተፈተለኩ ። ጣልያኑ ማንን ከማን እንደሚለይ ግራ ገባው ።

የምንዳዬ አባት ባለቤታቸውን አንዱ ቤት አስገብተው እሳቸው ወደ ደሴ በሚወስደው መንገድ በሸሁ—እምቡሬይ ድንጋያማ ቁልቁለት ሲሮጡ ፥ ዘልለው ያረፉበት ቋጥኝ በመንገበሩ ግራ እግራቸው ታጥፎ ወደቁበት ። እንደ ምንም ተነሥተው ለመሔድ ቢሞክሩ ቁርጭምጭሚታቸው ክፉኛ ተቀጥቅጦ በመውለቁ መላወስ ተሳናቸውና ጥሻ ውስጥ ተሸጎጡ ።

በዚያው መነሾ አንካሳ ሆኑ ። ምንዳዬ የዚያን ዕለቱን ታሪክ ከአባቱ ፥ ከፍ ካለም በኋላ ከእናቱና ከሌሎች ሰዎች ሰምቷል ። ማጀቴ ግቢ ያያቸውን ፈረንጆች ፥ "እነዚህ ጣልያን አይደሉም" ስላሉት ጥርሱን ነክሶባቸው ባያውቅም ፥ ጣሊያኖችም እነርሱን እንደሚመስሉ ግን ዐውቋል ።

"ምነው አንድ ጣልያን አግኝቼ ፥ ቀልጥሜ—ቀልጥሜ በለቀኩት! ወይ ነዶ!" ይላል ያባቱ ነገር ትውስ ሲለው ።

ቀኛዝማች በዘመነ አርበኝነት ፈጸምኩ የሚሉትን ጀግንነት ሲያወሩ ፥ ምኞቱ በሳቸው ድርጊት ውስጥ ይሠርፅና የሰማውን ያከናወነው ይመስል ደስ ይለዋል ።

ምንዳዬ ካርሎ ቤርናርዲኒን እያስታወሰ ፥ "ጣልያን የ ሚሉት የዚህ ዓይነቱን ሰው ይሆን?" አለ ከትዝታው መልስ ።

ሠራተኞቹ ለምሳ ሲወጡ ፥ የምንዳዬን የዱላ አያያዝና ጠንቃቃ አቋቋም እያዩ ሲያልፉ ፥ አንዳንዶቹ " አ!አዲስ ባለ ቁምጣ !" ሲሉ ፥ ሌሎች "ገና እንግዳ ነው ፥ የመጣበት ዜታዎ ገና አልተራገፈም "እያሉ ሲወጡ ፥ አረማመዳቸው ፈጠን ፥ አነጋገራቸው ጮክ ያለ ነበር ። ምንዳዬ ሕድሩ በላከለት ሻይና ዳቦ ዋለ ።

ሠራተኞቹ ከምሳ ሲመለሱና ምሽት ላይ ሲለቀቁ ቆሞ አሳለፋቸው ። በሕይወቱ የመጀመሪያዋ ልዩ ቀን በዚህ ዓይነት አዋዋል ስትፈጸም ፥ ሞገስ 12 ሰዓት ላይ ምንዳዬን ወደ ቤት የሚወስደው ሰው



ልኮለት ስለነበር ፥ መመላለሻውን መንገድ በደንብ እያሳየ ይዞት ገባ ። እቤት እንደ ደረሰም ባልና ሚስቱ ፥ እንዲሁም ቀኛዝማች ሲቀበሉት ፥ ጐንበስ ብሎ እጅ ነሣ ። አሁን ገና ከሰዎች ጋር የተቀላቀለ መሰለው ።

እጁን ታጥቦ የላቀች ሠራተኛ ያቀረበችለትን ምግብ ሲበላ ፥

"እህ ?! እንዴት ነው ? ትለምደው ይመስልሃል ?" አሉት ቀኛዝማች አንድ ሁለቴዬ እንደ ጎረሰ ።

"እንዲህ እንደ ዛሬው ከሆነ አያእተኝም ቀላል ነው"አለ እያላመጠ።

"አይዞህ በርታ! የከተማ ሰው ነቃ—ነቃ ይወዳል ። እኛም አደራ ብለነዋል ። ይረዳሃል " አለው ሞገስ ። ከሌሎች ቤተሰባዊ ጭውውቶች በኋላ ፥ ቀኛዝማች ምንዳዬን እውጪ አስጠርተው ፥ አበረታቱና ፥ "ደመወዝ እስኪሰጡህ ቀን— ቀን በምሳ ሰዓት እንዳይቸግርህ" ብለው ዐሥር ብር ሰጥተውት ሲሔዱ በጣም ደስ አለው ።

የበሯ የታች ማጠፊያ የተገነጠለው እዲቧ የምንዳዬ መኝታ ቤት ከግራ ከቀኝ ማድ ቤትና ዕቃ ቤት አማክለዋታል ። ዐልፎ ዐልፎ የተቆፋፈረ ወለሏ ውሃ ተርከፍክፎበት ተጠርጋለች ። በታጣፊ የሸራ አልጋ ላይ ፥ ሽማውና አመድማ ብርድ ልብሱ እንደነገሩ ጣል ተደርገዋል ። የቀን ውሎውና የተሰጠው የመኝታ ክፍል ስሜቱን ስላመሳቀሉት ፥ ሳይበላው እንዳከከና ሳይቆረቁረው እንደ ተገላበጠ ነጋለት ።

ከሊሴ ገብረ—ማርያም ትምህርት ቤት በስተምሥራቅ ፥ ራስ ናደው ሠፈር ውስጥ ከሚገኘው ከሞገስ መኖሪያ ቤት እስከ ጋራዡ ያለውን መንገድ ሁለት ሦስቴዬ ካሳዩት በኋላ እንደልቡ መመላለስ ቀጠለ ።

ሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ የምንዳዬን አቀጣጠርና ያመጡትን ሰዎች ካወቀ ወዲህ ፥ በምንዳዬ በኩል አክብሮትና ውዴታው እንደሚተላለፍለት በመገመት ፥ በገባና በወጣ ቁጥር አየት ያደርገዋል ። ምንዳዬ ፈረንጁ የጋራዡ ባለቤት መሆኑን የሰማው ግን ፥ ከአዳሪው ዘበኛ ነበር ።

ኢጣልያዊነቱን እንደ ሰማ ሰውነቱን ወርር ቢያደርገውም ፥ "ይኽ ደህናው ጥልያን ቢሆን ነውዬ ፥ ቀኛማችም አይጠሉት ነበር ፥ አጅሬ እንዲህ ዋዛ !" ብሎ ራሱን ሸነገለና ፥ "እኔውም ሞኝ ነኝ ፥ እስቲ የሰው የሰብስቴ ጊዜ ፈረንጅ የት አገኘው ብዬ ነው መናደዴ? የኔ አባትንኳ ከሞተ ይኸው ስንትና ስንት ዘመኑ" አለ ከሕሊናው ጋር ሲመክር ።

ምንዳዬ የድካሙን ዋጋ አገኘ ። ከትልቅ መዝገብ ላይ ባውራ ጣቱ ፈርሞ የመጀመሪያው ወር ደመወዙን 25 ብር ሲቀበል ፣ በጣም ከመገረሙ የተነሣ "ተሳስተው ይሆን እንዴ" ብሎ ደግሞ ደጋግሞ ቆጠረው ።

* * *

የምንዳዬ ባላሰቡት ሁኔታ ለቆ መውጣት ለወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ የምሥራች ሆኖላቸው ስለ ሰነበተ ፣ "አንድ ማኢድ ወደቀ!" አሉ በሸዋርካብሽ ፊት ። አይበጁኝም ከሚሏቸው መካከል አንዱ ካይናቸው በመገለሉ ፣ አካላቸው ዘና ፣ ሕሊናቸው ቀና ማለት ቢጀምርም ፣ አንድ የተለመደ ጥርጣሬ ግን በአእምሯቸው ውስጥ እንደ ውሃ አዟሪት መሽከርከሩን በመቀጠሉ ፣ "ይኸንዬኮ እኚህ ስንስኒያም ሰውዬ ሥራዶየዋለሁ እያሉ እዚያቹ ጋለሞታቸው ጋ አስቀምጠውት ይሆናል ። ዐይኔ ብቻ አይያቸውዬ እኔ ምን አሻኝ ፣ እዚያው ተሰባስበው ይግማሙ" ይላሉ ። ሐሳባቸው ፈጥኖ ይለዋወጣል ። በአንድ እምነትና ምክንያት ላይ ጸንቶ መሰንበት ይሳናቸዋል ። የአንዳንድ ምክንያት ጠንቅ ደግሞ አእምሮ ውስጥ ሥር ሰዶ ስለሚደረጅ ፣ በቀላሉ አይነቀልም ወይም አይጐለሰስም ። ስለዚህም ፣ ቂማቸው የማይፋቅ ፣ በቀላቸው የማይቃለል ይሆናል ።

* * *

ሞገስ እምባቸው ፣ ከቀድሞዎቹ ሁለት ሚስቶቹ ፣ በመልክና በቁመናዋ የላቀች ፣ ያሳዩዋት የማይጠፋት ፣ የነገሯት የሚገባት ሚስት በማግኘቱ ፣ 'ጣመኝ—ድገመኝ' እያለ ኑሮውን ተያይዞታል ። "እንዲት ያልተማረች ቂል ባላገር አግብቷል አሉ ፣ ሰው ቢጤውን እያጣ" እያሉ የዱሮ ሚስቶቹ የነዙትን አሉባልታና ወሬ ከጆሮውም አልጻፈውም። ለሱ እንከን የለሹ ናት ። እንኳንና ዛሬ እንዲህ ብዙ ነገር ዐውቃና ነቃ—ነቃ ብላ ቀርቶ ፣ ያኔዬ ገና ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ዘንድ ሳለችም ፣

"ነይ እንሒድ እኔ ቤት ደርሰን እንምጣ?" ሲላት ፣

"ሆ! ኧረ ምን አረግ!—— ደሞ መዘዝ ዱሉኛ" ብላ ስታፍር ፣ "ቶሎ ደረስ ብለን እንመልሳለን — —" ብሎ ሲያባብላት ፣ "እኔ እምቢኝ ፣ የሳቸው ነገር አይታወቅም — —እግሬ ወጣ ከማለቱ ቢሉኝስ" ስትለው ፣ "የሔዱት እኮ በጣም ሩቅ ቦታ ነው ፣ ሳይመጡ እንመለሳለን ምንድን ነው እጉል መግደርደር!? ነይ እንሒድ" ብሎ አባብሎ ሲወስዳትና መኪናው ጋ ደርሶ በሩን ከፍቶ ሲገባ ፣ እሱ በገባበት በር በኩል የምትገባ መስሏት ቆማ ስትመለከት ፣ ቶሎ ብሎ



እጐኑ ያለውን በር ሲከፍትላት ፣ የበሩ ደፍ ቅልጥሟን ፣ ጉበኑ ራሷን ገጭቷት ፣ ጭንቅላቷን ትክሻው ድረስ አስቀድማ ገብታ ፣ ቀሚሷን ሳትሰበስብና ሳታስተካክል ፣ ወንበሩን ሳትደገፍ ቀጥ ብላ ተቀምጣ ፊት ለፊት ስታይና ፣ ፍሬን ሲይዝ ወደ ፊት ስትሽቀነጠር ፣ እንዲሁም እቤቱ ገብታ ያየችው ልዩ ልዩ ዕቃ ብርቅና ድንቅ ሆኖባት ፣ "ይኸ ምንድን ነው ፣ ያ ምን ማረጊያችሁ ነው? — —" ስትል በነበረበት ጊዜም ቢሆን ፣ ለሞገስ ዐይን ፣ ፍላጐትና ልብ ሙሉ ነበረች ።

አሁንማ ከጊዜ ወደ ጊዜ መልክና ደም—ግባቷ እንደ ለም መሬት አዝመራ እያማረና እንደ መስከረም አደይ እያበበ ፣ የአካባቢውን ሰዎች አኗኗር ፣ አለባበስና አቀራረብ እየለመደች ፣ ልጁም ታይታ የማትጠገብ ያተር እሸት ፍልፍል መስላለት ፣ ሞገስ አሉባልታውን እንኳስ ቢኮራና ቢደሰት ምን ይጐድለዋል ?

ጊዜ እንደ መስኖ ውሃ እየፈሰሰ ፣ ቀናት እንደ ናዳ ድንጋይ እየተንደረደሩ — — ምንዳዬ ፣ ሞገስና ላቀች ፊታቸውን ሳያቀጭሙብትና የቤተሰብ ስሜት ሳይለየው ፣ እጃቸው እንደ ተዘረጋና መዓዳቸው እንደ ሞላ ከአምስት ወር በላይ ቢቀመጥም ፣ አካላቱ በስቅቅታ ተበላ ። ቀኛዝማች በሔዱ ቁጥር "እንካ እስኪ ይቺን ለሻይህ" እያሉ የደጎሙትንና ከደመወዙም ያጠራቀማትን ይዞ 'ሰው ከማስቸገር ወደ ራሱ ቁራሽ መዞርን' መረጠ ። እንዴት ብሎ እንደሚናገር ደግሞ ግራ ይገባዋል ። ይሉኝታ ይፈታተነዋል ። መንገድ ለመንገድ "ዛሬስ እነግራታለሁ ፣ እኔ ሌሎቹን ነውዬ ላኧችንስ አልፈራትም—እነግራታለሁ" ብሎ ይዘጋጅና እቤት ሲገባ ደግሞ ፍርሃት ይተናነቀዋል ።

አንድ ቀን ግን ፣ "ዛሬስ ምንም ቢሆን እነግራታለሁ ፣ ብቻዋን ብቻ ባገኘኋት" ብሎ ገባ ። ሳሎን ውስጥ ፎቴ ወንበር ላይ ተቀምጣ ከልጅዋ ጋር ስትጫወት ደረሰ ። ከፊት ለፊቷ ተቀምጦ ያሰበውን ሁሉ እጠር አድርጎ አማከራት ።

"ባየኸው ሲወድህና ሲራራልህ? እሱ እኮ ይኸን እንደ ውለታ አይቆጥረውም" አለችው ።

"ሰው ተየህ በላይ ምን ውለታ ይውላል? የናትም ልጅ አያረገው ።"

"ምን አረግንልህና? ለዚህ ለማደሪያው ነው ፣ ለባዶው ቤትዮ" አለችው በፈገግታ ።

"ዋ — እቴ ሆዬ! እኔን ሆነሽ ባየሽው እንዳልልሽ ደግሞ አዶል! ይህን ያክል ወራት ማ ያጋድዳል? ሳይበርደኝ — ሳይርበኝ — ሳይጠማኝ — የሰው ፊት ሳይፈጀኝ — —"

"ላንተ ተብሎ አልተጋገረ? ለሞተ እንጀራ ምን ቁም — ነገር አለው ብለህ ነው? ይኸንዬኮ — — ተሳቀህ ነው፣ አይ ያንተ ነገር" ብላ በአዘኔታ አየችው ።

"ቢሆንም! — ዋ — ላኧች! በየህ ባንድ ዓመት ዕድሜ፣ ስንቱን ያየሁና የታዘብኩት መሰለሽ? አሁን፣ አሁን፣ እያደር ለመድኩቲ ባየ ሽኝ ነበር እምረግጠውን መሬት ስፈራው! ዋ ካገር መውጣት፣ ዋ የሰው አገር ሰው መሆን! የዱር ዐውሬ ይብላኝ እንዳልኳቸው፣ ፈጣሪ አምላህ እናንተን ሰበብ ባይጥልልኝ፣ እንዴት እሆነው ነበር? እስቲ በይ ማን ነው? 'ይቺን አፍህ አድርጋት' ብሎ ደበቅ እርጎ እሚያጎርስ? 'እስቲ በይ ማነው ቤቱን ጠራርጉለት እያለ አይዞህ በርታ የሚል ሰው'" አላት ሆዱ እየባባ ።

"አንድ ነገር የተናገርንህ ይመስላቸዋል ። እሳቸው እንደሁ ጥቂት ይበቃቸዋል ። ለማንኛውም እስቲ ሰንበት ቢልና — —" አለችው ውዴታን በሚገልጽ ቃና ።

"የሳቸው አይቸግርም፣ ቀስ ብዬ እነግራቸዋለሁ ። ቀኑ ሲበዛ ጊዜ ጭንቅ አለኝ ። ሌላው ቢቀር ወስፋቱን እንኳ ብችል ብዬ ነውዴ—" አላት አንገቱን ሰበር አድርጎ ።

"እንዲያው ተሳቀቅ ቢልህ ነው! — — ማታ ስትገባ መኪና አጥበህ፣ አታክልት ኮትኩተህ፣ ምን ላግዛችሁ ብለህ ነው ። ኧረ መቼ ቀን ቂጥህ መሬት ነክቶ ያቃል?" አለችው በቅንነት ።

ጊዜ እንደ መስኖ ውሃ እየፈሰሰ፣ ቀናት እንደ ናዳ ድንጋይ እየተንደረደሩ — — —

ምንዳዬ ሰንበትበት ብሎ፣ ሠንጋ ተራ አካባቢ የሱ ቢጤ ባለ አነስተኛ ደመወዝ ሠራተኞች የሚመገቡበትን ምግብ ቤት ሁኔታና አካባቢ፣ የሚከፈለውንም የገንዘብ መጠን ነገራቸውና፣ ሆዱን ከውጪ አድርጎ፣ ማደሪያ ብቻ እንዲረዱት ባልና ሚስቱን በለዘብታ አዋያቸው ። መሳቀቁ ስለ ገባቸው ሰንባብተው ፈቀዱለት ።

እሱም፣ ሥራውንና አካባቢውን እያደር ስለ ለመደው፣ እንግዶች ሲገቡ መርቶ ቦታ ማሳየትን፣ ደንበኞች ከሆኑ ያለ ጥያቄ በፈገግታ ማሳለፍን ዐወቀበት ። ሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒም፣ "ኬሽቶ ብራቦ!" በማለት ንቃትና ትጋቱን ወደደለት ። ሕድሩም ያለቃውን አስተያየት ተንተርሶና፣ የነሞገስን አደራና ጉትጎታ ለመወጣት፣ "አንቴ በጣም ሥራህ ትወዳል፣ ታከብራል ። እኔውን እንዳንቴ የአመሰለ ኀበዝ ሰው እወዳሎ ። ከዛሬ ጀሚርካ ለመካኒኮሽ ኪያቤን ዕቃን አቀባሊ ሆንካ ትሠራል" ብሎ ወደ ጋራዥ ክፍል ተላላኪነት አዛወረው ።



# ምዕራፍ ዐርባ አራት

መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ፣ ወደ አዲስ አበባ የመጡበትን ጉዳይ አጠናቀው ሣር—አምባ እንደ ተመለሱ፣ ምንዳዬ ለባለቤቱ የላከላትን የከተማ ጥበብ ቀሚስና ኩታ፣ ለልጆቹና ለቸርነት የሰደደላቸውን ሙሉ ሙሉ ልብስ ሰጥተው፣ ለሳቸውም የገዛላቸውን ካኪ ኮት አሳይተው፣ ሁሉንም ካስደሰቱ በኋላ፣ የወሰዱትን ደብዳቤ ለማንበብ ቢሞክሩ፣ የሆሄያቱ ነባር ቅርፅ የተቀየረ ይመስል፣ ያንዳንዶቹ ተጥመልምሎና ተቆልሞ፣ አጥሮ ወይም ረዝሞ ሲያገኙት፣ "ይኸ ደሞ ማ እሚሉት ፊደል ይሆን?" በማለት ንባባቸውን ሲያቋርጡ፣ አንባቢውም ሆኑ ሰሚዎቹ ከተባለው ነገር አንዱም ሳይያዝላቸው 'ይድረስ' የ'አይድ ረስ' ያህል እየተነበበ አለቀ ።

ቄሱ የመስተንግዷቸውን በልተውና ጠጥተው ወጣ ከማለታቸው፣ ልኬለሽና ቸርነት ልጆቹን ይዘው ወደ አካባቢው 'ራቦር' ጸሐፊ ቤት በረሩ ።

ከትከሻው ጠበብና ከጭንቅላቱ ተለቅ ብሎ ወፈርፈር ያለው 'ራቦር' ጸሐፊ፣ ከቤቱ ደጃፍ ሰበሰብ ላይ ተቀምጦ አገኙት ። ከቆሸሸ ልብሱ ጋር ከሩቁ ላየው፣ በጅምር የቀረ ድብኝት ይመስላል ። የለየለት ስካራም ነው ። ያው ስካሩ የኑሮውን ፀሐይ አሽቆልቁሎ የሕይወቱን ገመድ አሰለሰላት ። በስከረ ቁጥር፣ ካለቃ እስከ ምንዝር፣ ከባለጉዳይ እስከ አጃቢ የሚያገኛቸውን ሰዎች ሙልጭ አድርጎ ስለሚሳደብ፣ አቤቱታ ያስለቻቸው የወረዳ ገዢዎች በጸፉበት የማስጠንቀቂያና የቅጣት ብዛት ሲገመገም የሚሻሻልና የሚታረም ሰው ሆኖ ባለመገኘቱ ከሥራ ተሰናብቶ፣ የማጀቴና የአካባቢው መንደሮች ልዩ ልዩ ማመልከቻዎች ጸሐፊ ሆኖ ይኖራል ። አብዛኛውን ጊዜ ካገሩ ከሣር—አምባ አይወጣም ።

እነ ልኬለሽ ደብዳቤውን ሰጥተው ከፊት—ለፊቱ ተቀመጡ ። "ለውድ ባለቤቴ ለልኬለሽ፣ ለልጆቼ ለአሻጋሪ እና አጥላባቸው፣ ለውድ ጓደኛዬ ለቸርነት፣ እንደምን ከርማችኋል? እኔ በጣሙን ደህና ነኝ፣ እስከ ዛሬ ድረስ መጥቼ ያላየኋችሁ፣ ገና ባለመመቻቸቴ ነው ። ሥራ መያዜን ከዚህ ቀደም አስጥፌላችሁ ነበር ። ፈቃድ ስጡኝ ብዬ እንዳልመጣ ገና አዲስ ሠራተኛ በመሆኔ ነው ። ሁለዜ ከሐሳቤ አትለ

ዩም ። ቀን በውኔ ሌት በልሜ ትታዩኛላችሁ ። በጣም ናፍቄአችኋለሁ ። እንደ እህልና ውሃ ነው የራባችሁኝ ፣ የጠማችሁኝ ። የሚያሠሩኝን ሰውዬ ፣ በሰውም ቢሆን አስለምኜ ፈቃድ ካገኘሁ ፣ ላንድ ቀን ጀምበርም ብትሆን መጥቼ አያችኋለሁ ። ስለኔ እንዲች ብላችሁ አታስቡ ፣ አይዟችሁ ፣ ጥቃት አይግባችሁ” የሚለው እንደተነበበ የልኬለሽ ዐይኖች አጤዙ ። ምራቋን ዋጥ አድርጋ ዐይኖቿን ከደን ስታደርጋቸው ጤዛው ኩልልታ ሆኖ ወረደ ። ፍቅር ፣ ምንዳዬ ፣ ትዝታ ፣ ም — ን — ዳ — ዬ ። የሷ እንባ ሳያባራና ፣ ቸርነት ዐይኑን ወረቀቱ ላይ እንደ ተከተለ ፣ ልጆቹ ሁሉንም ተራ — በተራ እንዳዩ ደብዳቤው ተነቦ አለቀ ።

ልኬለሽ ደስ ብሏት እንዳገራ እንደ ሸንኩርት ውሃ ምንጭ እንባዋን ለቀቀችው ። ቸርነት ደብዳቤውን ላነበበላቸው ሰውዬ ፣ “እስቲ ይቺን ለውሃሁ አርጓት” ብሎ ሐያ ሳንቲም ጨበጥ አደረገለት ።

እነ ልኬለሽ ተያይዘው እቤታቸው እንደገቡ ፣ በሉ እንግዲህ ተሳሳሙ ተብለው የታዘዙ ይመስል ፣ በልኬለሽ ጀማሪነት ተሳሳሙ ። ልጆቹ በደስታ ፈነደቁ ።

“ይህን የዛሬውን ደስታ ማ ያገኘዋል ?” አለች ዐይኗ እንባ እያረገዘ ።

“እስቲ እሱ ለራሱ ምን አለውና ነው እንዲህ ማረጉ ? በሰው አገር እየተንከላፈተ?” አለ ቸርነት ።

“የሱን ልብ ማ ያገኘዋል? እንዳይከፋን ብሎ ነው ። እነዚያ እነዚያ እምናአቸውንም ደስ አይበላቸው ብሎ ነው — ዋዛ መስሎሃል! ምንም ብሆን አለሁ ማለቱ ነው” አለችው ።

“ያጣንና የተቸገርን ይመስለው ይሆን እንዴ? መርሳትማ በየትኛው አንጀቱ ይረሳናል? ምንስ ቢሆን ሚስትና ልጅ አይረሳ!?” አለ ቸርነት ለቀልድ ያህል እየሣቀ ።

“መስሎሃል! ሚስትነቴን አትይ! ተኔ አስበልጦ ነው እሚወድህ ። እንዲህ ወረኸት መላኩ ቃልቀረ ፣ አሁን ምን አለበት እሱም እንደቀኛማይ ፣ ያን ኮቶግራፍ ሚሉትን ተነሥቶ ቢልህልን ፣ በትንሿ ትበአን ነበር ፣ ይኸ ትልልኡ ለሹምቹ ነው መሰል?” አለች እየፈገገች ።

“እስቲ ደሞ ሰንበትበት ብለን እምናየውን በምን እናቀዋለን ። አቦ የሱ ሥራ!” አለ እየሣቀ ።

“ይኸ አባብይ መይ እመጣለሁ አለ እማምይ?” አለ አሻጋሪ የለበሰውን ጐመኔ ካኪ እያየ ።



“ቲነበብም አልሰማህ እንዴ ሽታዬ ? መሰንበቻውን እመጣለሁኮ አለ” ስትል እንባዋ ወረደ ።

“ይቺ እማምይ ደሞ! ያልሰማሁ መስሎሻል? ምነው እያሃች ሆነን አብዬ ቸርነት ነግሮኝ!”

“ምን ብዬ ነገርኩህ አሻጋሪ ?ፈቃድ ቲሰጡኝ መጥቼ አያችኋለሁ ብሏል ነው ያልኩህ!—አለያም እኔና አንተ ሔድ ብለን እናየዋለን!” አለ የምሩን በሚያስመስል አንደበት ።

“አቤት ይኸ አብዬ ቸርነት !!”አለ እየሣቀ ።

* * *

ቸርነት ፣ የራሱንና የባልንጀራውን ማሳ እያረሰ ፣ ልኬለሽና ልጆችዋ ሳይቸገሩ ፣ ጐተራዋ እንደ ሞላና ገበታዋ እንደ ከበደ ፣ ምድጃዋ ሳይቀዘቅዝና ማንም ወስላታ ቀና ብሎ ሳያያት ፣ ታፍራና ተከብራ ተቀምጣለች ።

አፈሣም ቢሆን ልቡ አላረፈም ። ምንዳዬ ባልታሰበ ቀን መጥቶ ጉድ እንዳያፈላበት እየሠጋና ውስጥ ውስጡን እየፈራ ፣ ከነቤተሰቡ እጃቸውን ሰብስበው አፋቸውን ከርክመዋል ።

መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ፣ ለምንዳዬ ቤተሰብ የወሰዱት ደብዳቤና ልብስ ፣ እጥፍ በእጥፍ ተጨማምሮበት ፣ ያልተባለው እየተባለና ያልተዛተው እየተዛተ ፣ ወሬው ውሎ ሳያድር ጃራን ተሻግሮ ዞን—አምባ ዘመተ ። ልኬለሽ ይህን በመስማቷ ፣ “እንዲህ እያሳመሩና እየጨማመሩ ያውሩለታ!” ብላ ካንገቷ ቀና ፣ ከልቧ ዘና አለች ።

ቸርነትም የሚወዱት እንዲያደንቁለት ፣ የሚጠሉት እንዲያዩለት ፣ ምንዳዬ የላከለትን ሙሉ ልብስ አዘወተረው ። አንዳንድ አሽሟጣጮችና ነገረ— ሠሪዎች ፣ “የሎሌነቱን ፣ የሚስትና የቤት ጠባኢነቱን ፣ ጥብቆ ቢጤ ገዝቶ ላከለት ። ዋል አደር ብሎ ሚስቱን ቲቀማው ተጐኑ ያገኘዋል ። ‘ነፈዝ ባል የሚስቱን ውሽማ ይቀልባል’ እሚሉ ተረት ለካ አለትም አዶል?” እያሉ አስወሩ ። አሉባልታው ግን ፣ ከእርሱ በፊት ስንትና ስንት ጊዜ እየተወሩ እንደ ሞቱት አሉባልታዎች ሁሉ ፣ በየዕለቱ እየማቀቀ ሞተ እንጂ ፣ እንደ አንዳንድ ሽምድምድ ውሸቶች እንኳ ፣ የአሚሚት ወግና ግናዝ አልደረሰውም ።

የልኬለሽ ፣ የልጆቿና የቸርነት መንፈስ ግን ፣ በሚታፈስ እውነትና በምንዳዬ ይመጣል ተስፋ እየለመለመ — —ጊዜ እንደ መስኖ ውሃ እየፈሰሰ ፣ ቀናት እንደ ናዳ ድንጋይ እየተንደረደሩ — — — ፍቅር ፣ ምንዳዬ ፣ ትዝታ ፣ ናፍቆት — — — — —ልኬለሽ — — — ምንዳዬ — — እነአሻጋሪ —— ቸርነት — — —

# ምዕራፍ ዐርባ አምስት

ምንዳዬ ፣ ሠዐረ ተስፋ ጋብር የሰጠውን ያገለገለ ሰማያዊ ቱታ
ለብሶ ከወዲያ ወዲህ ሲል የቆየ ሜካኒክ ሠራተኛ መሰለ ። በመጀመሪ
ያው ወር የልዩ ልዩ መፍቻዎችና የመኪና ዕቃዎች ስም አልያዝህ
እያለው አያሌ ቀናት ተቸገረ ። "ኪያቤ እንግሌዜ ፣ ፒንሳ ፣ ካቻ ቢቴ ፣
ላሜራ ፣ ሮታ ፣ ቺንጊያ ፣ ቻርኪዮ ፣ ክሪክ ፣ አሊዮ ፣ ባሌስትራ ፣ ኮሎ ፣ ራዲ
ያቶሪ ፣ ኪያቨ ትሬዲቺ—ኪያቪ ኳቶርዲቺ ፣ ኪያቬ—ዙንዲቺ — —ሌባ
ጎማ—"እያሉ ሲልኩና ሲጠይቁት መላ ቅጡ ይጠፋዋል ። በጥቆማ አሳ
ይተውት ያቀረበውን ነገር ለይቶ ለማወቅ ፣ ቅርፅና መጠኑን ትኩር
ብሎ እያየ የዕቃውን ስም በልቡ ደጋግሞ ይጠራል ። አንዱን መፍቻ
"ዙንዲቺ ይባላል" ብለው አሳይተውት ከሆነ ፣ ያንን ዙንዲቺ ፣ ዙን
ዲቺ ዙንዲቺ በማለት ላይ ሳለ ፣ እንደገና "ፒንሳ ፓፓጋሎ!"ሲሉት፣
በሆዱ ፣"እምኑ ጣጣ ውስጥ ገባሁ ወንድሜ !አንዱን ሲሉት ሌላው፤
ይሉና በአካባቢው ያገኘውን መፍቻ ሁሉ ሰብስቦ ፣ "ተየሀ መኻል
ትመርጡት ይሆን?" ብሎ ያቀርብላቸዋል ።

"ፒንሳ—ፓፓጋሎ ማለት ይኸ ነው" ብለው ነጥለው ያሳዩታል።
እንደገና እንዳይጠፋው ስሙን ሲደጋግሙው ፣ "ቢንሳ አባጋሎ" እስከ
ማለት ይደርስና ፣ በመኻሉ ደግሞ ፣ አንዱ ሜካኒክ ሌላ መፍቻ ሲጠይ
ቀው አዲሱን ስም ሲያሳድድ የመጀመሪያዎቹን ይዘነጋቸዋል ። በተ
ለይም አንዳንድ ቀልደኛና ተረበኛ ሠራተኞች የምንዳዬን የዕቃዎች
ስም አጠራር ሲሰሙ ከት ብለው ስለሚሥቁበት ፣ ውስጥ—ውስጡን
ይናደድና የቀልድ መሆኑ ስለሚገባው ፣ እሱም ሣቅ እያለ ሥራውን
ይቀጥላል ። መቼም ይሁን መቼ ፣ አብዛኛው ሠራተኛ ፒንሳን ፣ ቢንሳ ፣
ቪቴን ፣ ቤቴ ፣ አልዮን ወልዮ— — — ሲልና የተባለውን ትቶ ያልተ
ባለውን ዕቃ እያቀበለ የተማረ በመሆኑ ፣ የምንዳዬ መሳሳትና መደና
ገር ያስከተለው ሣቅም ወዲያው አባርቶ ይረሳል ።

የሠራተኞች ቅንና የዋህ ልብም እንደ እንግልቱ ቆዳቸው ድድር፣
እንደ መጃው መዳፋቸው ሻካራ ሳይሆን ፣ እንደ ብርሃን ጨረር ሠርፆ
የሚዘልቅና እንደ ላባቸው የሚንቆረቆር የወንድማማችነት ባሕሪ ሰን
ሰለትነት አለው ። ምንዳዬም ከቅን ልቦናቸው እውነትን ፣ ከንጹሕ ሕሊ
ናቸው መተሳሰብና ፍቅርን ፣ ከግልጽ አንደበትና ልግስናቸው ፣ መቀ

ራረብና መተዛዘንን ቀሰመ ። ከመሰንበትም የገጠር አነጋገርና ግት ርነቱ እየተሻሻለ ፣ የሠራተኞችን ባሕሪና ሁኔታ መላበስ ጀመረ ። የልዩ ልዩ ዕቃዎችንም ስም ፣ ቀድሞ እንደሚያውቃቸው ሞፈርና ቀንበር ፣ ድግርና ወገል ፣ ዋልታና ምሰሶ ፣ መንሽና ላይዳ—ከማወቅ ዐልፎ አን ዳንድ የሚሠሩ ነገሮችን ፣ ማጠባበቅና ማላላትን ፣ መቆራረጥና ማቃ ናትን ፣ ቀስ በቀስ ለመደ ። ቀድሞውንም በእርሻና በተጨማሪ የጉ ልበት ሥራ የጠነከረ አካሉ ፣ በመንገድ ብዛት የከረረ ጡንቻና ጅማቱ ዛሬ ደግሞ ከብረታ ብረት ጋር በሚደረግ ትንቅንቅና ሥራ እየጠነ ከረ ፈረጠመ ።

የቀኛዝማች ውዴታቸው ሳይሆን የገንዘብ ድኅማቸው ፣ "ከእንግዲ ህስ ምንም አይል ፣ ራሱን እየቻለ ነው" በሚል ግምት ፣ "በአይዞህ በርታ" ተተካ ። በርግጥም የወር ደመወዙ ከዘበኝነት ጊዜ ክፍያው ጋር ሲነጻጸር ከሁለት እጥፍ በላይ አድጓል ። ሽቅብ ተንጠራርቶ እነ ቀኛዝማችንና ሞገስ እምባቸውን ለመጋበዝ ባይቃጣውም፣ እሱም በደ ረጃው ፣ በቢጤዎቹ ተጋብዞ መጋበዝንና ውለታ መመለስን ፣ ከዋል— አደርም ለወ/ሮ ደጅ— ይጥኑ "እስኪ ይቺ ለቡናሁ ትሁንሁ" እያለ ጨበጥ ማድረግን ጀመረ ።

ከቀኛዝማችና ከሞገስ ፣ ወይም ከሌላ ሰው ጋር ሲነጋገርም አን ደበቱ ዘና ፣ አነጋገሩ ፈጠንና ኀላ ማለት ያዘ ። ስለ መኖሪያው ጉዳይ የማሰላሰሉ ነገር ግን እየጨመረ እንጂ ፣ እየቀነሰ ባለመሔዱ ፣ "እስከ መቼ ድረስ ሰው አስቸግራለሁ ፣ እንኳን ባዳና ዘመድም ቢሆን ይሰለቻል" በማለት አውጥቶና አውርዶ የራሱን ውሳኔ ወሰነ ።

በቅድሚያ ቀኛዝማችን አማከረና ላቀችንም አዋያት ። ሰውየው ሐሳቡን ደግፈው የመቋቋሚያ ድጎማ ሲሰጡት ፣ ላቀችም አንዳንድ የማሰናጃና የመመገቢያ ዕቃዎች አዘጋጀችለት ። ሞገስም የበኩሉን ሰነ ዘረ ።

ምንዳዬ ፣ ከአንድ የጋራዥ ሠራተኛ ጋር በደባልነት ለመኖር ቤቱን ለቆ ሲወጣ ፣ ከፍ ያለ ልባዊ ምስጋና አቀረበ ።

በበዓላትና በዕረፍት ቀናት ወደ ቀኛዝማች ቤት ሲሔድ ፣ ሚስትዮዋ ያቺኑ እንዳቀሙ የሚያደርጋትን ጫማ ፣ የሚለብሳትን የተተኳኮሰች ካኪ ልብስና ተራ ሸሚዝ ሲያዩ ዐይናቸው ይቀላና ፣ "ይኸ ጥፍራም ባላገር እከኩን አራገፈ አይደል ! እኔ ተኀዳሁዪ ፣ አዳሜማ ተጠቃቀመ ችብኝ ። እዚያ ስንቱ የለፋላቸው አሳረ—መከራውን ያያል ፣ ይኸ በደ ህና ጠጠር ጣይ አስጠንቁሎ ፣ ሰላ ብሎ ገባና ሰው ሆነ ። አንዳች ነገር አበስ ብያደርግባቸው ነውዪ ፣ እስቲ ምን አርጎላቸው ነው ፣ እሱን እዚህ ሥራ ዶለው ፣ እዚያ ደሞ ሚስትህ እርሻዋን ታሳርስ ማለታቸው ? ሙቻ



ታለሁዋ ! ያቺን መሬት አስመንጭቄ መቅኖ ባላሳጣው" እስከ ማለት ደረሱ ።

ሽዋርካብሽ ግን ምንዳዬ ሲመጣ ፣ ዐልፎ — ዐልፎ ልኩን ባል ሳተ ድፍረት ፣ የሴትዮዋን ሁኔታ እየገመተች ታሜውተዋለች ። "እኔስ እንደሱ የሚያልፍልኝ መቼ ይሆን?" በማለት ራሷንም ፣ እምላ ኳንም ትጠይቃለች ። መልስ አታገኝም ፤ የሩቅ ተስፋም አይታያት ።

"አሁንማ ያዲስአባ ሰው መሰልክ ምንዳ?"አለችው ።

"ከዋል አደር የት ይቀራል?"

"እስቲ ለኔም ቀስ ብለህ ሥራ ፈልግና እሰው ቤት ዱለኝ"አለችው ዙሪያዋን አይታ ።

"በያ ደሞ ደህና ተንፈስ ያልኩትን ፣ እንደገና ጥርስ አስገቢኝ — —እኝህ ቤሽቲያ ዘመድሽ ነገሩን አዙረው የቡና ማከተሚያ ነው እሚያረጉኝ ።"

"እውነትም በሽተኛ"አለች ነገሩ ስላልገባት ።

ምንዳዬ ከት ብሎ ሣቀና ፣ "እኔማ ለጓደኞቼም ነግሬ ቢሆን አፈ ላልግልሽ ነበር — — አንቺ ግን" ከማለቱ ፣

"አይለፍልሽ ብሎኝም እንደሁ ፣ የላይኛው ጌታ ያቃል ። ላመድ ያለው ቂጥ ለኮርቻ አይሆንም ይባላል ፤ እዚሁ ዐመድ ላመድ ተርመ ጥምጠሽ ቅሪ ካላለኝ — —"

"ለምን አገሬ መልሱኝ አትያቸውም ። ምን ዕዳ አለብሽ!!"

"ኧረ በምን ሥራ አጣሀልኝ ! አበስ ገበርኩ! ለዕድሌም አላሳየው ፣ ይልቅ አንተ የወንድምነትክን ዋልልኝ! የኔን ዘመድ አታንሣ! ከዘመዱ ጉዳይ ናት! መጨበጫም የላት ። አሁንማ እንዳለፈው ቅዳሜ ጣል አር ጋኝ ፣ ባንዲት ጨርቅ ተጣብቄ ቀረሁ" ብላ እንባ ሲተናነቃት ፣ አዘነ ።

ምንዳዬ ሊጠይቃቸው በሔደ ቁጥር አንዳች ተስፋ ይሰማታል ። ባጋጣሚ ሴትዮዋ ሳይኖሩ የደረሰ ዕለት ብሶቷን ስትነግረው ቀለል ይላታል ። እሱ ግን ፣ ሆን ብሎ የሚመላለሰው ሴትዮዋን ለማበ ሳጨትና መሻሻሉን ለማሳየት ነበር ።

ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ግን ፣ እሱ የገመተውን ያህል አልተበሳ ጩም ። በተገናኙ ቁጥር ፣ "የኔ ጎርጊስ አዛዬን ነቀለልኝ" በማለት በሽ ንጋይ ፈገግታ ይቀበሉና ፣ "ደህና ነህ ወይ? ምነው መሰንበቻውን ጠፋህ?" ይሉታል ።

"ደህና ነኝ፣ ሥራው በየት አላውሶ! ፋታ አይሰጡ — —" ይላል ሥር— ሥሩን ግን "ደግ አሳቢ መሳይ!—መጥፎ ጊንጥ" እያለ ።

"ከሣር——አምባ የመጣ ሰው አላገኘህም? ያቺ ልኬለሽ ደህና ናት? ትልክባታለህ?"

"ደህና ነች ። ታለፍ—ታለፍ እልክባታለሁ"

"እነኛ ልጆችህስ ልጄ? ናፍቆቱ እንዴት አርጓቸው ይሆን ?"

"ደህና ናቸው! እናታቸው እያለች ምን ይሆናሉ? ትልቁም እርፍ ይዞ ይወናከራል አሉ ። እኔ እሱን ሳህል አርስ ነበር"

"ታመጣታለህ ፤ አንተንም እዚሁ ሌላ ከጀለህ" አሉት በስላቅ ድምፅ ።

"ምንስ ቢሆን እሷ አትሻልም ብለሁ ነው?"አለ የሚሉትን ለመ ስማት ።

"ምን ታረግ?—አንተስ ውሎህ ከነማጋ ሆነና? ደሞ ብለህ —ብለህ አትሻልም ወይ አልክ ? 'ወንድና ቢላዋ የሰባ ይወዳል' አሉ እቴዋ ሺምልጃሽ ። ሁሉም ቀሪ ነው ። የምር አይምሰልህ— እንዲያው ብቻ የቅልውጥ ውሃ ይጣፍጣል ይባል የለ" አሉ ኮስተር ብለው ። ልብ ለልብ ስለሚተዋወቁ፣ ዝም አለ ። "ምን ታረግ— ምን ታረግ!!እንተም እንደ ጌታህ ሌላ አስፈልጎህ ይሆናላ?! ለዚያች ለድሃም እዝጊሃር ያቅ ላታል ልበለውና ምን እንደሚል ልስማው ይሆን" ብለው ሊመልሱ ለት ካሰቡ በኋላ ከፋቸው ላይ መለሱት ። ምንም እንኳ ምንዳዬ በልኬ ለሽ ምትክ ሌላ ሴት ባይመኝም፣ ከባልንጀሮቹ ጋር መጠጥ ሲጠጣና የሩካቤ ፍላጐቱ ሲቀሰቀስ ፣ ሴት አዳሪ ቤት መሔድ ጀምሯል ።

"ሰው ፣ እህልና ውሃ በልቶና ጠጥቶ ዝም አይል ፣ አንዳይ ጉድ ተፈጥሮብን" ይላል አምሮቱን ለማርካት ከራሱ ጋር ሲዶልት ። ሆኖም የቤተሰቡን ናፍቆት ሊቋቋምና ብቸኝነቱን ሊያቃልልለት አልቻለም ። ስለዚህም ፣ ምን ማድረግ እንዳለበት ሲያወጣና ሲያወርድ ፣ ጊዜው እንደ ሙስኖ ውሃ እየፈሰሰ ፣ ቀናት እንደ ናዳ ድንጋይ እየተንደ ረደሩ — —ምንዳዬም ከአዲሱ ኑሮና ሥራ ጋር እየተለማመደ ፣ አንድ ዓመት ነጎደ ።



## ምዕራፍ ዐርባ ስድስት

ቀኛዝማች ፣ ቢጤዎቻቸው የሚያከናውኑትን የእንካ—በንካ አኗኗርና ለማደግም የት ጨበጥ ፣ እንዴት ረገጥ ማድረግ እንደሚገባቸው በይ በልጥ እየገባቸው ሔደ ። በተለይም ገንዘባቸውን እንዴትና ለምን እንደ ሚያወጡና ሐሳባቸውን ለማን እንደሚያካፍሉ ስላወቁበት ፣ ከሌሎች ጋር የጀመሩት ወዳጅነት እየተጠናከረ ፣ ከአቶ ወርቅነህ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ሳያጤኑት ላላ ። በዚህም አቶ ወርቅነህ መዘውር ቀደም ሲል እንደ ተመኙት ሳይጠቀሙና ቀኛዝማችም ወደ ወይዘሮ ደጅ— ይጥኑ የመሔዳቸው ልምድ ከሠልስት ወደ ሳምንት እየረዘመ ፣ እጃቸውም እያደር በማጠሩ የአቶ ወርቅነህ የጥርጣሬ ጥንስስ መብላላት ጀመረ። ሆኖም "እስቲ ለማንኛውም ዋል—አደር እንበል ፣ የፍቅርም የጥላቻም እያደር ይለያል" ብለው ለጊዜው ታገሡ ። ነገር ከያዙ ቶሎ አላምጠው አይውጡም ።

የቀኛዝማች የወቅቱ ተፍ—ተፍ ግን ፣ እንደ ቀድሞው ለምንዳላ ብትና ዳሌ ፣ ለሚያረገርግ ቂጥና ገላ ብቻ መሆኑ ቀርቶ ፣ ለተጨማሪ ሀብትና ንብረትም ስለነበር ፣ "ሲያመቸኝ ሲያመቸኝ መሔዴን አልተ ውኩ ። እህሉን ከሣር—አምባ ፣ ጮማውን ካዲስአባ አላጓደልኩ ። የቤቷ ቱም ይኸን ያህል አልተንቀባረረች ፣ በላይነህ የብር መውቂያ አው ድማ አለው ያለው ማን ነው? አይ ካለች ፣ እዚያው ማጀቷዋ ልትመ ለስ ትችላለች" አሉ የአቶ ወርቅነህ ቅሬታ የስሚ ስሚ ሽው ስላላቸው የኔንም ወስዳችሁ አድርሱልኝ በሚል አኳኋን ። በሚገቡበት ትላል ቅም ሆነ መካከለኛ ሆቴል ሁሉ የሴት አዳሪው ብዛትና ዓይነት ፣ የቀኛዝ ማችን ሴሰኛ ልብ በምርጫ ስላንበሸበሸው ፣ በጉዳያቸው ጣልቃ — ጣልቃ ቀልባቸው ያረፈባትንና ስሜታቸው የጓጓላትን ሴት ለመገና ኘት ፣ የሥራ ደረጃም ሆነ የዕድሜ ጸጋ ክብር አላወካቸውም ።

ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ፣ ስለ ኑሯቸው ይበልጥ ማሰላሰል የያዙት ፣ ከላቀችና ከምንዳዬ አንዳንድ ስጦታ መቀበል ከጀመሩ ወዲህ ነበር ። "እንዲህ እዚያ ታች ወርጄ አረፍኩታ ! ሰው ተገዛ ሎሌው ርዳታ ከተቀበለ ወዲያ ምን መላ አለው" ብለው ይተክዙና "እልሂን ሳልወጣ አልሞት" በማለት ከንፈራቸውን ይነክሳሉ ።

ሞገስ የወ/ሮ ደጅ—ይጥኑን የቀድሞ አኗኗርና ጠባይ ከገዛ ባለቤቱ ከተረዳ በኋላ ፣ "እኝህማ ከሴት አዳሪ በምን ይሻላሉ? እኔኮ

ከቀኛዝማች ሌላ ምንም ሰው እሚያስጠጉ አይመስሉኝም ነበር’’ በማለት እቧንም እያደር ሊያባልጉት ይችላሉ ብሎ በመጠርጠር ፣ ሴትዮዋ ዘንድ በየጊዜው እንዳትሔድ ፣ ከሔደችም ቶሎ ደርሳ እንድትመለስ በጥብቅ አስጠነቀቃት ። ታዝባ እግሯን ብታሳጥርም ፣ እጅዋ በምንዳዬ በኩል መዘርጋቱን አላቋረጠም ።

* * *

አቶ ወርቅነህ መዘውር በያጋጣሚው ሁሉ ፣ ስለ ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ የለየለት ጥብቅና ቆመው ፣ ቀኛዝማችን በለሰለሰ ምላስና በሰላ አንደበት መሞገቱን ተያያዙት ። ሴትዮዋንም ፣ “አትሞኚ ፣ ቶሎ ቶሎ ግፈፊ ፣ እንዲህ ያለውን ሰው ፣ እያባበሉና እያሣሣቁ ካልጋጡት ፣ እጁ በቀላሉ አይፈታም ። አሁንማ ብዙ ነገር ዐውቀዋል’’ በማለት ብዙ ነገር አማከሯቸው ።

የሴትዮዋ ተስፋ እንሰራራ ። ተበደልኩ ብሎ ማማረርን ፣ ቀሩ ብሎ መበሳጨትንና ቀኛዝማች ሲመጡም ማበጥ መቆጣቱን እርግፍ አርገው ተዉት ። እንዲያውም ፣ “ተንግዲህስ ወዲያ አልሞኝም’’ ብለው በአካልና በምላሳቸው ለመጠቀም ታጥቀው ተነሡ ።

ጊዜም አላጠፉ ። በጣፈጠ መዓድና ቀልብን ጠፍሮ ከጉዳይ በሚያዘናጋ ያልጋ ላይ ድሪያ የሰውየውን ነፍስ ሲኮረኩሯት ፣ የቀኛዝማች ነፍስ እየተክለፈለፈች ሰተት ብላ ወጥመድ ገባች ። ማ ሊለቅ ! ከዚያማ እንደበታቸው ለእሺታ ፣ እጃቸው ለስጦታ ተዘረጋ ። በጥቂት ወራት ውስጥ አነስተኛ ምድረ—ግቢ ያለው ባለሁለት ደጃፍ ቤት ተገዛ ። ‘እስተዛሬም ተታልያለሁ!—እንግዲህ እንድ አልኩ’ አሉ በልባቸው ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ። አቶ ወርቅነህ መዘውር ነገሩ በሳቸው ጉትጎታና ብርታት ብቻ የተፈጸመ ለማስመሰል ፣ “ቀደም ብዬም ተናግሬ ነበር ። እንዲህ ያለውን ሰው ቀስ ብሎ በዘዴ ነው ማለብ ፣ ‘መጀመሪያ የቂጧን አለች’ አሉ ዝንጀሮ ። ይህን የመሰለ ደህና ቋሚ ንብረት ከጨበጥሽ ፣ ከእንግዲህ ወዲያ ደግሞ ፣ እንደ ምንም በርትተሽ መቋቋሚያሽን ትመነዳድቢና ፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ ይመከርበታል ። ያነዬ ታዲያ ገሸሽ እላለሁ ቢሉ ፣ አንቺም ዘወር ነው ። እንዳንቺ ያለ መልከ—መልካም የሰው እጅ አይቶ አይኖርም ። ባታውቂበት ነው እንጂ ለብዙ ሰው ትተርፊ ነበር ። ስንትና ስንት ጥሪት ታበጂ ነበር’’ በማለት የበርትተሽ ግፈፊ ምክራቸውን ሥራዬ ብለው ተያያዙት ። እጅሪትም ፣ “አሁንማ ዐውቄበታለሁ ፣ እስተዛሬም የመካሪ እጦት ነው’’ በማለት ጅምራቸውን ገፋበት ።



ካዛንቺስ ከአስፋወሰን ት/ቤት ማዶ ያስገዙትን ቤት እንደ ነገሩ አሳድሰውና አንዳንድ ዕቃዎችን አስገዝተው ሲገቡ ፣ ከፍተኛ የድል አድራጊነት ኩራት ተሰማቸው ።

ቀኛዝማችም ማንነታቸው ታውቆ ፣ “መጡ እንዴ! ሔዱ እንዴ!’’ በማይባሉበት አካባቢ እንደ ልብ ሔድ መለስ ማለቱን ቢወዱትም ፣ ሴትዬዋ አቶ ወርቅነህ ግቢ በነበሩበት ጊዜ ፣ ማንም እንደልቡ ገብቶ ሊያነጋግራት አይችልም ብለው ስለማያስቡ ፣ አንዳችም ጥርጣሬና ቅናት ዳብሷቸው አያውቅም ነበር። አዲሱ መኖሪያ ግን፣ ቅናትና ጥርጣሬ ፈጠረ። ቀልባቸው መከፈል ፣ ልባቸው መሸበር ጀመረ ። በተለይም ቤቱን በመግዛት ረገድ የወሰዱት ያልተብላላ ፈጣን ውሳኔ ፣ ጸጸቱ እየጠዘጠዘ ፋታ ነሣቸው ። “ወይኔ በላይነህ! ከነዘመዴ ተመሳጥራ ሥራዋን ሠራች አደል ። ይቺ መልቲ ፣ ለካ እንዲያ እለቃቅሳና ሰባብካ ያጣደፈችኝ ለብልሃቷ ኖሯል!ዋ አለማወቅ! የዋዛ ሰው ሙስያታለሁ ፣ አንድ መላ ይበጅላታል’’ በማለት የግል ጠባቂ ለማስቀመጥ አሰቡ ። ይህን መላ ማጀቴም ተጠቅመውበታል ። ልዩነቱ የማጀቴው ከውጪ ሆኖ የሚሰልል መሆኑ ነበር ። ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ግን ፣ የሚሰልላቸውን ሰውዬ እንዳወቁ ፣ እየት—መዘን አድርገው ፣ በመጀመሪያ ክርሱን ጠቅጥቀው ምላሱን በስብከት ይሰንጉና በኋላም በጥቅም አርጩሜ ይነዱት ነበር ።

ሴትዩዋ የማጀቴው ኑሯቸው በዐይነ—ሕሊና ከመታየት ዐልፎ ውል አላቸው ። ያውም ብዙ ያዩና የለመዱበት ውልታ ። ቀን በጥየቃ ሰብበና ማታ በጨለማ ተገን ከሚገቡት ወዳጆቻቸው ያገኙት የነበር ልዩ ልዩ ጥቅም ፣ እንደገና ጉልቶ ታያቸው ።

* * *

ወ/ሮ ደጅ— ይጥኑ አዲሱን ቤታቸውን ወደዱት ። “በየህ ላይ አንድ እንዳልኳት ሆና የምታድር ሠራተኛ ባገኝ ፣ እንደ ምንም ብዬ ነፍስ እዘራ ነበር’’ ብለው ወይዘሮ መንበረን አማከሯቸው ። ተግባቡና ተሳካላቸው ።

ቀኛዝማችም አውጥተውና አውርደው ፣ ቢበድሉት የሚናገር ፣ ቢያጠቁት የሚቆረቆር ሰው የለውም የሚሉትን ድሃ ገበሬ ከሣር—አምባ አስመጥተው ፣ “ሰው ጥሩ ነው ፣ ብቻሽን ስትሆኚ እንዳትፈሪ ብዬ ነው ። መደፈርም ይኖራል ። ማጀቴ ቢሆን አሳብ አይገባኝም ነበር ። እዚህ ግን ማን ያውቅሻል’’ ብለው ጠባቂ አኖሩ ።

ሆኖም ፥ በሦስትና በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ፥ ዐይን ከጣሉባቸው የአካባቢው ወንዶች መካከል ያወቀበት እግሩን አስልቶና ጊዜውን አጢኖ ጐራ ማለት እንደ ጀመረ ፥ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ጠባቂያቸውን በጣፈጠ ፍርፋሪና ባደረ ቅራሪ እየሸነገሉ ፥ ምላሱን ቀየዱት ። ቀኛዝ ማች ሲጠይቁት ግን ፥ "እኔ እንዲህ ያሉ ሴት አይቼም አላቅ! እንኳን ሰው ወፍ ዝር አይልም" ብሎ የሴትዮዋን ታማኝነት ይገልጽላቸዋል። እሱ ግን ፥ 'እንደ ገበያ አህያ ዐሥሯን ሲያሸቱ ዕድሚያቸውን ፈጁት' ይላል በልቡ ።

የገጠር ደመወዙ እስከ ረፋድ የማታቆይ ማሳ ስትሆን ፥ ያቺንም ከመጋዞ መሬት ጋር የሚያርሳት ልጁ ነበር ።



# ምዕራፍ ዐርባ ሰባት

ምንዳዬ ሁለተኛ ዓመቱን እንደ ጨረሰ ፥ የግርግሬ አንጋሬ እምታ ሀል ልሙጥ ቆርቆሮ ፥ የሸራ ወይም የጐማ ቅዳጅ ያነጥፍና ከተበላሸ መኪና ሥር ፥ በጐኑ ወይም በጀርባው ተኝቶ የላላውን አጥብቆ ፥ የተ ሰበረውን ቀይሮ ብቅ ሲል ፥ የተለበለበ እንጨት ይመስላል ። እንደተ ቀጠረ ሰሞን ያደረገው ድርጊትና የፈጸመው ስሕተት ሁሉ ትዝ ሲለው ብቻውን ይንከተከታል ። ሠራተኞቹ በዘበኝነቱና ከዚያም ወዲህ መፍቻ እቀባይ ሆኖ ሲሠራ በነበረበት ጊዜ ያደረገውን የቶሎ ዐውቄ ልመ ስገን ጥድፊያ እያስታወሱ ሲሥቁበት እሱም አብሮ ጦሽ ይላል ። በተ ለይም አንድ ጊዜ አንዲት ተጠግና የቆመች ፊያት 1500ን በውሃ አጥቦ በናፍታ እንዲወለውላት ታዝዞ ሲሠራ ፥ ሠራተኞቹ ሆን ብለው ይጠቃቀሱና መኪናይቱን ከበስተኋላ ሲገፏት ቀስ ብላ መንሸራተት ትጀ ምራለች ። ምንዳዬ ደንግጦ እመር ብሎ ከውስጧ ይወጣና ፥ ከፊት ለፊት ቀድሞ ሊያቆማት ይሞክራል ። ቦታው ትንሽ ቁልቁለታማ ስለነበር ፥ ከአቅሙ በላይ ትሆንበታለች ። ሠራተኞቹ ከያቅጣጫው ሲሥቁ ፥ "አንድ መላ በሉኝ ፥ እኔ ልለቅላችሁ ነው" ይላል ።

"በርትተህ ያዝ እንጂ ! ብትጋጭስ?"

"ምንዳ! ዐይኑ እያዬ — — ይዳጥላችኋል ! መልቀቄ ነው!" ሲል፥ እየተሟሟቁ ይረዱታል ። ያን ዕለት ማታ አብሮ ሲሥቅ አመሸ ።

ከሥራ ሰዓት ውጪ አብዛኞዎቹ የያዙትን ይዘው በየመጠጥ ቤቱ ይሰገሰጋሉ ። ቀን ጉልበታቸውን በሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ ሲያስመ ጥጡ ይውሉና ፥ ማታ ማታ ደግሞ ገንዘባቸውን በየመሸታ ቤቱ ሲከ ሰክሱ ያመሻሉ ። ንዴትና ብሶታቸው በመጠጥ የሚቃለል ይመስላቸ ዋል ። ንግግራቸው ሁሉ አጭርና ቁርጥ ያለ ሆኖ ፥ ከወደዱ መሬት ፥ ከጠሉ ሬት ናቸው ። የበቀላቸው ክንድ አያላውስም ።

ምንዳዬ ከልዩ ልዩ ሠራተኞች ጋር ባወራ ቁጥር ፥ አንዱ ስለሌ ላው ዐመል እየነገረው ፥ ካሚታና ካሉባልታው ፥ ከቀልድና ከጨዋታው ስለ አካባቢው ሰዎች ጠባይ አያሌ ነገር አወቀ ። ሲኞር ካርሎና ወኪሎቹ የሚያቀርቡና የሚያርቁት ፥ የሚጠቅሙና የሚጎዱት ሠራተኛ እንዳለም ተገነዘበ ። ከሠራተኞቹም መካከል እነ ማን በጐሪጥ እንደሚ

ተያዩና እነ ማን እንደሚቀራረቡ አስተዋለ ። እሱም ፤ “ያጐረሰ ገሠገሠ፤ እጅ ያሳጠረ ጦሙን አደረ” የሚለውን የሠራተኞች ዋዛ መሳይ አባባል አጢኖ ፤ ከፍ ብሎ ሕድሩን ፤ ዝቅ ብሎ የሱን በታቾች መጋበዝ ለመደ ።

በቀልድም ሆነ በቁም — ነገር ምንዳዬና ሠዐረ ይቀራረባሉ ። የቅርብ አለቃው ቢሆንም የመግባባታቸው ደረጃ ቀስ—በቀስ እያደገ በሔመዱ ፤ ባልንጀራነት መሠረቱ ።

“ይኸ እምሐራይ ትንሽ ወንድምዬ ይመስለኒ ፤ ታናሽ ወንድምዬ እንደዚ እንደ ምንዳይ ሕርኩት ነበረ” በማለት እያሞገሰ ይወደዋል ። ሁለቱ ስለየትውልድ መንደራቸው በሚያወሩበት ወቅት፤ ምንዳዬ ላይ ላዩን ሲያጫውተው ፤ ሠዐረ ግን ፤ ያየውንና የሚያውቀውን ሁሉ ልቡን ከፍቶ ይነግረዋል ። ልዩነታቸው እዚህ ላይ ብቻ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ግን ይግባባሉ ። ሲጠሉም ሆነ ሲወዱ ተመሳሳይነት አላቸው ።

ቅርበታቸው እያደር በመጨመሩ ጓደኝነታቸው ዳብሮ ምስጢር መጋራትና ብሶታቸውን መወያየት ጀመሩ ። ምንዳዬ የሱንና የባላንጦቹን ጉዳይ እንደ ግላዊ ምስጢሩ ስለሚቆጥረው አውርቶለት አያውቅም ።

ሠዐረ ብዙ ማውራት አይሆንለትም ። ለጋስ ነው ። ከፍ ያለ የሜካኒክነት ችሎታ ቢኖረውም ፤ ‘የሥራና የችሎታዬን ያህል አይከፈለኝም’ በማለት ዘወትር ይማረራል ። መጠጥ የምሬት መርሻና የብስጭት ማቃለያ አለመሆኑን ቢያውቅም ፤ ለጊዜው ያረሳሳል በሚል ሰበብ ፤ ከሥራ እንደወጣ ወደ መጠጥ ቤት ጐራ ማለትን ያዘወትራል ። ያነዬ እንደበቱ ተከፍቶ ምላሱ ይፍታታል ። ሕሊናው ውስጥ የሚያመረቅዝ ቁስል ያለ ይመስል ፤ በሰከረ ቁጥር በቀልና ጥላቻው ጐልተው ይወጣሉ ። ፍርሃትና ተለማማጭነት አይታዩበትም ። ምንዳዬንም ፤ “አንቴ ሁሉጊዜ በክእለትካ ተአመን ፤ ዕውቀት ያለህ ሰው ከሆንካ ፤ ከመንም በታሽ አይትሆንም ፤ አይዞኸ ፤ እኔ እሚያውቅ ያለሁ ነገር ሁሉ እሳይሃል ፤ ከስተምህረካዬ ንመንም አይትፍራህ” ብሎ የሚያውቀውን እያሳየና የሚጠይቀውን እየነገረ ፤ ከበሰለ ዕውቀትና ችሎታው ደረጃ በደረጃ አጋራው ። ምንዳዬ ካደገበት ኅብረተሰብ የወሰደውን አብልልቶና አጠጥቶ የማደግና አደግድጎ የመኖርን ጠባይ በሠዐረ ግፊትና ምክር ቀስ በቀስ እየቀነሰ ፤ በራሱ ልፋትና ችሎታ ተደላድሎ የመቆም አዲስ ጠባይ ፤ ገና ድክ—ድክ ከምትለው ዕውቀቱ ጋር ተቀበለ።

* * *



ሠዐረ በኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ፤ በሐማሴን አውራጃ ፤ በደቀ—ተሽም ወረዳ የወከድባ መንደር ተወላጅ ነው ። በጣሊያን ጊዜ ፈረንጆቹ ለሙን የእርሻ መሬትና አካባቢውን ፤ ከአገሬው ሕዝብ በግዴታ ነጥቀውና ነቅለው የፈለጉትን ያህል መሬት ይይዙ ነበር ። አቤት የሚባልበት ሸንጎ ፤ ፍትሕ የሚጠየቅበት አደባባይ አልነበረም። የነሠዐረ መንደርም በለምነቷና በአካባቢው የተፈጥሮ አቀማመጥ ምቹነት የተነሣ ፤ አያሌ ጣሊያኖች ዐይናቸውን ጣሉባት ። ተቀራመቷት ። የነሠዐረ ቤተሰብ መሬትም አንድ ኢጣሊያዊ እጅ ገባ ። ጣሊያኖቹ ያወጡት ሕግ ፤ ራሳቸውን ጠቅሞና ተክሎ ፤ አገሬውን የጉልበት ሥራ አገልጋይ የሚያደርግ ነበር ።

ኢጣሊያዊው ከዐፅመ ርስታቸው ከነቀሏቸው ሰዎች መካከል አንዳንዶቹን መርጦ በእርሻ ሥራ ላይ ሲያሠማራ ፤ ሌሎቹን ደግሞ የምርቱን ውጤት አሥመራ ወስደው ለፋብሪካና ለግለሰብ እንዲያደርሱ ደለደላቸው ። ቀሪዎቹ መንደርተኞች ግን ፤ በሐበሻና በጣሊያን የመኖሪያ ክልል ወደ ተከፈለችው አሥመራ ገቡ ። የሠዐረ አባት ለዕለት ጉርስ በማትበቃ ክፍያ በሚገዛቸው ኢጣሊያዊ ርግጫና ጡጫ እንዲሁም በሚያሳየው ትዕቢትና በሚያደርሰው ሥቃይ ተማረሩ ።

አንድ ቀን ሌሊት ፤ የጣሊያኑን የስንዴ መጋዘን እሳት ለኩሰውበት ጠፉ ። በዚያን ዘመን ልጅ የነበረው ሠዐረ ፤ እናቱና እኅቶቹ ታስረው ሲገረፉና ላንድ ዓመትም በነጻ እንዲያገለግሉ ተፈርዶባቸው በግፍ እየተንገላቱ ሲሠሩ አይቷል ። አባቱ ግን አውሬ ይብላቸው ፤ አሞራ ይንጫቸው ሳይታወቅ የውሃ ሽታ ሆነው ቀሩ ። ጊዜ እንደ መስኖ ውሃ ሲፈስም — —ተኩላ ለቀበሮ አቀበለች ፤ እንግሊዞች በጣሊያኖች እግር ገቡ ። የከረመው መጋዝ ባዲስ መቀርጠፊያ ተተካ ። ዓመታት አለፉ ። አንዱ ባለሥልጣን በሌላ ሲተካ ፤ ጣሊያኖቹ ከሕዝቡ የነጠቁትን የእርሻ መሬት ግዙን አሉ ። አቤቱታ ሰሚና ፍትሕ ሰጪ አልነበረም ። ውሳኔ ተሰጥቶ ትእዛዝ ተላለፈ ።

መንደርተኞቹ የገዛ ርስታቸውን እንዲገዙ ፤ አለበለዚያ ለሌላ ገዢ እንደሚሸጥ ተነገራቸው ። የጥቅም ተካፋይ ሐበሾችም አብረው አረጠረጡ ። ግፍ የገዘገዛቸው መንደርተኞች ተሰብስበው መከሩ ። እምቢ ቢሉ ማምለጫ ፤ አቤት ቢሉ መደመጫ አልነበረም ። የፍትሕ ጉሮሮ ታንቋል ። እናም የገዛ መሬታቸውን ለመግዛት ተገደው ተስማሙ ። የተገመተውን ብዙ ሺህ ብር በሦስት ጊዜ ክፍያ ከፍሎ ለመጨረስ የግዴታ ውል ገቡ ። የሠዐረ ቤተሰብ ግን ፤ በግዢው መዋጮ ላይ ለመካፈል ሳይችል ቀረ ። እሱም በዚሁ ተበሳጭቶ ሥራ ፍለጋ ወደ አሥ

መራ ይሔድና ከከተማው በስተሰሜን ትንሽ ወጣ ብሎ ፣ በአንድ ኢጣሊያዊ የጡብ ፋብሪካ ውስጥ በቀን ሃምሳ ሳንቲም ይቀጠራል ።

ኑሮ እየመረረውና ጭቆና እያንገሸገሸው ብዙ የሥራ ቦታ ቀያየረ። በኋላም ጋራዥ ውስጥ ተቀጥሮ ጥቂት ዓመታት ከሠራ በኋላ በ1954 ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ ጋራዥ ተቀጠረ ። ይህንና ሌሎችንም የመከራና የደስታ ትዝታዎቹን ለምንዳዬ አጫውቶታል ። "ወዬ ጉድ! ለካ ከኔም የባሰ አለና! እህ! ካሉ ስንት ጉድ ይሰማል" ብሎ በአዘኔታ ራሱን ነቅንቋል ።

ጊዜ እንደ መስኖ ውሃ እየፈሰሰ ፣ ቀናት እንደ ናዳ ድንጋይ እየተንደረደሩ ። — — —



## ምዕራፍ ዐርባ ስምንት

ስንሰለቱ እንደ ከረረና ፣ ቀንበሩ እንደ ከበደ የሠራተኛው የድካም ውጤት ሰተት ብላ ወደምትገባበት ትገባለች ። አራሹም ፣ ቀጥቃጩም ከሞፈርና ከሞተር ጋር ይተናነቃሉ ።

ሠዐረ 'የሠራተኛ ማኅበራትን ከሚያቋቁሙ ሰዎች ጋር በድብቅ እየተገናኘ ይመሳጠራል' የሚል የስሚ—ስሚ ወሬ ከአሠሪ ወኪሎች ዘንድ በመድረሱ ፣ 'ሳይዘገይ አርፍደሃል ፣ ሳይለግም ሥራ በድለሃል ፣ ሲጠግን መሣሪያ ሰብረሃል ፣ አለቆችህን ገላምጠሃል' በሚል የሐሰት ክስና በሥልጣን ኃይል በመጠቀም ፣ ደመወዙን እየቆረጡ አበሳጩት። ቅጣቱ እየጨመረና ጥቃቱ እየከረረ ሔደ ።

ክፉኛ በተበሳጨበት አንድ ዕለት ፣ ከምንዳዬ ጋር ወደ መጠጥ ቤት ይሔዱና ሠዐረ አከታትሎ ይጠጣል ። ያም ቢሆን አልሰነፈ ። እየተዘዋወሩ ሲጠጡ ካመሹ በኋላ የሞቅታቸው ደረጃ ከፍ እንዳለ ፣ አዘውትረው ወደሚገቡበት ቡና ቤት ይገባሉ ። ይጨምሩበታል ። በመኻሉ ሠዐረ ወዳጁ ከሌላ ወንድ ጋር ስትሣሣቅና ስትዳራ በማየቱ ደሙ ይፈላና አፉ እንዳመጣ መሳደብ ይጀምራል ። ምንዳዬም አብሮ ደሙ ፈላ ። የሠዐረ ደም እንደፈላ አልቀረም ። ግብግብ ገጠመ ። ሁለት—ሁለቱም በደህና ቡጢ እንደ ተዳቁ ፣ ሠዐረ የተጣዩን አንገትጌ ይዞ ከወደራሱ ወደ ጐንና ወደ ኋላ እየተለጠጠ ፣ በጭንቅላቱ የሰውዬውን አፍንጫና ከንፈር ሁለት ሦስቴ አላትሞ ሲያደማው ፣ ሰውዬውም ያንኑ ያህል ደህና አድርጎ መደወተው ። ሠዐረ እያጠቃ ሰውዬው እየተከላከለ ሲናረቱ ፣ የዚያኛው ሁለት ባልንጀሮች ገላጋይ መስለው ተቀላቀሉ ። ዳር—ዳር ሲል የቆየው ምንዳዬ "አባ ገላግሌ !" ብሎ እንደ ቀትር እባብ ሲወረወር በቅድሚያ አንድ ቡጢ ቀመሰ ። ወገቡን ሰበር ፣ አንገቱን ቀርቀር አድርጎ ፣ በሚያውቀው የትግል ዘዴ ሰውዬውን ሽቅብ አጉኖ ከመሬት ደባለቀው ። አልተነሣም ። ሌላው ሰውዬ ግን ፣ የዋዛ ዱለኛ አልነበረም ፣ በቡጢ አጣደፈው ። ምንዳዬ የሚያዋጣው መስሎት በዚያኛው በዘዴው ሽቅብ አጉኖ ከመሬት ሊደባልቀው ሲል ፣ እላዩ ላይ ተጣብቆ ሙጭጭ አለበት ። ጎንበስ ብሎ አራገፈውና እላዩ ላይ ተከመረበት ። ጥቂት እንደ ተቦጣቦጡ ፣ በትርምሱ መኻል የተንከባለለች የቢራ ጠርሙስ ምንዳዬ እጅ ገባች ። ደህና አድርጎ ተጠቀመ

ባት ። ሠዐረም በበኩሉ ፤ እንደዩ ወድቆና ሁለተዩ ጥሎ ሰውዬውን አብረክርኮታል ።

ከየትና ማን እንደ ወረወረባቸው ሳይታወቅ ፤ ሠዐረ ቀኝ በራው ስላጤ ላይ ፤ ምንዳዬ ከግራ ጕሮው ግንዱ ከፍ ብሎ ፤ ላመል ላመል ታህል ተፈነከቱ ። አንዲ ሴት ከወደ ማድቤት ባመጣችው ደህና ፍልጥ ምንዳዬን ሁለተዩ ነረተችው ። ዘንጋ ማለቱ ቢበጃትም ፤ መለስ ብሎ ለቀም አደረገና አንድዩ እንዳሳረፈባት የሴትዮዋ ነገር አቢቃ ። ከዚያ በኋላ እከሌ አባ እከሌ ሳይል መደዳውን አጨዳቸው ። የሸሸው ሸሽቶ ሌላው ገለል አለ ። ሠዐረ የአምቦ ውሃ ጠርሙስ ፤ ምንዳዬ ፍልጡን ይዘው ቆሙ ። ያንደኛው ደም ከፊል ፊቱን ይዞ አንገትና ደረቱ ላይ ፤ የሌላው በጕሮ ግንዱ ወርዶ አንገትና ትከሻው ላይ አዋዜ መሰለ ።

ደማቸውን እየጠራረጉና እየተሳደቡ ዐረፍ ከማለታቸው ሁለት እንደ ተልባ የሚንጣጡ ሴቶች ፖሊስ ይዘው ከተፍ አሉ ። ከነምንዳዬ ሌላ ሁለት ወንዶችና አንዲት ሴት ጠረጴዛ ተደግፈው ደማቸውን ይጠራርጋሉ ። ከሳሽ እንሆናለን ያሉት እነ ምንዳዬ ተከሳሽ ሆነው ፤ ከጡጫውም ፤ ከእርግጫውም እየቀመሱ ወደ 5ኛ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰዱ ። ከዚያ ቀደም ታስሮ የማያውቀው ምንዳዬ መንፈሱ ተረበሸ ።

ፖሊሶቹ ከወሰዷቸው ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ ቃላቸውን እየሰጡ ሲወጡ ፤ የመጠጥ ቤቱ ባለቤት ፤ ጠፋ ያሉትን የንብረት ዝርዝርና ደረሰ የተባለውን ጉዳት አስመዘገቡ ። የብጥብጡ ቆስቋሾችና ለተሰባበረው ንብረት ተጠያቂዎቹ እነ ሠዐረ ናቸው በመባሉ ፤ ቀበቶቻቸውን ፈትተውና ገንዘባቸውን አስረክበው እስር ቤት ሲገቡ ፤ ምንዳዬ ገና አይቶ ያልጠገባትን ሮመር ሰዓቱን ፈትቶ ሲያስመዘግብ ፤ የተነጠቀ ያህል ነደደው ።

የጣቢያው እስር ቤት የብረት በር ተከፍቶ ፤ ፖሊሱ እነ ምንዳዬን ወደ ውስጥ ገፈተራቸው ። ተግተርትረው መደዳውን ተሰባጥረው እተኙ ሰዎች መኻል ሲወድቁ “ቡሽቲ! እናክን ! ቤሽቲያ ! ትፋታም ! ባስታርድ! ኢልማ ሃደራው! ኩሱ ኡመክ!” የሚል የስድብና የርግማን ናዳ ወረደ ። በዚያውም ጥፊ ፤ ቡጢና ርግጫ ቀልባቸውን አጠፋው ። ሰማይ መሬቱ ዞረባቸው ። እንደምንም ተደናብረው ከተዘጋው በር ጥግ ቆሙ ። ምንዳዬ ተናካሽ አውሬዎች መኻል የገባ መሰለው ። ድንገት አንድ አጠር ያለ ጸጉረ—ሉጫ ፤ ጠይም ድሪምቢታም እመር ብሎ ተነሣና ፤ ምንዳዬ ላይ “የሻማ!” ብሎ በማንባረቅ በኃይለኛ ቃሪያ ጥፊ አላግቶ ሠዐረንም ከመቅጽበት አጣፈረው ። ሠዐረ እንዳመሉ “ወዲ አይተ!” ለማለት እንኳ ቅጽበታዊ ፋታ አላገኘም ። ተደመመ ። ምንዳዬ ጥንስስ መሰለ ።



የእስረኞቹ ካቦ “የሻማ!” ብሎ እንደገና ሙኾባቸው ። ሠዐረ የመጣው ይምጣ አለና ፤ “የብልናን! ወዲ ኸልቢ ! ፖሊሲያ ወሰዱት !”

“ቡሽቲ! ሽረ እናክን!” ብሎ ምንዳዬን ሆዱ ላይ በቡጢ ሲመታው ምንዳዬ ወደፊት ጎንበስ አለ ። እንደገና ከሥር በቡጢ ሽቅብ መታው ። ከንፈሩ ተሰንጥቆ ደማ ። ሠዐረ ክፉኛ ተናዶ ተራውን እንደሚጠብቅ ሰው ተገትሯል ። ካቦው በንቀት ተጀንኖ እንደ ቆመ ፤ ምንዳዬ ብልጭ አለበት ። የሠራ አካላቱን ወረረው ። በሥራ ብዛት ለፍቶ እንደ ጉማሬ ቆዳ በደደረ እጁ አፍንጫው ላይ ጠዘለው ። ድንገት በኃይለኛ ምት የተነረተው ካቦ እጆቹን አንጨፍሮ ሲወድቅ እስረኞቹ ተጯጩሁ ።

ምንዳዬ “እስቲ አባቱ ሲነካኝ አያለሁ! አንድ ሰው አንቄ መሞት አያቅተኝ?” ብሎ የከረረ ቡጢውን እንደ ጨበጠ ፤ ዐይኑን ጕልጕሎ ቆመ ።

“እኛ ብሕጊ ነው የመጣን ፤ ከይትነኸኡና ነገር ከይታመጡ! እንተዘየሎ ተታሐሐዝና ንሞታል ! ለእናንት የሚፈራ የለም!” አለ ሠዐረም ለመማታት ተዘጋጅቶ ።

አንዳንዶቹ እስረኞች ሲፈሩ ፤ ሌሎቹ በተደፈርን ባይነት ከየቅጣጫው አፈጠጡ ። በጡብደሉ ካቦ የተበደሉት ግን ፤ “ጎሽ! ወንድ! በኛ ተለምዶ! አብዝቶት ነበር ! እንዲህ አንዳንድ ጊዜ እንኳ ይቅመሳት እንጂ!” አሉ ውስጥ—ውስጡን ። ካቦው የደማ አፍንጫውን እየደባበሰ ቀና አለና ፤ “እንዳትነኩት! ‘ሪንጉ’ ኋላ ይከፈታል! አልቢትር እኔ እመርጣለሁ” ብሎ ተቀመጠ ።

ምንዳዬ ፤ “ግድየለህም አታስብ! ሁለት ነፍስ አልያዝኩ! ምንን ኋላ ድረስ አስኬደህ!! የወንድነት ተሆነ ይኸነዬ ነው” ሲለው ፤

“እኛ ፈራሕ ሰዎሽ አይንምሰልካ! ቦርኮ! ቴስታ ዲጋሊና! ከፈለካ ናዓ!” አለው ሠዐረ ።

የእስረኞቹ ካቦ ፤ “ግድ የለም! ለሁሉም ያደርሰናል!” ካለ በኋላ ወደ ሌሎቹ መለስ ብሎ ፤ “እናንተ ደሞ አትገተሩብኝ ተቀመጡ! የዶሮ ላባ ሁሉ ተሰብስቦ!” ብሎ ገላመጣቸው ። ከእነ ምንዳዬ በስተቀር ሁሉም ተቀመጠ ። ክፍሉ ጸጥ አለ ።

ከተዘጋው የብረት በር አናት በላይ ከብረቱ ፍርግርግ ፋካ ጀርባ ተንጠልጥላ የምትበራው አምፖል ፤ በሲጋራ ጢስ ቀልቃ በበራሪ ነፍሳት ኩስ ቆሽሻለች ።

ካቦው በዝግታ ተራምዶ እነ ምንዳዬ አጠገብ ቆመና፣ “ጨብጠኝ! ብራቦ! የኛ ካስየስ ክሌይ! ሶኒ ሊስተን!” ብሎ በትዕቢት እየሣቀ እጁን ዘረጋ።

“ቫይ ቪያ! ዲስክራሲያቶ!” አለ ሠዐረ።

“ዋ! ዛሬ ቀን! ወጊድ ብየሃለሁ ሰውዬ! አሳር እንዳይከተልህ!” ብሎ ምንዳዬ ቡጢውን አዘጋጀ።

“ምን ግቢሩ ትለናል! አንተ ሰውዬ የምታመጣ ነገር አለ ዛሬ ቀን! ወዲ ካኔ!”አለ ቱግ ብሎ።

“ምነው አንተ ብትተው! ደህና ሰው አልነበርክም እንዴ?” አሉ አንድ ሽማግሌ ቢጤ ካቦውን።

“ዝምበል! የቡሃቃ ሌባ! ሐድና ማድቤት ለማድቤት ሊጥህን ድፋ! አጅዛ !!” አላቸው ዘወር ብሎ። አልመለሱም።

ካቦው፣ “በል ተወው፣ ረጋ ብለን እንጫወታለን! ይቺን የሽሮ ድንፋታ እናውቃታለን” ብሎ ተመልሶ ተቀመጠ። አንዳንድ ሞገደኛ ሰው ሲያጋጥም፣ አረጋግቶና ተመራርጦ በመደብደብ፣ ምናልባት የደበቀው ገንዘብ ካለም ፈልፍሎ ማውጣት፣ አለበለዚያም በማግስቱ እንዲያስመጣ ቃል ማስገባት የተለመደ ዘዴ ነው።

እንደገና ጸጥታ ሆነ።

ከእስረኞቹ መኻል አንዱ፣ “ለምን የሻማ ክፍላችሁ በሰላም አትተኙም” አለ።

“እሁን ከየት ናመጣል?”

“የነበረንን እኮ አስረክቡ ተብለን አስረክበናል — የት አለን!” አለ ምንዳዬ በቁጣ።

“ምን ያስቆጣሃል ታዲያ? ደርቲ! ጢት እናመጣለን አትሉም!!” አለ ሌላው።

“አይትሳደብ! እዚህ ሁላችን ሐደ ኢና! ኢቐራንቲ!”

“ቀድሞ ነገር ማ አናግሮን! ከውጪ ዱላ ከግቢ ዱላ!!”

“ተአብ አታብዛ! — —ገንዘብ አስመዝግባችኋል!!” አለ አንድ ባለ ሰላላ ድምፅ።

“ጢት ስንት — ስንት ትከፍላላችሁ?” አለ ሌላ ቃጭል ቢጤ።



“የምን ጥያቄ ማብዛት ነው፥ ካድረ ባለቀፎዋን ነዋ! አምስት ገቢሬ!”

“እንዲህ በወጉማ መጠያየቅ ያባት ነው። እናንተ ታዲያ በየት?” አለ ምንዳዬ።

“የሻማ እንደሚከፈል አታውቅምና ነው?! ጉረኛ !!” አለ ሌላው በንቀት።

“አፉ! እባካችሁ ዝም በሉ! እንተኛበት!! አያስቸኩልም!!” አለ ሰባራ አንኮላ መሳይ ጉሮሮ።

ምንዳዬና ሠዐረ እንደ ቆሙ፣ ሁሉም እግሩን ወደ ቤቱ መኻል እየ ዘረጋ ተኛ። በግድግዳው ዙሪያ ካርባ በላይ ጭንቅላቶች፣ እቤቱ መኻል ከየልብሱ ሥር ብቅ—ብቅ ያሉ ከሰማንያ በላይ እግሮች። በእግሮቹ ጣልቃ—ጣልቃ ወደ ተለያዩ አቅጣጫ የተኙ ሰዎች። የአብዛኛዎቹ ጸጉር ተንጨብሮ የተቆጣጠረ፣ የገላቸው ላይ ፋክት መስመር፣ በየጥፍራቸው ስፋት መጠን የተሰበጣጠረ፣ ጭቅቅት የጠገበ ሸሚዝና ካናቴራ፣ የብብትና የገላ ቅርናት፣ ክፍል ውስጥ የሚሸናበት ገረወይና ግማት፣ የልዩ ልዩ ሰዎች ትንፋሽና ላብ ድብልቅልቅ ክርፋት፣ እስኪለመድ ቅልብሽ ከሚያሰኝ ሁኔታው ጋር ራስ ይመታል። ግድግዳው ላይ የተገደሉት ቱኋኖች ደም መጠኑ የተለያየ የቃለ—አጋኖ ምልክት መስሎ ጠቋሯል።

የእስረኞቹ ካቦ፣ ሌሊት በነምንዳዬ ላይ የሚፈጽመውን በቀል እያሰላሰለ፣ ከሌሎቹ በተሻለ ደባደቦ ላይ ተንጋሎ ጣራ ጣራውን ያያል። እነ ምንዳዬ፣ እዚያው ማዕዘኑ ጋ ትንሽ ቦታ አግኝተው ጠጋ ሲሉ የሽንት ገረወይና አፉን ከፍቶ ተቀበላቸው። ምንዳዬ ተናነቀው።

“ማ!እንታይ ዝአመሰለ ዕላጅ'ዩ!” አለ ሠዐረ። አንዱ ሣቀበት።

“ማ አባቱ ነው እሚሥቀው!? ምናለ ብትተዉን?!” አለ አንዱ እየተነፋነፈ።

“የሰው አባት አትሳደብ እከካም!” ብሎ መለሰለት።

“ዛሬ እያንዳንድሽን ነው እምረግጥሽ!” አለ ካቦው።

“አህያውን ፈርቶ ዳውላውን” ሳይል አልቀረም አንዱ በልቡ።

ምንዳዬ የደረሰበትን ጉዳት ሲያሰላስል እንቅልፍ ባይኑ አልዞረም። ሠዐረ ወለሉ ላይ ዘርፈጥ ብሎና ግድግዳውን ተደግፎ፣ ጭንቅላቱን ጉልበቱ ላይ አሳርፎ ያንጎላጃል። ካቦው እነሱን ለመበቀልና ሽንት ፉት ለማሰኘት፣ ዘሎ ጉብ የሚልባቸውን ደቂቃ ይጠባበቃል።

እስረኞቹ በተለያየ ድምፅ ያንኮራፋሉ ፤ ይቃዣሉ ፤ ይባንናሉ ። አን ዳንዱ “ውሸት ነው! እኔ አላየሁም! እምላለሁ! ገርፈውኝ ነው! ማንም ይጠየቅ! አልነበርኩም! በግድ እመን ከሆነ እሺ! ታዲያ ምን ሠርቼ ልብላ! — —” ይቃዣል ። ካቦው ቀና ብሎ ሲያይ ከምንዳዬ ጋር ዐይን ላይን ተጋጩ ። አንዱ የሌላውን ሐሳብና ዝግጅት ያወቀ ይመስል ተፈራሩ ። ካቦው ችላ ብሎት ተኛ ።

ከንጋቱ 12 ሰዓት አካባቢ ፣ ሁሉም ተራ በተራ ወደ ሽንት ቤት እየሔዱ በፍጥነት ሲመለሱ፣ ምንዳዬና ሠዐረ በገረወይና ሲጠራቀም ያደረውን ሽንት አውጥተው እንዲያፈሱ በፖሊሶች ታዘዙ ። ረፋዱ ላይ ቃላቸውን እንዲሰጡ ወደ ጽ/ቤት ሲወሰዱ ሠዐረ በዚያቹ አጋ ጣሚ ወደ ቤቱ መልክት ላከ ። ባለቤቱም ሁኔታውን ለነሕድሩ ስት ነግር ፣ የምንዳዬ መታሰርም ለሞገስ እምባቸው በስልክ ተነገረ ።

ሞገስና ቀኛዝማች ፣ 5ኛ ፖሊስ ጣቢያ ለመድረስ ጊዜ አልፈጀባ ቸውም ። በሚያውቁት መንገድና በለመዱት ብልሃት ተሯሩጠው ሁለቱ እስረኞች 48 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ 6ኛ ወረዳ ፍ/ቤት ቀርበው በዋስ እንዲለቀቁ ተደረገ ። ክሱም ከሦስትና ከአራት ቀጠሮ በኋላ በአነስተኛ የገንዘብ ቅጣት ተዘጋ ።

ከዚያች ምሽትና ሁኔታ ጀምሮ የሠዐረና የምንዳዬ ጓደኝነት በይበልጥ ጠበቀ ። ሌሎች የማያሳዩትን የአሠራርና የአጠጋገን ብል ሃት በማሳየት፣ችሎታውን እንዲያዳብር ረዳው ። ያን የተቀጠረ ሰሞን እየተብረገረገ ሲፈነጣጠቅ፣ “እንዲያው ምን ጉድ ይሆን ?” በማለት የተገረመበትን የመበየጃ ቀላጭ ብረት ፣ ዛሬ እንደ ልጅነቱ የጅራፍ ቀንዲላ ይዞ እንደልቡ እያገላበጠ ሲበይድበት ይገርመዋል ። ያን ፣ “ያንተ ያለህ! የዝግንትል መዓት ፣ ምኑን ከምኑ አቆራኝተው አቆላ ለፉት” እያለ በተመስጦ ሲመለከተው ስለ ነበረው የመኪና ሞተርም በእጁጉ አወቀ ።

ሠዐረ ፣ የሞተርና የፍሬን ጥገናና እድሳት የተደረገላቸውን መኪና ዎች ለመፈተሽ በሚወጣበት ጊዜ ፣ “እሱ ማኪና ብታሽግር ይረዳል” በሚል ሰበብ እየያዘው መሔድ በመጀመሩ ፣ ቀስ—በቀስ መኪና እን ዴት እንደሚነዳ ማወቅ ጀመረ ። ከብዙ የፍተሻ ጉዞዎች በኋላም ፣ “ይቺ ማኪና ብትይዛት ምዝዋርዶ ትሽላለህ ?” ብሎ ጠየቀው ።

“ዛሬስ አያቅተኝም” አለው በፈገግታ ።



## ምዕራፍ ዐርባ ዘጠኝ

ሸዋርካብሽ ውል በሌለው ቅጥር ወይ በመንፈቅ ወይ ባመት በሚሰጥ አልባሌ ቀሚስና ነጠላ ፣ በእንዲህ ያለ ጊዜ ቀን ይወጣልኛል ይከንዱ ስለገዛ ኑሮአቸው ከማውጠንጠን በቀር ፣ እንዲች ብለው እንደ ማያስቡላት ታውቃለች ። በእርግጥም ሴትዮዋ አዲስ አበባ በተዋወ ቁአቸው ያገራቸው ሰዎች በኩል በሚደርሳቸው ወሬ ፣ ለወይዘሮ ደጅ ይጥኑ ተደርጓል ብለው በሚያስቡት ነገር ሁሉ የሚያንገበግብ ቅናት ስለ ነበረባቸው ፣ ስንኳንስ ለእሷ ፣ ለገዛ ልጆቻቸውም ደንታ ቢስ ሆነዋል።

ሸዋርካብሽ ፣ ተልካም ይሁን ተከትላ በወጣች ቁጥር በምታያቸው የከተማ ሴቶች ሁናቴና ፣ ሌሎች ሠራተኞች ደመወዝ እንደሚከፈላ ቸውም በማወቋ ፣ “እስተመቼ በነጣ ሳገለግል እኖራለሁ” በማለት ልቧ ሸፍቷል ። መብል መጠጡ እንደልብ በሆነበት ቤት ኑሮዋና ፣ ከአድ ካሚው የገጠር ሥራ በመገላገሏ አካላቷ ሞልቶ ፣ ደም—ግባቷም ሞቅ ደመቅ ማለት ይዞ ነበር ። አካሏም ቢሆን የሩካቤ ሥጋ ጥያቄ ማቅረብ ከጀመረ ወሎ አድሯል ። ሌላው የዘወትር ችግርዋ ግን ፣ ሐሳቧን የም ታካፍለው ሰው በአቅራቢያዋ አለማግኘት ነበር ። ምንዳዬ እንዳመሉ በሔደ ቁጥር ፣ አካባቢውን ስልላ ችግሯን የምትነግረው ለሱው ነበር። እሱም ቢሆን ቅን ጠባይዋንና ገራገር አቀራረቧን በሚገባ በማወቁ ፣ የቆየ ቂሙን እርግፍ አድርጎ ትቶታል ።

“እረ ተው ጋሼ ምንዳ—እረ ተው አጨክን ? እረ ተው እኔንም አሳልፍልኝ ?” ትለዋለች ።

“እኮ ምን ሳርግልሽ ?—እማረግልሽ እኮ ነው የቸገረኝ?” ይላታል ባዘኔታ ።

“ተው ተየህ ተቤት ጉላግለኝ ?! ተው አንዱጋ ሥራ አስገባኝ ? ተው ግድየለህም ፣ እኔም ሰው እሆንና ዘመድ እሆንህ ይሆናል?”

“ደም ደህና እፎይ ያልኩትን ነገር ልትቀሰቅሽብኝ ነው? ወዲት ገባች ቢባልስ ?”

“እረ ተው ካንጀትህ አውጋ ! አንተ ብቻ እሺ በለኝ ፣ እኔ አቅብ ታለሁ ፣ እሌላ ጋ ሥራ አግኝቼ ሔጃለሁ ብላለች ብላችሁ ንገሩልኝ እላ